ቦሌ ክፍለ ከተማ

ዓመታዊ

ሽ.③ ከ 201-ሙጫቂሻ

"እሮጊት አይደለሁም ።"

"የለም ፣ ልጃገረድ ነሽ እንግዲያው ።"

ይቀጠላሉ ።

ሚስተር እስተርን ለሚያነበንበው ነገር ፣ ሚስተር ሮዜንታል መልስ
ሳይሰጥ ዝም ያለ እንደሆነ ፣ " ምን ይዘጋሃል ?" ሲል ይደነፋል ።

"እንተስ ምን ያንጣጣሃል ? ! ለዚህ ያበቃኸኝ መቼ አነሰህ ?"

"እኔ ነኝ ያሰርኩህ ?"

"እንተው ነህ ምክንያቱ ! "

"እውነቱን ታሪክ ነው የጻፍኩት ። ደግሞ እስቀድሚ አማክሬሃለሁ
ለዚህ ወፈፌ ጠበቃ ቁምለታ ! እንተም ከእርሱ አትሻል ።"

"ወፈፌ ነኝ እኔ ?"

"የምንጣጣ ፍየል ምላስ ነኝ እኔ ታዲያ ?"

ጥርስ ይጋጠጣሉ ።

ብዙ ዓመታት በሰላምና በስምምነት ኑረው ፣ አሁን ምን እንደ
ካቸው ምክንያቱን ራሳቸውም ሊረዱት አልቻሉም ። ምናልባትም
ካሰፈታዳቸው በአንድ ጣሪያ ሥር፣ በአንድ ግድግዳ ከልል ውስጥ በ
ንድነት እንዲኖሩ በመደረጋቸው ፣ በፊት የየራሳቸው ጓዳ ይችለው
በረው ዐመለቸውን ሰላወጣው ሊሆን ይችላል ። ወይም አስረኝነቱ ሆ
ባሻ አድርጓቸው ይሆናል ።

ውጥረቱ እጅግ የሚብስበት ቀንና ሁናቴም አለ ።

ማታ መብራት ጠፍቶ ባልና ሚስቶቹ በየጥንዳቸው ሲጋደሙ
የቀኑን ብሽቀት በአንዳች ዐይነት ሰማካካሰም ይሁን ከልብ በመነ
ፍቅር ከአንዱ በኩል የወሲብ ስሜትን የመፈጸም ፍላጐት ይነሣባ
የሚሰዮን ባህል ነውና ማፈር መጨነቅ አለ ። ግን መሆኑ አይተርፍ
ልዩ አተነፋፈስ ፣ ልዩ እንቅስቃሴ ሲሰማ ደግሞ ከሴላው ጥንድ ጆሮውን
አንቅቶ የሚያዳምጥ ፣ የሰው ሰሚት ውስብስብ ነውና ሴላም ሴላም የሚ
ያስብ ይኖራል ። ምናልባትም ጥርሱን እያፋጨ ። ከዚያኛውም ጥንድ
ቢሆን ፣ የሚያዳምጠው ፣ ወይም ሴላ ሴላ ነገር የሚያስብ ከአጠገቡ እን
ዳለ ስለሚሰማው ፣ የወሲብ ከንዋኔው በዚያው ላይ ብቻ ያተኮረ ወይም
የረጋ ስላልሆነ ብስጭትና ሠቅቀን የተቀላቀለበት ይሆናል ። ጧት ታዲ
ሲተያዩ ዐይንህ ላፈር መሆን ነው ።

ቴዎድሮስ፣ የእስተርንን ጽሑፍ ምሥጢር እንዴት አገኙት ? የ
ለው ጥያቄ ሲነሣም እንደዚሁ ነው ።

"የጻፍኩት ለብቻዬ ፣ ያስቀመጥኩት ከቤቴ ፣ እኮ እንዴት ዐወቁ ?"
ሲል ደግሞ ደጋግሞ እስተርን ይጠይቃል ።

"መቸም በቅርብ ያለሁት እኔ ነኝና ጠርጥረኸኝ ከሆነ እሱው እን
ዳወቀ ይፍረድብኝ" ስትል ሚስስ እስተርን የሹራብ ሥራዋን ሳታቋ
ርጥ ፣ ክፍሉን በሙሉ በመቃኘት ትተበላለች ።

"ዛዲያ ማንን ማለትሽ ነው ?" ሲል ሚስተር ሮዜንታል እጁን
ይቀስራል ።

"እኔ እንጃ ።"

"እኔ ማንን አልኩ ?"

ሁሉም ዐይናቸውን ያጉረጠርጣሉ ። ሚስስ ሮዜንታል ግን ፣ ከው
ስጥ ጥርጣን ትበላለች ። ይህ ጥያቄ በተለያየ አቀራረብ ብዙ ጊዜ ከተደ
ጋገመ በኋላ፣አንድ ቀን ሚስስ ሮዜንታል መቻል አቃታትና አፈረጠችው ።

"እኔ ነኝ ! እኔ ነኝ የተናገርኩት " ስትል ሮዜንታል ሙሽቸ ፣
ሚስተር እስተርን ለስንተኛ ጊዜ ከቁርስ በፊት በቁርስ ፈንታ ላቀረበው
ጥያቄ ። ጆሮዋቸውን ማመን አቅቷቸው ሦስቱም ፍጥጥ አድርገው ተመለ
ከቷት ።

"አዎ ! እኔ ነኝ ። የምታደርጉትን ማድረግ ትችላላችሁ ። ከማያ
ቋርጥ ንዝንዛቸሁ አደብሰም " አለች በሚንጨረጨር ድምፅ ።

ከረጅም ጊዜ ዝምታ በኋላ፣ "ግን ለምንድን እቴ? " ስትል እንደ
ወስፈ በሰላ የአሽሙር ለዘብታ ሚስስ እስተርን ጠየቀቻት ።

"እንጃ ! እንጃ !" አለች ሚስስ ሮዜንታል እሁንም በጩኸት ።
ከዚያም ሳያታወቃት ዕንባዋ ባራት መሥመር ይወርድ ጀመር ። በዕን
ባዋ መጋረጃ ውስጥም ፣ በንኖ የሚጠፋው ሁሉ ምኞቷ ፣ ጭጋግ ለመሰለ
የሚሲዮናዊ ሕይወትና በመጨረሻም ከእነርሱ ጋር አብሮ ለእስረኝ
ነት የዳረጋት የዕድልዋ መጨረሻ ታያት ።

"እም ! ጉድህን ያወጣሁት እኔ ነኝ" አለች እንደገና ሚስስ ሮዜ
ንታል ፣ ከሐሳብ ትርጓሌዋ ስትመለስ በሚስተር እስተርን ላይ ዐይንዋን
አፍጥጣ። ተበዳይ እርሷ እንደ ሆነች ያህል ፍልሚያ የሞ ትጠይቅ ትመስል
ነበር ።

ሚስስ እስተርን ፣ ከሥር የሚፈላ ድፍድፍ እንደሚገፋው የማሠር
ከዳን ደረቷ ከፍና ዝቅ እያለ፣ጥቂት ጊዜ ዝም ብላ ተመለከተቻትና ድንገት
ተወርውራ ገብ አለችባት ።

ጠባቂዎቹ ጩኸት ሲሰሙ እየተሯሯጡ ገቡ ።

"እንህ ፈረንጆች አበዱ ?" አለ አንደኛዉ የመገረም ሣቅ እየመጣ
በት ።

Meysor Bro
t.me/BooksandYou

ታንጒት ፣ ሥጋቱ የተሰማት እያደር ቀስ በቀስ ነበር ።

አቡነ ሰላማ ፣ የጠየቋትን ሥርየት ፈጽማ ደብረ ታቦር ከተመለሰች ከጥቂት ወራት በኋላ ፣ በድፍን ጐንደር የታወቁ የነበሩት ወይዘሮ ደብሬ ፣ ላሙና በር አጠገብ ከፈሩ ውስጥ ሞተው መገኘታቸውን ወሬ ሰማች ። ማን እንደሆነ ባይታወቅም ፣ በጐራዴ ወግቶ የገደላቸው ሰው ነው ይባላል ። ወሬውን ቀድመው ያገኙት የዓለሜና የእንግዳ ሚስቶች ሲሆኑ የነገሩዋትም እነርሱው ነበሩ ። ከወይዘሮ ደብሬ ጋር የነበራትን ወዳጅነት እያወቁ ቤተ ክርስቲያን ላይ እንደ ዋዛ በድንገት የነገሩዋት ፣ በአደባባይ አሬታዋን ስትለቀው ፣ በሆዳቸው ለመጣለቅ መሆኑ ገባትና እንደ ምንም ችላው ቤቷ ደረሰች ። ከዚያም ሁለት ቀን ሙሉ ብቻዋን እያለቀሰች እርሟን አወጣች ።

የመጨረሻ ስንብታቸው ሁኖቱ ታወሳት ። ‘እኔ ነኝ ተዚህ ሁሉ ጣጣ ያስገባሁሽ ። ላንቺ ነው እንጂ የምሠጋው እኔማ ተንግዲህ ወዲህ ብጠፋኝ፡ ለነፍሴ እሆናለሁ እንጂ ምኑ እንዳያቀርብኝ ? በኔ ላይ እንደሆነ ያሰቡትን ይሥሩ ’ እያሉ ከሆዳቸው ሊያስገቡዋት የፈለጉ ይመስል ፡ ጭምቅ አድርገው ዐቅፈው እየተንሰቀሰቁ አልቅሰው ነበር ። ያን ጊዜ ልብ ባትለመም አውን እንደገና ስታስታውሰው ፡ አንድ ወይንት ከባድ ፍርሃት አድሮባቸው ሳይሆን አይቀርም ነበር ። ምን ነበር ያስፈራቸው? የዚያን ጊዜ ፍርሃታቸው ከአሁኑ አሟሟታቸው ጋር ዝምድና አለው ይሆን? ጐንደር ሔዳ ለመላቀስና በዚያም አሟሟታቸውን በትክክል ለማወቅ ሐሳብ መጥቶባት ነበር። ነገር ግን ፡ የምታላቅሰው ሁኖኛ ዘመድ በቅርብ እንደሌለና ቴዎድሮስ በጐንደር አካባቢ እያለ ለገብርዬ ሳትነግር መሔዷ ደግ እንዳልሆነ ስትገነዘብ መልሳ ተወችው ። ‘ነዘንሞንና ሐሳብሞን በሆድሞ ተብራ ዝም አለች ።

ከጥቂት ወራት በኋላ ደግሞ ፡ የፈላሻ ሚሲዮናውያን መታሰር ወሬ መጣ ። ስለ ታሰሩበት ምክንያት መጀመሪያ የተረጋገጠ ነገር አልነበረም ። የተምታታ ነበር።አንዱ፡‘ቴዎድሮስን በአደባባይ ስለዘለፉዋቸው ነው’ ይላል ። ሌላዉ ፡ ‘ብዙ የብራና መጻሕፍትና የብር መስቀል ይዘው ወደ ሀገራቸው ሲሔዱ ተያዙ’ ይላል ። ‘በእርግጥም በኩል ከቱርኮች ጋር ሲላላኩ ስለተገኙ ነው’ የሚልም አለ። ያምሆነ ይህ፡ታንጒት ለእስረኞች ትንሽ

አዘኔታ ቢሰማትም ጉዳዩን ከራስዋ ጋር አላያያዘችውም ነበር ። ቴዎድሮስ ፣ ምሕረታቸው አጠር ፣ ቁጣቸው ከረር ፣ ቅጣታቸው ከበድ እያለ ሐዲ እንደ ገለልተኛ አስተናጋጅችው ።

ቆይቶ ወረው እየተጣራ ሔዶ ፣ ከሚሲዮናውያኑ አንዱ እስተርን የተባለው የቴዎድሮስን ታሪክ አራክሶ መጻፉ ተረጋገጠ ።

አሁን ባያስደንግጣትም ከነከናት ። ከእናትዋ እንደ ሰማችው ስለ ቴዎድሮስ ዘርና አስተዳደግ እርቧም ነግራው ነበር ። 'ዛዲያ ከነገረችው ምኑ ነው ያስቆጣው ?' ፣ ለመታዘብ ያህል ፣ ጥዋ እያባዘተች ወይም እየፈተ ለች ጉዳዩን እንደዋዛ ስታብላላው ፣ ሕሊናዋን የሚፈታተኑ ብዙ ሐሳ ቦች ይመጡባታል ። ስለ ትውልዱና ስለ አስተዳደጉ ለእስተርን የነገረ ችው ከእናቷ የሰማችውን ቢሆንም፣ቴዎድሮስ ራሱ ለሰው ከአሜአቱውና ከሚያሜውተው የተለየ አልነበረም ። በተራ ዘርነቱም ፣ በድህነቱም እያ ፍርበትም ። እንዳንድ ቅሬታ ቢኖራትም ፣ ቴዎድሮስን ታደንቀዋለች ። ትመካበታለች ። እንደሚያስብላትም ታውታለች ። ታዲያ አቡነ ሰላማ መጀመሪያ ሲጠይቋት እንደ ፈራችው ሳይሆን ፣ አስተርን እንዳለው ታሪ ኩን አሳምሮ የሚጽፍለት ከሆነ ፣ ቴዎድሮስም እውነተኛ ታሪኩ መታ ወቁን የማያፍርበት ከሆነ በማለት ነበር የነገረችው ። ግናስ ይግሞ ? ብላ ራስዋን ትጠይቅና ፣ ሕፃን ሳለች እናትዋ የነገረቻት ሁሉ ሲታወሳት ራስዋን ትጠራጠራለች ።

እናትዋ ካለርስዋ ያልወለደች ፣ የህልውናዋን ዓላማና ፍቅርዋን ሁሉ ላንዲት ልጅዋ የሰጠች ፣ ከደማነቷና ከፍቅርዋ ጋር የተፈጸመባት በደል ዘወትር እየተሰማት የጠወለገች ባልቴት ነበረች ። ሸክላ ስትሠራ የዋለችበትን እጅዋን ከተጣጠበች በኋላ ፣ የሕፃን ፊትዋን እየጠራረገች ላት ፣ 'ራበሽ ያይኔ ዓለም ? አይዞሽ ። አሁን ምሳ ይደርሳል ። እስተዚያ ቆሎ ቆርጥሚ ። መቸስ ምን ይደረግ ? ባይልልን ነው ። ግና ዘሬችን ባይ ወደድ ፣ ዝምድናችን ባይፈለግ ፣ ምንተዳችን ! ሠርቶ ማደር አያቅተን' ትላት ነበር ።

ታንጉት አባትዋን አታውቀውም ። ሞሲጋ ደርሶ ሲመለስ ሽፍታ አደጋ ጥሎበት የሞተው ገና አንድ ዓመት ሳይሞላት ነበር ። እሷም ፣ ገና ሳትወለድ አንሥቶ ፣ በበሽታ ከመ ደብ ላይ የዋሉት ሴት አያትዋም የሚ ኖሩት በእናትዋ የሸክላ ሥራ ነበር ። ግን ምንም ቢሆን ጉርሮዋቸው ተዘግቶ አድሮ አያውቅም ።

ታንጉት ፡ ሰባት ዓመት ገደማ ሲሆናት እናትዋን በሸክላው ሥራ ለመርዳት ፈልጋ ነበር ። አልፈቀደችላትም ። 'ይህንንስ ሙያ እጅሽ አይነካውም ። እኔ ቁሚ እየሔድኩ ። ባይሆን እንደ ዕድልሽ ሴላ ሴላውን ትደርሽበት ይሆናል' በማለት ከለከለቻት ። ምክንያቱን ሳትነግራት ታንጉትም ሳይገባት ቆየች ።

ወሥሮ ዓመትዋ ገደማ ፣ አያትዋ እንደ ሞቱ ፣ በዚያን ጊዜ በቋራ የታወቀ ጭቡዝ የነበረው የዛሬው ቴዎድሮስ ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ መጥቶ ጸቦ ቆሎ ከሰጣት ከሰንት ጊዜ በኋላ፣እንደገና አንድ ቀን ብቻውን መጣና ከእናቷ ጋር ብዙ ተነጋገሩ ።

ከደጃፍ ጥግ የተቀመጠችው ታንጉት ፣ ካሣ እንደሚለምን ዐይነ ት እንጉቱን ደፍቶና ቀስ ብሎ የሚናገረው ባይሰማትም ፣ እናትዋ ራስዋን በእምቢታና በምሬት እየነቀነቀች መልስ የምትሰጠው ከፍ ባለ ድምፅ ነበር ። 'ፈጥሞ የማይሆን ነገር ነው ! ጹር ዱር ቀረ ።

'የናቴ አጥንትም ይረግመኛል ።'

'እኔ በሕይወት እስካለሁ ምንም ችግር የለብንም ።'

'እናቴ በሰማይ በምድር ቃል ይዛኛለች ። ተዚያ አልወጣም ። ምንም ቢሆን ።'

'እንተ ምን አጠፋህ ? ባባትህ ጉዳይ አትጠየቅበት ! ግና የናቴ ቃል ደግሞ ቃል ነው ።'

ተሰነባብተው ሲሔድ የተጣሉ አይመስሉም ነበር ። ግን በመካከ ላቸው አንድ ከባድ ጉዳይ እንዳለ ታንጉት ተሰምታት ነበር ። ከዚህ በኋ ላም ፣ እህልና ከብት የያዙ ሰዎች ሲመጡ እናትዋ አልቀበልም እያለች ብዙ ጊዜ ትመልሳቸው ነበር ።

ታንጉት ምሥጢሩ የገባት ቆይቶ ፣ ቆይቶ ነው ።

እናትዋ በድንገተኛ በሽታ ሞታ ታንጉት ከዘመድ ቤት ተቀምጣ ላለች ሰዎች መጥተው ፣ ከዘመዶቿ ጋር ተነጋግረው ወደ ካሣ ሠፈር ይዘ ዋት ሔዱ ። ያን ጊዜ ስሙ በድፍን ቋራ የተጠራ ሆኖ ነበር ።

በካሣ ፡ በኋላም በቴዎድሮስ ቤት ያደገችውና የኖረችው ፣ በፍቅርና በእንክብካቤ ተይዛ ነው ። የቂም ጠባሳ የሚተው በደል ተፈጽሞባት አያውቅም ። ስታጠፋ ካሣ ቢቆጣትም ፣ ቢቀጣትም እንደ ባዕድ ሳይሆን እንደ እኅት ፣ እንደ ልጅ ነበር ። ሚቿ ተዋበችም እንደ ልጅ ነበር የምታ ያት ። በኋላም ገብርዬን እንድታገባ ስትደረግም ፣ በመጀመሪያ ፈቃድዋን ተጠይቃ ነበር ።

የለም ። በጊዜው ፣ እየታወቀት ሆነ ብላ ቴዎድሮስን ለመጉዳት ያደረገችውስ አልነበረም ።

''ወዳጄችን የቴዎድሮስን ታሪክ አሳምሮ ሊጽፍ ተነሥቷልና ፣ ለኃጢአትሽም ሥርየት ፡ በምታውቂው ነገር ሁሉ እርጅው'' ብለው አቡነ ሰላማ ጠየቋት ። 'እሺ' አለች ። በጊዜው እምቢ ለማለት የማት ችልበት የራስዋ ምክንያት ቢኖራትም ፣ ከመሠረቱ ከአቡነ ሰላማ ጋር

በቅርብ እንድትወዳጅ ፡ አንዳንድ የሚጠይቋትንም ነገር እየፈጸመች ፡ እየ ጋበዘችና እያስተናገደች ፡ የሚሥሩትንና በቢታቸው የሚሆነውን ነገር ሁሉ እንድትነግረው ያዘዛት ራሱ ቴዎድሮስ ነበር ። ምናልባት ፡ ከመ ጀመሪያ ባትቀርባቸው ኖሮ ይህ ሁላ ሊደርስ አይችልም ነበር ይሆናል ። ቴዎድሮስ፡ አቡነ ሰላማን እንደሚጠረጥራቸው ገብቷታል ። ከዚያ በፊት ያገኘችውንና ጠቃሚ የመሰላትን ሁሉ ስትነግረው ኑራለች ። አቡነ ሰላማ በመጨረሻ የጠየቋትን መንገር ነበረባት ? ስለ ነገረችው መነሻ የሆነ ውን ጥፋቷን ይምራት ኖሮ ይሆን ? ሌላው ቢቀር ፡ ለሚስተር እስቱርን ከነገረችው ብዙውን የማታውቅ መስላ ማስቀረት አትችልም ነበር ? ምና ልባት የአያትዋ ቃለ - ግዝት የእናትዋ ምሬት በስውር ሕሊናዋ ከተ ቀበረበት ወጥቶ ለመበቀል ፡ ወይም ለመጉዳት ሞምሮ አድርጋው እንደ ሆነስ ?

ቴዎድሮስስ ቢሆን እሱ እንደ መሰለው ፡ ስሙን ለ ሂያጠፋ የነገ ረበት ማን መሆኑን ከሌላ ዘንድ ሲሰማ ፡ በቅንነት ወይም በሞንቀት ያደረገችው መሆኑን መች በቀላሉ ያምናታል ? በሚችች ፍላጐት የተቀ በረውን ፡ ራሱም ደብቆ የያዘውን ምሥጢር የምታውቅ መሆንዋን የሚያውቅ አይመስልም።ወይም እያወቀ የማያውቅ መስሎ ሊሆን ይችላል።

ያም ሆነ ይህ ነገሩ ሲወጣ ፡ ‘ የአያትሽን ቂም በቀል በእኔና በሚች እናቴ ስም መጥፋት መወጣትሽ ነው ?’ ብሎ በንደሌት ሲታጠል ታያት ። የፍቅሩን ፡ የደግነቱንና የርኅራሄውን ያህል በተለይ አሁን አሁን ምሬ ቱና ቁጣው ደግሞ ፡ ራሱንም ሌላውንም የሚያታዮል እሳተ ነበልባል መሆኑን ታውታለች ።

ታንጉት ፡ አሁን እንደገና መለስ ብላ ስታስበው ሌላም የሚከነክ ናት እንቆቅልሽ አለ ። ፈታዳቸውን እንድትፈጽም የሚያድርጉበት ሰበብ ቢኖርም አቡነ ሰላማ፡ ስለ ቴዎድሮስ ዘር ፡ ዘመድና አስተዳደግ ከሌላው ሰው ሁሉ የበለጠ እርሰዋ የውስጡን የምታውቅ አድርገው ለምን ጠየ ቋት ? መቸም ቀራቢ ናት ብለው በእጋጣሚ ነው ? ወይንስ ሌላውንም ምሥጢር በማወቃቸው ? ከሆነስ እንዴት ዐወቁ ? እርሷ እንደምታው ቀው በሕይወት ያሉት የምሥጢሩ ባለቤቶች እርሷና ቴዎድሮስ መሆን አለባቸው ። እንዲያው ምናልባት አባቱ ዐውቀው ፡ እሰ ም ከአባቱ ሰምቶ ከሆነ ሌላው ጋረድ ነበር ። በሕይወት ሳለ ፡ ሌላ ስሜቱን ቢገልጽም ይህንን ግን የሚያውቅ መስሎ አይታይም ነበር ። ከሞተ ስንት ዓመት ሆኖታል ። ደግሞስ ካልጠፋ ሥፍራ ከፈረንጅ ጋር ያብረ ብርሃን ሥላሴ መቃብር ቤት መገናኘታቸውን የመረጡት ለምን ነበር ? የሚፈሩት ነገር ቢኖር ነው ? ሌላ ምክንያት አላቸው ? ወይስ ይኸውም እንዲጋጣሚ ቤተ ክርስቲያን ከመሳለም ጋር ያመቻል ብለው ነው ?

ታንጉት ፡ ይህንን ሁሉ ስታሰላስል ሞንቀት እያረገዘች ሔደች ። በምክርና በሐሳብ የሚያገላግላት የቅርብ ሁነኛ አላገኘችም ። ለዚህ ጊዜ

የምትሆናት ተዋበች ነበረች ። ታንጉት በኋላ - በኋላ የሚገባውን ክብርና ሞገስ የነጠቀቻት ይመስል ፡ ቅናት ቢጤ ቢሰማትም ብዙ ምሥጢር ይካፈሉ ነበር ። ተዋበች ፡ ስንኳን ቴዎድሮስ ላሳደጋት ፡ ለቴዎድሮስ ባለሟል ለገብርዬ ሚስት ቀርቶ ማንንም በፍቅር የሚያገ ሰፊ ሆድ ፡ ሰፍሳፋ እንጀት ፡ ንጹሕ ልብ ነበራት ። በየዋህነት ያደረገችው መሆኑን ትረዳላት ፡ ምሥጢርዋን እንደ ራስዋ ትጠብቅላት ነበር ። ቴዎድሮስንም ልታሳምንላት የምትችለው እርሷ ብቻ ነበረች ። ብታስብ ፡ የምታምን ውና የምትተማመንበት ሌላ ሰው ማን አጣች ።

ቴዎድሮስ ፡ ከነሠራዊታቸው እስረኞቹን ይዘው ወደ ደብረ ታቦር የተመለሱት ፡ ታንጉት በዚህ ዐይነት የሐሳብ ባሕር ውስጥ በመዋኘት ላይ እንዳለች ነበር ።

የቴዎድሮስ መቃረብ ቀድም ብሎ እንደ ተሰማ ፡ ከሠፈር ቀርቶ የን በረውና የደብረ ታቦር ነዋሪ ሕዝብ ፡ ሊቀበላቸው በአደባባዩና በመሞጫ ቸው መንገድ ግራና ቀኝ ተሰባሰበ ። ወትሮም ቢሆን ዘመቻ ቆይተው ወደ ሠፈር ሲመለሱ ፡ ሰው ወጥቶ በሆታና ዕሞፈራ መቀበሉ የተለመደ ነበር ።

አሁን ደግሞ ፡ ፈረንጆቹን እስረኛች ይዘው መምጣታቸው ሲሰማ ፡ ከሚስዮናውያኑ ጋር ቅያሜ የነበረባቸውና አሁን አንጀታቸው ቅቤ የጠጣው ‘ የጋፋት ልጆች ፡’ የጋፋት መንደርና የአካባቢውን ሰው ሁሉ ቀስቅሰው ይዘው ስለመጡ ፡ ከወትሮው የተለየ ብዛት ነበረው ። ሠፈር የቀሩት የመር አለቆችና የመር አለቆች ሚስቶች ፡ ሌሎችም የታወቁ ካህናትና ወይዛዝርት ከቤተ መንግሥት ፊት ለፊት በሚገኘው አደባባይ ላይ እንደየማዕረጋቸው ቦታ ቦታቸውን ይዘው ይጠብቃሉ ።

ሠራዊቱ ገና ብቅ ሲል፡ እልልታው እንደ ዓውሎ ነፋስ ከሩቅ እያረገበ መጣ ። ሞብጨባው ፡ ሆታው አስተጋባ ።

ከፊት የቀደሙት ታፈር ፈረሰኛች ነበሩ ። ተዮሎ ብዛት ያለው እግረኛ መር ተከተለ ። ከዘመቻ መልስ ወይም በረጅ ም ጉዞ የደከመው እየቀንጠባጠበ እንዳይቀርና በጣም ሲደክምም ለማረፍ እንደ ያመች ተብሎ ፡ እግረኛው ሠራዊት ከቴዎድሮስና ከመር አለቆቻቸው ቀድሞ እን ዲጓዝ ይደረጋል ። አሁንም እንደዚሁ ነበር ። በአደባባዩ የተሰበሰበው ሕዝብ በድፍንና በእንድነት የዕልልታና የሞብጨባ አቀባበል ያድርግ እንጂ ፡ እያንዳንዱ ደግሞ በግል በዐይኑ የሚፈልገው ነበር ።

የዘመተ ባል ፡ ወንድም ፡ ዘመድ ፡ ወዳጅ በደኅና መመለሱን ለማረ ጋገጥ ። ለሐሳብዋ ሞንቀት መልስ የምታገኝበት ያመስል ፡ የታንጉት ዐይን የሚፈልገው ደግሞ ፈረንጆቹን እስረኛች ነበር ። ከእግረኛው ሠራ ዊት ቀዮለው መጡ ። ግራና ቀኝ ፡ ፊትና ኋላ ነፍጥ በያዙ ወታደሮች ከመከበባቸው በስተቀር እጃቸውንም ሆነ እግራቸውን አልታሰሩም ።

ሁሉም የሚጓዙት በክብት ነበር ። ነገር ግን ፣ የእስረኛ ወግ ሆኖ የውስጥ ስሜታቸውን በማንጸባረቅ ሰውነታቸው ጠውለግለግ ያለ ይመስላል ። ያሰራቸው፣ወይም የተሰበሰበው ሰውሲያሾፍባቸው መልሰው ለማሾፍ ይመስል ግንባራቸውን አኮማትረው ፣ ከንፈራቸውን እየለጠጡና እያንጋደዱ ግራና ቀኝ ሕዝቡን በክፉ ዐይን ይመለከቱታል ። ዐይን ሰውን የሚገድል ቢሆን ኖሮ ፣ በዚያ አደባባይ ስንቱ በተረፈረፈ ነበር ። በተለይ ሚስስ ሮዜንታል ደረቷን ገፋ ፣ አንገቷን ቀና አድርጋ እቀማመጧን እንደምታስተካክል አውንም-አውንም ራሷን እየሰበቀች ግራና ቀኝ ስትገላመጥ ፣ በእስረኝነት የምትጓዝ ሳይሆን ፣ በአንድ ከፍተኛ ዙፋን ላይ ተቀምጣ ሕዝቡን የምትዳኝ ታስመስለው ነበር ።

ከአጠገቡዋ ሲደርሱ ፣ የታንጉት ልብ በኃይል ይመታ ጀመር ። ዐይንዋ እንደ ችካል ፣ በተለይ ከእስተርን ላይ ተተክሎ አብሮ ተጓዘ ። እስረኞቹ ከቆሙ ችበት ፊት ለፊት ደርሰው ፣ ከእስተርን ጋር ዐይን ለዐይን ሲ.ወጋጉ ፣ ራስዋ ራስዋን እስክትታዘበው ልብዋ ስንጥቅ አለባት ። ሰላምታ በመስጠት አኳኋን አንገቱን ላመል ያህል ቀልበስ አረገ ። ዐይኑ በእርሷ ላይ ብዙ አልቆየም ነበር ። ለታንጉት ግን ዝንተ ዓለም መስሎ ተሰማት ። ከወለፉ በኋላ ስንኳ ከጀርባው በኩል ስትመለከተው ፣ ዐይኑ እንደ ተተከለባት ሆኖ ይታያት ነበር ። ምናልባት ሌላው ሰው የተለየ እስ ተያየት አላስተዋለበትም ይሆናል ። ታንጉት ግን ፣ ዕድላቸውን በቅርብ ጊዜ እንደምትጋራ በመንፈስ የነገራት ይመስል ፣ የአዘኔታ ወይም የክስ እስተያየት ያነበበችበት መሰላት ። ታንጉት ያልተገነዘበችው ከእስተርን ጋር ዐይን ለዐይን ሲገጣጠሙ ፣ ሚስስ ሮዜንታል አይታ በፈዝ ፈገግ ማለቷን ነበር ።

የታንጉት ዐይነ ሕሊና ከእስተርን ጋር አብሮ ሔዶ ስለነበር ቴዎድሮስ ከሞር አለቆቻቸው ጋር በእጠገብዋ ሲያልፉ ፣ ገብርዬ ከፈገግታ ጋር ጠቀስ ሲያደርጋት አስተውላ አላየችም ። በገመድና በጠፍር በመቀናጀ ወደም በነጠላ ታስረው በእግራቸው እየተጓዙ የመጡት ፣ በዘመቻ የተማረኩትና በሌላም ወንጀል የተያዙት ኢትዮጵያውያን እስረኞች ነበሩ ። ከእነዚህም እስረኛች መካከል ታንጉት በሚገባ ያላየችው ፣ ምናልባት ዐይንዋ ወርዶበትም ቢሆን ያላስታወሰችው አንድ ሰው ነበር ።ከሚ ሲዮናቹ ቤት አብሮ የተያዘው ደብተራ አክሊሉ ። ልም ዐይኑን አጨንቁሮ ፣ ከግር እስከ ራስዋ ከመረመራትና ከገመገማት በኋላ ፣ ንቀትም ፣ የፈዝ አዘኔታም በተቀላቀለበት ዛቻ ራሱን ላይና ታች እያወዛወዘ ዐለፋት።

የታንጉት ሐሳብ ፣ እንደ መጅ የሚመላለሰው በጥቂት ጥያቄዎች ላይ ነበር ። 'እስተርን ተናግሮባት ይሆን? ምን ምን አለችኝ ብሎ? እስከ አሁን ካልተናገረስ ወደፊት ሲያስጨንቁት ማውጣቱ ይቀራል ? ቴዎድሮስስ ምን ያደርጋት ይሆን ?' ታንጉት እነዚህን ጥያቄዎች መልሳ መልሳ በአእምሮዋ ውስጥ እያማሰለች፣እንደ ተለመደው ቴዎድሮስን ተከትላ ወደ አዳራሹ

በመግባት ፊንታ ደንገጡርዋ በለሙ በመገረም እየተኩተለጅት ሳይታ ወቃት ወደ ቤትዋ አመራች። የታወሳት ከረጅም ጊዜ በኋላ ነበር ። ግብር ከገባ በኋላ ደግሞ ፣ አዳራሽ መግባት የባሰውን መጋለጥና የቴዎድሮስን ቁጣ መጋበዝ ሆኖ ተሰማትና አንድያውን ቀረች ።

"ምን ሆነሻል ታንጉት? አሞሻል?" ሲል ገብርዬ ጠየቃት ። ከግብር ተመልሶ ፣ ቤቱ ገብቶ ከተሳሳሙ በኋላ ።

"ደኅና ነኝ !" አለች ቅዝዝ ባለ አነጋገር ።

"ዛዲያ ምነዋ ?"

"ምኑ ?"

"እዳራሽ ያልነበርሽው !"

ታንጉት መልስ ስትፈልግ ፣ "ቴዎድሮስም 'የት ሔደች?' ብሎ ስላንቺ ጠይቆ ነበር" አላት አከታትሎ ።

ለቅጽበተ ዐይን ከው አለች ። "ምነው በደኅና ?"

"እሀ ? ሲያጣሽ ጊዜ ነዋ ! ታውቂው የለ የሱን ነገር ። እንኳ ሁነኛ ቀራቢውን ሌላውንም ቢሆን ዐይኑ ያስተውላል ።"

"ዛዲያ ቴቆጣ ?" ስትል ታንጉት ጠየቀች ።

"እይ ! ድንገት 'እምሚት ይሆን ?' ብሎ ጠየቀና 'እረ እደባባይ አውን ነበረች 'ሲባል ጊዜ 'ትጠብቅሃለች ፣ ቶሎ ሒድላት' ብሎ ቀለደ ብኝና መልሶ ተወው ።"

"እንግዲያው አልተቆጣማ" ስትል መልሳ ጠየቀች ፣ በሥጋትና በተስፋ መኻል እየዋለለች ።

"ምን እስቆጣው! እንቺ ግብር ስለ ቀረብሽ? ብቻ ካለወትሮሽ ።"

"ኖማታው ጀንበር ግንባር ግንባሬን ስለ መታው ፣ በውሃ ላቀዝቅዘው ብዬ መጣሁና በኋላ ጥሼ እንዳልገባ ደግሞ" ትከሻዋን ነቅነቅ አደረገች ። "የሚጠላ ላምጣልህ ?"

"መጠየስ ጠጥቻለሁ ። ግን ያንቺን እጅ ደግሞ ናፍቄአለሁ ።"

"ፈረንጅ እስረኞችንም አመጣችኋቸው" አለች ታንጉት ጪጋን ቀምሳ ስትሰጠው ፍጋጭ ፍሊጋ ።

"ዛዲያ የት እንተዋቸው?"

"የማታግልዲቸውና አገራቸው የማይሔዱ ?"

"አይይ ! አባ ታጠት እምርሮባቸዋል ።"

"እስተዚህ መጥፎ ሥራ ሠርተዋል ?"

“ሲሰደብ ማን ደስ ይለዋል ? በተለይም እባ ታጠቅ !”

“ምን ብለው ተሳደቡ ?”

“ዘሩ እንዲህ ነው ፣ እስተዳደጉ እንዲህ ነው ፣ ዐመሉ እንዲህ ነው ፣ ብለዋል አሉ ። እኔማ በኋላ ነው የሰማሁት ።”

“እውነት ተሆነ ምን አለበት” አለች ታንጉት ፣ ደፈር ብላ ጠጁን ልትደግመው ማንቆርቆሪያውን እያመጣች ።

“ይኸን ሁሉ ምን አመጣው ? አገርን ከመምራት ችሎታዉና ከበጎ ተፈጥሮው ጋርስ ምን አገናኘው ?”

“እና በጣም ተናዱዋል ማለት ነው” አለች ታንጉት ለሦስተኛ ጊዜ ።

“በፈረንጆቹ ላይ ስንኳ አሁን ትንሽ በረድ ያለለት ይመስላል ።እንዲያውም ዛሬ አብረውን አዳራሽ ግብር እንዲበሉ ተደርጓል።ዛዲያ ምን እያለ ቀለደባቸው መሰለሽ ? የተራበውን መንገደኛ ታሪክ አወጋላቸው ። ‘ አንድ የራበው መንገደኛ ከባቄላ አዝመራ እሸት ደረሰና ባለቤቱ የግዙር መንገደኛ ብሎ ጋበዘው ። ያን መንገደኛ ከረሃቡ የተነሣ መጀመሪያ እንደ ከብት ከነቆረፈዱ ጐሰጐሰ ። ሆዱ ትንሽ ጋብ ሲል እየፈለፈለ መብላት ጀመረ ። አንድያውን ጥጋብ ሲሰማው ደግሞ የውስጡን ሽፋን እየላጠ መዘባነኑን ሲጀምር ፣ ባለቤቱ ሰውዬ ‘በል በቃህ ፣ እህል አታበላሽ’ ሲል አሰናበተው ሲል ነገራቸውና ፣ ‘እናንተም መጀመሪያ እንደ መጣችሁ ትሕትና አሳያችሁ ። ቀጥላችሁ ትንሽ ጠገብ ስትሉ በሃገሬ ጉዳይ እየገባችሁ መፈትፈት ሞከራችሁ ። አሁን ደሞ ይባስ ብላችሁ ፣ እኔን በማዋረድ ያገሬን ክብር ለመግፈፍ ታጣችሁ’ አላቸው ፣ እንደ መሣቅም እያለ ። ብቻ ፣ እኔ የምፈራው ...”

“እህ ?”

“ሰውየውን አያርገኝ ?”

“ማን ሰውዬ ?”

“አባ ታጠቅኮ በፈረንጆቹ ሳይሆን የባሰ የተናደደው ፣ እኔን ሮሚጠላ ፣ እኔን መጉዳት የፈለገ አንድ ያገሬ ክፉ ሰው መኖር አለበት ያገራቸው ብሎ ነው ። ያንን ማግኘት ነው የሚፈልገው ።”

“ዛዲያ የሚያገኘው ይመስልሃል !”

“ይዋል ይደር እንጂ የት ይቀራል ብለሽ ? አባ ታጠቅን ታውቂያ ዋለሽ ። ያሰበውን ካሳደረሰ እንደማይተው ።”

“ምን ሊያረገው ነው ቢያገኘው ?”

“አሆሆ ! ትጠይቂያለሽ ? አባ ታጠቅ ባገሩ ከብርና በናቱ አጥንት ከማለ ስታውቂው ?”

ታንጉት ፣ የጉዳዩ ከባድነት ቢታወቃትም በውሃ ጥም የሚሠቃይ መንገደኛ በጠራ የበጋ ወራት ድንገት ዝናም ይጥላል ፣ ወይም ጭው ባለ ደረቅ በረሃ ምንጭ ይገኛል ፣ ብሎ የእባቢውን እውነት በተስፋ እንደሚሽ ፍን ሁሉ ከጭንቀቷ የተነሣ፣ የጠበቀችው መልስ ጭንቀቷን የሚያቃልል ዐይነት ነበር ። የገብርዬ አንጋገር ግን፣ በጭንቀቷ ላይ የባሰውን በድንጋጤ መታት ። ሳይታወቃት የቴዎድሮስን ቅጣት የምትከላከል ይመስል ሰውነቷ ሲንዝር፣የያዘችው ማንቆርቆሪያ ከእጅዋ ወድቆ ሲደፋ የተረጫጨው ጠጅ የገብርዬን ልብስ አርከፈከፈው ።

“ውይ !” አለች በድንጋጤዋ ባንና እንደገና በመደንገጥ ። ገብርዬ በበኩሉ ያልተለመደ ተግባርዋ አስደንግጦት ኩታውን እያራገፈ ብድግ ብሎ በሁለት ክንድዋን ደግፍ አደረጋት ። “ምን ሆንሽብኝ ዛሬ ታንጉት?” ታንጉት ልጅ ለመውለድ ባላት ብርቱ ጉጉት ተዘሀም ተዘያሞ ስትል ያልሆነ መድኃኒት ትወስዳለች የሚል ሥጋት አለው ።

“ደኅና ነኝ ። እንዳልኩህ ፀሐይ ነው” አለች በእጅዋ ግንባርዋን እያሻሸች ።

“ተይ ! ሌላ እንዳይሆን” አላት ዘለፍለፍ ያለ ሰውነቷን ደግፎ ወደ አልጋው እየወሰዳት ።

“ደሞ ምን በሽታ አለብኝ ልትል ነው !” አለች ከድንጋጤዋ መለስ ብላ በቀልድ ቁጣ ዐይነት ።

“ኧረ ! ኧረ ! አንቺ ጤና ሁኝልኝ እንጂ ምን ገዶኝ ?” ጨርቅ ቢጤ በውሃ ነክሮ ከግንባርዋ ላይ አደረገላት ።

“ደኅና ነኝ እኮ አልኩህ ! የፀሐዩ ትኩሳት ነው ። አሁን ይሻለኛል ” አለች ታንጉት ከራስዋ አጉልነት ዐልፎ ገብርዬን ሐሳብ ላይ በመጣልዋ እያዘነች አቃልላ በመናገር ።

ገብርዬ ግን ፣ ታንጉት ደኅና እንቅልፍ የወሰዳት ከመሰለው በኋላ ከቤቱ ታዛ ተቀምጦ ማሰቡ አልቀረም ።

ገና በቋራ በረሃ ሳሉ ፣ ቴዎድሮስ ያሳየው ሕልም፣ ያመለከተው ዓላማ የፈነጠቀበት ተስፋ ፣ ያሳደረበት እምነት እያማረ ፣ እየሠመረ ሲመጣ ቆይቶ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቴዎድሮስን እንዳስከፋውና እንዳሳዘነው ሁሉ፣ገብርዬን ም ግር እያሰኘው ሔዷል ። በየጊዜው ያልታሰበ አዲስ ሁናቴ ይፈጠራል ። የሰዎች ዓመል እንደዚሁ እየተለዋወጠ አስችግሯል። የታመነው ይከዳል ። የተሾመው ፣ ክብር ማዕረግ የተሰጠው ይሸፍታል። ብርቱ ባላጋራ የነበሩት ፣ ተመሳጥረው ፣ ተሻርከው ይገኛሉ ። ወዳጆች በደንገት ይጣላሉ ። የታሰበው የማይሳካበት ፣ ያልታሰበው የሚሆንበት ጊዜ ሆኗል ። ይህ ጠቅላላ ግልብጥብጡሽ ፣ ከአሁኑ ከታንጉት ሁናቴ

ጋር ምን እንደሚያገናኘው ገብርዬ በግልጽ ባይታየውም፣ እንዲያውም በያፈናው አውን ምን እንደሚያሳስበው ለይቶ ሊያውቀው ባይችልም እንዲሁ ብቻ ሐሳብ ያዘው ።

ሐሳቡ እንዲቀልለው ወይም ሐሳቡን እያብላላ ወደ መስክ ሲናፈስ ቆይቶ፣ሲመለስ ግን ታንጉት እንደ ወትሮዋ ነቃ ብላ፣ የራቱ ድግስ ቢቱን ሲያውደው አገኘ ።

ደስ አለው ። ራት ተበልቶ የመኝታ ሰዓት እስኪደርስ ጊዜው ተጉ ተተበት ።

—2—

ገብርዬ፣ ወደ መጀመሪያ ገደማ ላይ እንደ መገረም አለው ። ገበታ ተንሥቶ የምሽቱ ጣጣና ጉዳይ አልቆ ፣ ሠሪተኞች ወደየማደሪያቸው ተሠማርተው ገብርዬና ታንጉት በእልፍኝ ውስጥ ብቻቸውን ከትልቁ የጠፍር አልጋቸው ላይ ተኝተው ነበር ። ዕንቅልፍ ገና አልወሰዳቸውም። በተለይ ለገብርዬ የዕንቅልፍ ሰዓት አልነበረም ። የበላውና የጠጣው ሰውነቱን ተስማምቶታል ። ስሜቱን አሙቆታል ። በዚህ ላይ የብዙ ወራት ናፍቆቱ አለ።ገብርዬ ዘመቻ ሲሔድ እንደ ቆራቢ የተፈጥሮ ፍላጉቱ አክሩይ እንደሆነ ባይመሰስም ፣ከታንጉት ጋር እስኪገናኝ ሁልጊዜ እንደጓጓ ነው ። እንደ አዲስ ፍቅረኛ ገላዋን ከዕቅፉ ውስጥ ለማስገባት ይቸኩላል።ወዝዋን ይጠግኖል። እርሷም እንደዚሁ ነው የምትጠብቀውና የምትቀበለው። አሁንም በዚያው ዐይነት ስሜት ፣ ያሻሻታል ። ይዳብ ሳታል ። ሳም ፣ ዕቅፍ ፣ ሞምቅ ያደርጋታል ። ነገር ግን ታንጉት የፍላ ጉቱ ፍጻሚ፣ የስሜቱ አስተናጋጅ እንጂ እንደ ወትሮው አኩል ተካፋይ እለመሆንዋ ያስታውት ነበር ። ፍም ሆኖ ሲቀርባት ነበልባል ሆና ትቀ በለው የነበረውን ያህል ፣ አሁን ታሣሽር ገላ ብቻ ሆነችበት ።

“ምን ሆነሻል ታንጉት” ሲል ጠየቃት ፣ የስሜት እሳቷን ለማቀ ጣጠል በሁለመናው ሞክሮ ሲያቅተው ፣ስሜቱ ድንገት እንደ መቀዝ ቀዝ ፣ ሰውነቱ እንደ መሸማቀቅ እያለበት ።

“ምን አጠፋሁ” ታንጉት ቅር ልታሰኘው አስባ አልነበረም። ራስ ዋም ቢሆን መደሰቱን አትጠላውም ነበር ። ነገር ግን፣ ‘ልብ ካላየ ዐይን አያይም’ እንዲሉ፣ ሐሳብዋ በሞንቀት የተንጠለጠለው ወደፊት ከሚመ ጪት ዕድል ላይ ስለሆነ፣ ለፍቅር ጨዋታ ስሜቷ ሊነሣሣ አልቻለም ። ሁናቴዋ እንደ ፈትል ፣ እንደ ስፌት ፣ እንደ ምግብ ዝግጅት የማይቀር ተግባር የማከናወን ዐይነት ነበር ። ገብርዬ መገንዘብ አላቃተውም ።

“ተለወጥሽብኝ ! ” አላት ።

“ምን ሁኝ ?” ስታኝጋገረው ስንኳ አእምሮዋ የሚያውጠነጥነው ሌላውን ጉዳይ ነበር ።

“እኔ እንጃ ! በጣም ቀዘቀዝሽብኝ !” አውንም በዳበሳ ሊያሟሙቃት ሞከረ ።

“ትኩሳታሟን አግኝተህ ይሆናል !” ታንጉት ሐሳብዋ በሞንቀ ቅና በንዴት መካከል ተወጥሮ ሰለ ነበር፣ የተናገረችው ሳታስበው በድ ንገት ነበር ።

“ምን ?” እንደዚህ ስትናገረው የመጀመሪያ ጊዜ ነበር ፣ ገብርዬም ንዴት ብልጭ አለበት ።

መልስ አልሰጠችውም ።

“እህ !ከአሀያ ጋር የዋለች ጊደር ፈስ ተሞራ ትመጣለች እንደ ሚባለው ፣ከመንደር አውደልዳይና ጋለሞታ ጋር እየዋልሽ ዐመል አመ ጣሽ !”

ይህንን ሁሉ ጣጣ ያመጣባት ገብርዬ ይመስል ፣ ሞንቀቷ ወደ ንዴት ተለወጠ ። “ጋለሞታ ? እንዲያ እንጂ ። ይኸው ነበር የቀረኝ ! ” ከተ ጋደመችበት ወደዳር ፈቀቅ አለች ።

“እንቺው ትያለሽ ፣ እኔ አልወጣኝም !” ገብርዬ መገረሙና መና ደዱ ባሰበት ።

“እኮ እኔ ጋለሞታ ?” እንደ ግልቀስ ቃጣት ።

ገብርዬ ፕርሱን አፋዉና መልስ ሳይሰጥ ዝም አለ ።

“እህ ? ጋለሞታ ?” እርሷም በንዴት ፕርሷን አፋጨች ።

“አሁንስ እንዲያውም ምላስሽ ከጋለሞታም ከረፋ !” አለ ገብርዬ ከተጋደመበት በመወራጨት ዐይነት እንደ መቀመጥ እያለ ።

“ከርፋታም ! እኔ ነኝ ከርፋታም ! ”

ገብርዬ፣ በጥፊ ሊመታት ከቃጣ በኋላ እጁን ሰብሰብ አደረገ። “ወይ ጀሮሽ ደንቁሯል ፣ ወይ ጠበል ሒጅ !”

ታንጉት፣በንገርዋ ሁሉ ልክ እንዳልሆነች በእንድ በኩል ይሰማታል። ሁለቱም በከንዳቸው ላይ ተደግፈው ቁና በግለት ለእንዳናፍታ ተፋጠው።

ቢተያዩ ገብርዬ ምንም እንዳልበደላት ይታወቃታል ። ግን የምት ናገረውን መቋጣጠር አልቻለችም ። “እና እኔ ጋለሞታ ? እኔ ደንቆሮ !” አለች በጩኸት ።

“ታልሽ አም ! ነሽ !” አላት ገብርዬ በብሽቀት ።

"አዎ ነሽ !?" ታንጉት መልሶ እንዲያስተባብልላት የፈለገች መሰለች ። የሚመልስላት ግራ ገብቶት ተወው ።

" 'አቶ ጅቦ ሳታመሃኝ ብላኝ' አሉ። ተዚህ ሁሉ ሒጂልኝ።በቃሽኝ ብትል አይቀልም ?" አለችው ታንጉት ጠብ የመፈለግዋ ስሜት እየ ገፋት ። "ግድ ያለህ የለ ?"

"አረ በስማም በይ ሴትዮ !"

"ሴትዮ አትበለኝ ! ስም አለኝ ! ወይስ ስሜንም አስጠፋህ ?"

"እነማን ?" አለ በመገረም ዐይነት ።

"እነማን ብዬ ስንቱን ልቁጠርልህ ? በየምትዞርበት የምትገልበውን ቀሚስ ራስህ ነህ የምታውቀው !!"

ገብርዬ፣ በንዴቱ ላይ ጣቅ መጣበትና ከት አለ ። ' አዲስ ሁናቴ ያሳ የችው በቅናት ምክንያት ከሆነ መቸስ ምን ይደረጋል ? እንዳመጣጡ መቻል ነው እንጂ!'የሚል ሐሳብ መጣበት ። ከዚያ በፊትም ዐልፎ ዐልፎ የቅናት እሳት እየተጫረባት የተቆጣችበት ፣ የተብሰከሰከችበት ጊዜ አለ ። ታዲያ የፍቅር ጨዋታው ፣ ዕቅፉቱ ፣ ማባበሉ ፣ ዳበሳው ወዲያው ይመ ልሳት ነበር ። በአንጋገርዋም እንደዚህ ሆና አታውቅም ነበር ።

'ከመካንነቷ ጋር ዕድሜዋ እየጨመረ፣ ገላዋ እየላላ ሲሔድ የበለጠ እየተሰግት ይሆን ? ወይስ የተገላቢጦሽ የራስዋን ጉድ ለመሸፈን ሰበብ መፈለጓ ይሆን ? ራሱ ከስንት አንድ ጊዜ በርሷ ላይ እንደሚሔድ ምናል ባት ታንጉት በደንገት ተወሳልታ ሊሆን ይችላል ። ግን ለብዙ ዓመታት በሚያውቀው ጠባይዋ ፣ ታንጉት እስከዚህ ትከፋለች ፣ ወይም ይህንን የመሰለ ተንኰል ታስባለች' ብሎ መገመት አስቸገረው ።

"ሲሉ ሰምታ ፣ ዶሮ ሞተች ከጢስ ገብታ አሉ" አለ ገብርዬ እንደ ዋዛ ።

"እንዴት ? ለመግ ለማዕረግ የማትበቂ ምናምንቴ ነሽ ማለትህ ነው?" ስትል እንደገና ተወራጨች ፣ በስሜቷ ክቴዎድሮስ ጋር የተፋጠጠች ይመስል ።

"የለም ። ዘመቻ ባደክመው እንደኔ ባለ ሽማግሌ፣ ምን ይቀናል ማለቴ ነው" ሲል መለሰላት ነገሩን ለማብረድ።"እጉል ላለመጠራጠር ደግሞ ቆርቦ ዕርፍ ማለት" ሲል አከለ ።

"እንዲያ ነው !"አለች ታንጉት በማሽሚጠጥ ።

"ወትሮውንም ቢሆን እኔ እምቢ አላልኩ ።"

"እኔ ነኛ ዛዲያ ?"

"እምቢ ባትይም ፣ ፈቃደኛነትሽን ወይሞ መፈለግሽን አላሳየ ሽም ነበር ።"

"እህህ ! " አለች ታንጉት በምጸት እነጋገር ። " የለው ኃጢያትና ኩነኔ ማን አክብጅ አለኝና !"- አንተም ቴዎድሮስም አንድ ናችሁ " አለች በሆድዋ ።

"እንዴት ?"

"ቆረቡ የተባሉትን ባሉች ጉድ እያየነው ።"

"እነማንን ልትይ ነው?" ገብርዬ ቁጣውን ለቅጽበት እንደ መር ሳት ብሎ በጓደኞቹ ላይ የሚወራውን ሐሜት ለማወቅ ፈለገ ።

"ምን ስም አስቈጠረኝ !"

"ውሸት !"

"ምን አስዋሸኝ ! ዙፋን መጋራት የቀራቸው የደብረ ታቦር ቅም ጦች ይመስከሩታ !" አለች ፍርጥም አድርጋ ፍርሃቷን በዚህ በቀኗ የም ትወጣው ይመስል ።

"ምን ?" አለ ገብርዬ እንደገና በጨኸት። የነገሩዋ ዳር ዳርታ ወዲ ያው ታይቶታል ። "አባ ታጠቅን ማለትሽ ነው ?" አለ ጥርሱን ቅርጭም አድርጎ ።

"አልወጣኝም ።"

"ነው እንጂ ! የተንኮለኛው ፣ የነገረኛው ምላስ ሁሉ የተነሣበት በሱ ላይ ነው ።"

"እና እኔ ተንኮለኛ !" አለች ታንጉት ቀበል አድርጋ ።

"የሚሉትን ሰምተሽ ይሆናል ማለቴ እንጂ አንቺን አላልኩም ። እሱስ ቢሆን በሰው ሚስት ላይ አልተገኘ ! ደግሞም ተዋበች ተሞተች በኋላ ቁርባኑን አፈረሰ አይባልም ። ተጥሩ ወርቅ እስታልቆረበ ድረስ ። ምኑ ተመኾቶትስ ይቁረብ ?"

"ወትሮም እንዳይሆን እንዳይሆን ነው፣ የተፈጥሮ ዓመል ሰበብ ነው የሚፈልገው" ታንጉት፣የድፍረት ድንበር መዝለልዋ ገና ተናግራ ላት ጨርስ ነበር የታወቃት ። ግን እንደ እሳት እራት ጭልጥ ብላ ገባችበት ።

የድፍረት አነጋገርዋ የሚያስከትለውን ውጤት ለማሰላሰል ገብርዬ ፋታ አልሰጣትም ። በጦር እንደ ተወጋ ያህል "እ! "ብሎ ሲጮህና በቃ ሪያ ጥፊ ሲለጋት አንድ ሆነ ። ከድንጋጤዋ የተነሣ አልጮኽችም ። ድርቅ እንዳለች ቀረች ። ገብርዬም ቢሆን መዳፉ ከጉንጭዋ ጋር እንደ ተላተመ፣ ድንገት እሳት ውስጥ የገባ ያህል ድንጋጤ መላ ሰውነቱን ነዘ ረው ።

ከዚያ በፊትም ቢሆን ስታጠፋ ወይም ስታናድደው በምር ቁጥ ታታል ። እንደ ልጅ በቁንጥጫና በለበቅ ቢጤ እንጂ የቃሪያ ጥፊ ቀርቶ ደንደን ያለ በትር አሳርፎባት አያውቅም ነበር ።

ታንጉት ፣ በእንዳች የስሜት እንቆቅልሽ አዲስ ዐይነት የድፍረት አነጋገር እንዳመጣች ሁሉ፣ የገብርዬም የቅጣት ልማዱ የተለወጠበት ሳያስበው ነበር ። ወዲያው ጥፊው ባረፈበት በኩል በአፍንጫዋና በከንፈርዋ መጋጠሚያ ደም ሲመነጭ ማየት አላሰችለው አለና፣ ፈትቶ ከራስጌው አጠገብ አስቀምጦት የነበረውን ድጉን እንድትጠርግበት ሰጥቷት ከቤት ወጣ ። ከታዛው ሥር የቤቱን ግድግዳ ተደግፎ ሐሳቡ በንዴትና በጸጸት መካከል እየተንገላታ በዚያ ዐደረ ።

—3—

ወደ ማታ ገደማ ፣ ጥጥ ስታባዝት የነበረችው የታንጉት ደንገጡር እየተቻኮለች ገባችና፣ ‘‘መጡ !መጡ’’ አለች ።

‘‘እነማን ?’’ ስትል ታንጉት በቅፊታ ጠየቀች ።

እንግዳ እንዲመጣባት ያልፈለገችበት ምክንያትን በራት።ጪት ገብርዬ ውጭ ዐድሮ በባዶ አፉ ወደ አደባባይ እንደ ሔደ ነበር ፣ ትንሽ በተረጋጋ ሙንፈስ ማታ የሠራችው ጥፋት እየታወቃት የሔደው ። ለፍቅር ጨዋታው ሰውነቷ ሊሟሟቅላት ባይችል በነበረባት ሐሳብ ሊፈረድባት አይገባም ። ስሜቷ አልታዘዝ ካላት ምንም ማድረግ አትችልም ነበር ። ግን ገብርዬን በነገር መጠዝጠዝዋ ምን ይባላል ? ገብርዬ አልበደላትም ። የጭንቀቷ ምንጭ ሌላ ነው ። ጉዳዩን ጨርሶ በማያውቀውና በማያገባው በገብርዬ ላይ ብስጭትዋን መወጣት ‘አህያውን ፈርቶ መደላድሉን’ እንደሚባለው ዐይነት መሆኑ ነው ። ችግሩ ፣ አግባብ አለመሆኑ በወቅቱ አልታያትም ነበር ። ለጊዜው የተሰማት ፣ በቅርብ ባገኘችው በገብርዬ ላይ ብስጭትዋን ለመወጣት መሞከርዋ ነበር ።

በበነጋው፣ ወደ ኋላ ተመልሳ ጎዘንና ጸጸት ተሰማትና የፈሰሰ ውሃ እንደማይታፈስ ሁሉ ፣ እንደገና ወደ ሆድዋ ልትውጠው ባትችልም፣ ገብርዬ ማምሻውን ሲመጣ፣ ማታ በአነጋገርም ላደረገችው ጥፋት እንዳይቀየማት ለመለመን ፣ ስሜቷ በፈቀደላት መጠንም በፍቅር ጨዋታ ለማስደሰት ወስና ውላ ነበር ።

መካሻ ይሆን መስሏትም የሚወደውን የቋንጣ ወጥ ራስዋ በጥን ቃቂ ክሽን አድርጋ ሠርታለች ። የሚያመሻሽ እንግዳ ይዞ ከመጣ ግን ለምትፈልገው የርጋታና የግል ጭውውት ሁናቴው ላያመቻት ነው ። ‘የዛሬን እንግዳ ባይጐትትብኝ ምን ነበረበት’ እያለች በሆድዋ አጉመተመተች ።

‘አባ ታጠቅና ገብርዬ ናቸዋ !’ በማለት ደንገጡራዋ ስትመልስላት፣ታንጉት ድንገት በመብረቅ እንደ ተመታ ነገር ድርቅ አለች። ልብዋ የተተረተረ መሰላት ። ቴዎድሮስ ፣ ከንብርዬም ሆነ ከሌሎች ባለማሎቻቸው ቤት ወልፎ ወልፎ መሔዳቸው የተለመደ ቢሆንም፣ አስቀድሞያሳውቃሉ ። ለባለሟሎቻቸው ‘ነገ ታንተ ቤት ነው ምሳዬ’ ሲሉ ይናገራሉ ። ሚስቶቻቸውን ‘እስቲ ዛሬ ራቴን አብይኝ ?’ ሲሉ በቀልድ መልክ ይጠይቃሉ ። ወይም ደግሞ ‘ ራቴን የምበላው ተናንተ ዘንዳ ነው ’ በማለት ሰው ይልካሉ ።

ከባለሟሎቻቸው ቤት ሔደው መጋበዝ የሚፈልጉት ደስ ባላቸው፣ ጥቂት መዝናናት በፈለጉ ጊዜ ነው ። በእንደዚህ ያለ ጊዜ ጨዋታቸውና ቀልዳቸው ሲያስደስት ሌላ ነው ።

አሁን ድንገት መምጣታቸው ግን፣ለፈራችው ነገር መሆን አለበት ። ቁጣቸው እንደ ወላፈን ሲጋረፍ ተሰማት ። ለሚወርድባት መዓት እንደ መዘጋጀት ዐይነት ገላዋን ኩምትር ፣ ጥርሷን ቅርጭም አደረገች ። በጭንቀት ብዙ ጊዜ ከማማጡ እንደዚህ በቶሎ ለቁርጠኛው መቅረብ ፣ እንደ መገላገል ሳይሆንላት ይሩራል ! ታንጉት ዐይንዋን ከደን አድርጋ በአፍንጫዋ በሰፊው ተነፈሰች ። ‘‘እረ ድግስም አብሮ አለ !’’ የሚለው የደንገጡራዋ ድምፅ የተሰማት እንደ ስመመን በሩቁ ነበር ።

‘‘ምን ?’’ ስትል ታንጉት ጠየቀች፣ድንገት በመባነን ዐይነት ።

‘‘አዎ ! ሞሶብም ፣ ገምቦም የተሸከሙ ሰዎች ይታዩኛል ።’’

ታንጉት፣ ራስዋው ለማረጋገጥ ወደ በራፍ ወጣችና ተመለከተች ። መቅመጫዎቹን በጥድፊያ ስታሰናዳ አእምሮዋ ልዩ ልዩ መላ ምቶች ያተራምስ ገባ ። የትናንት ማታውን ገብርዬ ነግሮት፣ ‘እንቺም መጥፎ አትናገሪ ። አንተም አትምታት’ ብሎ ሊያስታርቋን ይሆን ? ዕድሜ ልኩን ደብቆት የኖረውን ምሥጢር ለባለሟሎቹ በይፋ ሊገልጸው ይሆን፣ ባለሟሎቹ ካወቁትማ ፣ ወዲያው ለድፍን ኢትዮጵያ ይደርሳል ። ከዚያ በኋላ ታንጉት በአዲስ ዐይን የምትታይ ትሆናለች ። ዛሬያ ይህስ መሆኑ ከሌላው ሥጋቷ ያድናታል ? የቴዎድሮስን ጠባይ ስለምታውቀው ያጠራጥራል ። ቴዎድሮስ ካልመሰለው ለማንም አይመለስም ። የሚያድናት ከሆነ የገብርዬ ሚሽት መሆንዋ ብቻ ይበቃት ነበር። ታንጉት ስለ አመጣጣቸው ደግ ደጉን ለማሰብ ትፈልግ እንጂ ከሥጋቱም አልወጣችም ።

ቴዎድሮስ እንደሆኑ አንዳንድ ጊዜ የሚሠሩት ሁሉ ፈጽሞ ያልታሰበና የማይመስል ነገር ነው ። ለምሳሌ ፣ አንድ ጊዜ ጥቂት ወስላቶች ተሰባስበውና ከፊታቸው ቀርበው እጅ በመንሣት ‘‘ሁሉም፣ በየሙያው እየገባ ይኑር ብለው ዐውጀዋልና እኛም በሙያችን እንድንተዳደር’ ብለው ይለምናሉ ። ‘ ሙያችሁ ምንድን ነው ?’ ብለው ይጠይቋቸዋል ። ‘ሙያችንማ ፣ ቤት መሰርሰር ጐተራ መስበር ፣ ከብት መንዳት ነበር ። ሌላ ሙያ እናውቅም’ ሲሉ ይመልሱላቸዋል ። ቴዎድሮስም ፣ የሆዳች

ውን በሆዳቸው ይዘው ፣ ፈገግታ በግላየት ፣ ‘ መልካም ነው ። ግን እና ንተ ብቻ አትመስሉኝም በዚህ ሙያ የምትኖሩት። አነሳችሁብኝ። ስለዚህ ሁላችሁም ተሰባስባችሁ ብትመጡ መልካም ነው’’ በማለት እንዲመለሱ የሚያደርግ የጉረሻ መላሻ አቅምሰው ያሰናብቷቸዋል ። እውነት መስሏ ቸው ፣ ተፈላልገው በብዛት ተንጋግተው ሲመጡላቸው ግን ዋጋቸውን ሰጧቸው ። በእንጻሩ ደግሞ ፣ በምንትዋብ ላይ የፈረዱትን ታንጉት ታው ቃለች። ግንኙቷን በኋላ ታንጉት እንዳጣራችው የደጃች ጓሉ ልጅ የሆነ ችው ምንትዋብ በልቅሶ ላይ ያወረደችውን ዘለፋ ፣ ዐይንዋን ሳታሽ እን ደገና በቴዎድሮስ ፊት ደግማው ፣ ምሕረት ተደርጎላት ፣ ቀለብ ተሠፍ ሮላት ፣ ቀለቧን እየበላች አውንም እንደ ጥላ በመከተል የስድብና የዘለፋ ግጥሟን እንዳወረደችባቸው ትገኛለች። እስከ አሁን ዝንቧን እሽ አልተ ባለችም ።

የታንጉት ጉዳይ ከምንትዋብ የተሰዬ መሆኑ ይታወቃታል ። ‘ዛዲያ ምንትዋብ የተበደለች መሆንዋ ታውቆላት ፣ ከሙሉ ምሕረት ጋር ፋለቀ እንደ ተሰፈረላት ሁሉ፣ እሷን ደግሞ የተገላቢጦሽ እንደ ፍታት፣እንደ ተዝ ካር በድግስ ሊፈርድባት፣ ሊቀጣት እንደ ሆነስ ግን ያውቃል ? እንግዲህ ያበጠው ይፈንዳ !’ አለች ታንጉት በሆድዋ ጥርሷን ቅርጭም እንዳደ ረገች ።

የቴዎድሮስ ድንገተኛ ጉብኝት ገብርዬንም በአእምሮው ውስጥ ጥያቄ አሳድሮበት ነበር።‘ትናንት ማታ በጥፊ ክፉኛ እንደ መታት ሰምቶ ሁናቴዋን ለማወቅ ይሆን ? ቴዎድሮስ በየቦታው የሚሆኑትን ዝርዝር ነገሮች ሁሉ የሚያገኝበት መንገድ አለው ። ደንገጡሩዋም ቢሆን ለአ መቤትዋ ማድላት አይቀርምና ነገሩ እንዲደርስ አድርጋ ሊሆን ይችላል።’ ብቻ ‘ገብርዬ ዛሬ ካንተ ጉጀ ነው የምናመሸው’ ሲሉት የቁጣ ሁናቴ አልታየባቸውም ነበርና ብዙም አልተጨነቀም ።

የቴዎድሮስ ምክንያት ግን ፣ ከዚህ ሁሉ ጨርሶ የተለየ ነበር ። እንዲያውም አንዳች ልዩ ምክንያት አልነበራቸውም ። በአቅራቢያ ከሆኑ ውሎ ማደር አያሰችላቸውምና ደብረ ታቦር እንደገቡ ጧት ፣ ወደ ጋፋት ገሥግሠው እንደ ሐዱ ያጋጠማቸው የሥራ ውጤት ለብዙ ወራት ተጭኖ ዋቸው የቆየውን የቅሬታ ፣ የጎዘንና የብስጭት ሸክም በመጠኑ የሚ ያቃልል ሆኖ አገኙት ። የብረት ማቅለጫ ጎንዳዎች በየመጠናቸው ተሠርተው አልቀው እንዳንዶቹ እየተቀለጠባቸው ነው ። የብረት ዐፈሩ ከሩቅና ከቅርብ እየተፈለገ መጥቶ በዐይነት በዐይነቱ ተቀምጧል ። የቅ ርጽ ማውጫው የሸክላ ዐፈር እንደዚሁ በዐይነት በዐይነቱ ተቆልሏል ። የመጀመሪያው ዋና ችግር ፣ የቀለጠውን ብረት ሳይፈረካከስ መያዝ የሚችል ቅርጽ ማውጫ ሸክላ ማግኘቱ ነበር ። በአገር የታወቁ ሸክላ ሠሪዎች ዕርዳታ ጭምር ተጠይቆ ከብዙ ጥረት በኋላ ተሳክ ቶላቸው፣ መድፍ የሚመሳስሉ ሁለት መጠነኛ ቅርጾች ለማውጣት ችለ

ዋል ። መተኩስ አለመተኩሳቸው አልተሞከረም ። ግን አስቸጋሪው ሥራ ዋናውን ቅርጽ ማውጣቱ እንጂ ፣ ባሩዱን፣መለኩሻውን ፣ ተስፈንጣሪውን እርሳስ ማኟላት የሚያቅት እንደማይሆን የጋፋት ሰዎች ለቴዎድሮስ ነገረዋቸዋል ። አሁንም የአንድ መጠነኛ መድፍ ግውጫ በመሥራት ላይ ነበሩ ።

ቴዎድሮስ፣ አነስተኞቹን የመድፍ ምስል ቅርጾች እንደ ሕፃን ጉንጭ በጉጉትና በስስት ዐይነት ደባበሷቸው።የብረቱን ዐፈር እንደሚያስጐሠ ውብ እህል ደግመው ደጋግመው በመዝገን ፣ ማየት ብቻ ሳይሆን እንደግ ሸተት አደረጉት ። ከዚያም ፣ በመለበድና በመተኮስ ላይ ያለውን ትልቁን ቅርጽ ማውጫ ፣ የአናጢውን ፣ የሽመናውን ፣ የማረሻ ፣ የግጭድ ፣ የመጥ ረቢያና የሌላም የብረታ ብረት መሥሪያውን ክፍል እየተዘዋወሩ ሲመ ለከቱ ፣ መንፈሳቸው እንደገና ተስፋ ዘራ ። በሰቀቀን ጠውልጎ የነ በረው ስሜታቸው እንደ መለምለም አለ። ግን ያውቃል ? ዕድሜም ፣ ሰላማዊ ፋታም ካገኙ ያለሙት ሁሉ እንደ ጨለመባቸው፣ ያሰቡት ሁሉ እንደ ራቀባቸው አይቀር ይሆናል። ከሌሊት በኋላ ንጋት ይከተላል ። ፈተና እንደ ምንም ይታለፋል ፣ እስኪያልፍ ግን ያለፋል ፣ ያማቅቃል ።

“ ወትሮውንም ቢሆን በተቻለ መጠን ትረዱኛላችሁ ብዬ እምነት የጣልኩባችሁ ቢሆንም” አሉ ቴዎድሮስ ጉብኝቱን ከጨረሱ በኋላ ስሜት ሰበርበር ባደረገው ድምፅ ፣ “ሠርታችሁ የቆያችሁት እጅግ እርጎ ነው ያስደሰተኝ ። እነዚያ የፈላሻ ሚስዮኖችማ የሠሩኝን ሰምታ ችሁ ይሆናል ። የጃቸውን ይስጣቸው እንጂ እኔ ሌላ ምን እላለሁ መቸስ! ተልጣ ለናንተም ደግሞ ውለታችሁን በገንዘብ ከፍዬ አልጨርስ ውም ። ለሙነተኛ ውለታ እሱ ምንድን ነው ? እላቂ ጠፊ ። እና አሁንም የሆነ እንደሆነ የምከፍላችሁ ዋናው ዋጋችሁ የልቤን ፍቅር ነው ። በተረፈ ግን ፣ የሚያስፈልጋችሁ ነገር ቢኖር እንዲረዳችሁ ለማለት ያህል—” ብለው እጃቸውን እንደ መዘርጋት ሲያደርጉ ፣ አብሮዋቸው የሚዘዋወረው ግምጃ ቤታቸው ጠገራ ብር የተቋጠረበትን ከረጢት እቀረበላቸው ። ሳይቈጥሩ እጃቸው እንደ ገመተ“ለጋፋት ልጆቻቸው” አደሉ ።

እያንዳንዱ ምናልባት ከሌላው የበለጠ ደርሶት ይሆናል ። ግን ቴዎድሮስ አቆነጣጠራቸውንና አሰጣጣቸውን እንደ ዕጣ ስላስመሰ ሉት ፣ ሁሉም በደስታ ፈካ እንጂ ቅር የተሰኘ አልነበረም ።“የጋፋት ልጆች” ሕፃናት ሳይቀር እንዳንድ ጠገራ ብር ተሰጣቸው ።

በዚህ ዐይነት የረካ መንፈስ ወደ ደብረ ታቦር ሲመለሱ ነበር ፣ ከገብርዬ ቤት የማምሽት ሐሳብ የመጣባቸው ። ቤት ሲገቡ ጥሩ ወርቅ በተለመደ ሞፍግግ ሁናቴዋ ደኅና ፈካ ያለ ስሜታቸውን መልሳ ታጠመልግባቸው ይሆናል ። ወደ አንደኛዋ ዕቁባታቸው መሔዱንም አልወደዱትም ። በጋሩት ያዩትን ተስፋ ማርከስ መስሎ ተሰማቸው ። ግድ ሆኖ ባቸው በግላቸው ለግላቸው የሚፈጽሙትን ተግባርነትልት ለሆነው ዓላማቸው ማሳረጊያ ግድረግ ቀፈፋቸው ።

በዚህ ላይ እንዳስተዋሉት የገብርዬ ሁናቴ ደስ አላላቸውም ነበር። የራሳቸው ስሜት በእርካታ የፈካውን ያህል ፣ ብዙም ዕንቅልፍ ሳይተኛ ከቤቱ ውጭ ያደረው የገብርዬ ፊት ፣ ሐሳብ ወይም ትካዜ ቢጤ ያጠላበት ይመስላል ። ሲያጫውቱት ቢያመሹ መልካም ነው ። ከጕልማሳነት እስከ ሙሉ ዕድሜ ፣ በደስታ ፣ በመከራ ፣ በድል ፣ በፈተና ከታጉጉትና ከገብርዬ የቀረበ ማንስ አላቸው ?

“እንጓች ፣ እንቺ ጉራዲቴ ፣ እንዴት ሰነበትሽ ? አሁንማ ኩራ ኩራ አልሽ መሰለኝ ። እልፍኝ አልወጣም ማለትሽ ነው ?” አሏት ፣ ታንጉት ጉልበታቸውን እንደ ሳመች ቀና አድርገው ሁለት ጉንጩዋን እገላብጠው እየሳሙ ።

ለደግ መምጣታቸውን ገና ከሩቁ በፈገግታቸው ገምታ ነበር ።አሁን አረጋገጠች ። ከልጅነቷ ጀምሮ ፣ “ጉራዲቴ ! የኔ ጉራዲት” እያሉ የሚጠሩዋት በተዝናኑ ጊዜ ነው ፣ ሊያቆላምጡዋት ሲፈልጉ ። እስከዚህ ጉራዳም ባትሆን ለቀልድ ፣ ለቁልምጫ ያወጡላት ስም ስለሆነ ትወደዋለች ።

“እግዚር ይመስገን አባ ታጠቅ ። እንተስ ደኅና ነህ ?” አለች ታንጉት፣ጭንቀቷ ድንገት ሲለቃት ገጿ ላይ ፈገግታ ተተክቶበት። ልጅ ሆናማ ጉራዲት ብለው ሲጠሩዋት የኩረኩሩዋት ይመስል ሣቅ ይመጣባት ነበር ።

“እንደ ጠየቅሽኝ !” አሉ በቀልድ ኩርፊያ ። “ለመሆኑ ትናንትየት ጠፉሽ ?”

“የት ጠፋሁ አባ ታጠቅ ?” ስትል ተዝናንታ መልሳ ጠየቀች ።

“ገበታ ላይ ሞች ነበርሽ ?”

“አዎ ! ወደ ቤት መጣሁ።”

“አሃ ! ከሌሎች ሴቶች ጋር ባንድ መሶብ ለመቀመጥ የጉራዳ ኩራት ተሰማሽ ? ቆንጆ አገኘሁ ብለህ እንተ ትሆናለህ የምታኩራራት” አሉት ገብርዬን ።

“እረ እኔስ ፀሐይ ራሴን ስላመመኝ ነው” አለች ።

“ዘመቻ ለዘመቻ ያልተንከራተትሽውን ያህል !? እውነትም አዘ ባንሃታል ገብርዬ ! ምን ግዛባነን!አበላሽተሃታል እንጂ !”

“ምን አለበት ዛዲያ !” አለች እየተደፋፈረች ሔዳ ።

“እንዴት እንቺ ጉራዳ ?”

“የምታውንበት ጌታ ፣ የምኩራበት ባል ቢኖረኝ ነዋ !”

“አየሀልኝ ይቺን ያረብ ምላሜ ፣ ሁለታችንንም ባንድነት ስትሞሽልቀን !” አሉ ቴዎድሮስ በመሣቅ ።

“ደሞም ፣ ‘አፍንጫ ቢጉተር እንደ መግላሊት ፣ በደም ይበልጡሽል እንጉራዲት’ ተብሏል ” አለች ታንጉት ፣ የበለጠ እየተደፋፈረች ። አባ ታጠቅ ከት ብለው ሣቁላት ። የውስጥ ስሜቷ ፊንደቀ ። ‘ምነው ዛዲያ ሁልጊዜ እንደዚህ ቢሆን ምን ነበረበት! ያ ነበልባል ቁጣውከየት ይሆን የሚመጣው’ ስትል አሰበች ። ራቧም ቢሆን ትናንት ምሽትና ዛሬም ሌላ ስሜት እንደ ነበራት ለጊዜው ተዘነጋት ።

እንደ ወግ ፣ እንደ ሥርዓቱ ለእራት የቀረበው ድግስ ቴዎድሮስ አሲዘውት የመጡት ድግስ ነበር ።

“ለእኔ ግን ፣ እስቲ ያንቺን እህል ልቅመሰው ። ዘበናይ መሆን ጀምረሽ ወንድሜን ጉድተሽው ይሆናልኮ” አሉ አባ ታጠቅ በቀልድ ። “እይእጅሽስ አሁንም ደኅና ነው። አልተበላሸም”በማለት እመሰገኑዋት፣ ቋንጣውን ወጥ እንድ ሁለት ጊዜ ከጕራረሱና የታንጉትን ቤት ጠላ ከተጐነጩ በኋላ ።

“እጉርሽኝ እንጂ ! ገብርዬንም እጉርሽው ! ወገኛ! መታፈሩ ነው ? በይ ድገሚኝ እንዳንጣላ” ሲሏት ሳይታወቃት እንደ መደንገጥ ልብዋ መታ አደረገ ። ወዲያው ግን መልሳ ተረጋጋች ። የተለመደ ዘዬ ነው ።

የተዝናናው ጭውውት ከእራት በኋላም ቀጠለ ። ቀልድ ፣ ተረብ ፣ የቀድሞ ትዝታ ፣ የአንዳንድ ሰዎች አስቂኝ አድራጎት ፣ የፈሪዎችና የጀግኖች ታሪክ ።

ነገር ግን ፣በጭውውቱ መካከል ዐልፎ ዐልፎ ቴዎድሮስ የረሱት ነገር ትዝ ያላቸው ፣ አዲስ ሐሳብ የመጣባቸው ወይም ከሐሳባቸው ጋር የሚጋጭ በሚመስል አኳኋን ፣ ላንዳፍታ በዝምታ ዓለም ጭልጥ ይሉና ፣ በአብዛኛው አድማጭ እንጂ ተካፋይ ሳትሆን፣ ትንሽ ፈቀቅ ብላ የተቀመጠችውን ታንጉትን ትኩር ብለው ይመለከታሉ።ብሩህ ዐይኖቻቸው የጭንቀት መብራት ሲያንጸባርቁ ወደ ሰው ውስጥ ሠርጸው የሚገቡ ይመስላሉ።

አሁን ግን ታንጉት አላስፈሩዋትም ። የሚመሯሩ ፣ ምሥጢር የሚፈልጉ ዐይነት እንጂ ቁጣ የሚፈነጥቁ አልነበሩም ።

ሆኖም ጥርጣሬ እንደገና መጣባት ። 'ምሥጢሬን ለማውጣት ከሐሳቡ ጋር እየተሟገተ ይሆን ? ነገሩን ሲሰሙ ሰዎች ሁሉ እንዲት እስ ደሚደነቁ ፣ በተለይም የእነእንግዳና የእነ ዓለሚ ሚስቶች ከላይ ኮንፈ ራቸውን እየመጠጡ በሆዳቸው እንዲት እንደሚጣለቁ ታያት ። ከውስጥ ስሜቷ ዘገነናት ። አላወጣችውም ።'

"ምን ትፈልጊያለሽ ጉራዲት ?" ሲሉ ደንገት ጠየቋት ።

ሳታስበው ለመጣባት ጥያቄ መልስ ጠፋት ። "ምን ይሞ ያስፈል ገኛል ?" ስትል መልሳ ጠየቀች ። "ሁሉም ነገር ሞልቷል ።"

"የሴት ጣጣ ማለቂ አይደለም ። ገብርዬ ለዚህ ከሰነፈግ ለጉድ ነው ። ላንቺ ለራስሽ ደስ የሚልሽ ነገር" አሏት ። ዝም ስትልባቸው ጥቂት አሰቡና፣ "ያችን ነገር ይዘሃታል ?" ሲሉ የግምጃ ቤት ባለሟላቸውን ጠየቁት ።

"ምኑዋን አባ ታጠቅ ?"

"ከአገው ንጉሤ ጓዝ ውስጥ ያገኘናትን መስቀል ።"

"አረ አልያዝኳትም ! እንደ ታዘዝኩት አስቀምጫታለሁ እንጂ !"

"እስቲ ሮጥ ብለህ አምጣት" ሲሉ አዘዙት ..... "የምትወጅትን ግሩም ጌጥ ናት' አሏት ታንጉትን ...

"ግሩም አይደለችም ?" አሉ ቴዎድሮስ በመጠየቅ ሳይሆን በግድንቅ አኳኋን ፣ ከግምጃ ቤት ባለሟላቸው የተቀበሉትን በከፊይ ጨርቅ የተጠቀለለ መስቀል ፣ ገላልጠው በሐብሉ አንጠልጥለው እያሳዩ ።

ታንጉት ልብዋ ስንጥቅ አለ ።

ሐብሉ እንደ ሽረራት ድር በረቂቁ የተሠራ ነው። መስቀሉ ከእናቱ ላይ እንድ ፡ ኒጐንና ጐን ሁለት፣ ከመካከሉ ላይ እንደዚሁ አንድ ፣ በጪፍ እንደ ኮከብ የሚያንጸባርቅ አራት ቀይ ፈርጦች አሉት ። 'እንደዚህ ያለ መስቀል የሚሠራ አንጥረኛ በድፍን ጐንደር መኖሩ ያጠራጥራል ። የባሕር ማዶ ሥራ መሆን አለበት' ስትል ታንጉት አሰበች ።

"ተየት አባቱ ነጥቆት ይሆን ?" ሲል ገብርዬ በመገረም አኳኋን ጠየቀ ።

"ፈረንሣዮቹ የላኩለት ስጦታ ወይም ያገር መግጥ ዋጋ ይሆናላ ! አሁን ማ ይሙት ይኽ ለወንድ ልጅ የሚላክ ገጸ በረከት ነው ? ግና እንግዲያው በሴት ጌጥ ሀገሬን እንዲሸጥላቸው ነዋ ?" አሉ ከምሬት ሣቅ ጋር ።

መስቀሉን ሲሰጧት እጃቸውን ዘርግተው ፣ ታንጉትም ለመቀበል ብድግ እንዳለች ፣ "እንዲያውም አንተ አጥልቅላት !" አሉት ገብርዬን ሐሳባቸውን ቀያሪው ፣ ።

"ባንተ ስጦታ ?"

"ምን ነው የኔ የብቻዬ የሚሆነው ? የራሴን ጉንዳላ አውጥቼ አላሠራሁላት ! አብሪን በዘመትንበት የተማረክ ነው ።"

"ቢሆንም ። ይሞም ሐሳቡ የመጣው ታንተ ነው ።"

"ይልቅስ እንካ ! እቧም ደስ የሚሉት ታንተ ሲሆን ነው ። የኔ እጅግ ለማንስ አይደል የሚሰጥ ? ባሌ ገብርዬ የሰጠኝ እያሰች ትኩራራበት እንጂ፣ ዋ ! ዛዲያ ወንድሜን በሚገባ ተንከባክበሽ ያዥው ። ዋ !" አሉ በተልድ ዛቻ ።

ሐብሉ ተጠልቆላት ጥቂት በመሽኮርመም ወደነት ጉልበቱን እንደ መሳም አድርጋ ቀና ስትል ፣ "እህ ! የአባ ታጠቅን ሚማ አትስማም ይል ቅስ ! አባ ታጠቅ ሰላለ ፣ እውነት እኔ የሰጠሁሽ መሰለሽ ጅሌ ?" አላት ።

"አትስሚው" ሲሉ ቴዎድሮስ ለጠቅ አደረጉ ። "ዛዲያ በይ ተነሺ እንጂ !" አሉ ታንጉት በዘያው እንደ ተደፋች ስትቆይ ጊዜ ትንሽ እንደ መገረም እየቃጣቸው ።

በዘያች ቅጽበት ግን ፣ ታንጉት ከራስዋ ጋር በመሟገት ላይ ነበረች። 'እንደ አለቃና ሚኖራ ሳይሆን፣እንደ ወንድማማች ወይም እንደ እኩል ጓደኛሞች በገብርዬና በቴዎድሮስ መካከል ያለው ፍቅርና መተሳሰብ ፣ ሁለቱም ለእርስዋ ያሳዩት ፍቅርና ይህ ነው የማይባል ልግሥና ፡ ስሜትዋን በጥልቅ ነካው ። አንጀትዋን በላው ። ማቂ ፡ አልቅሽ የሚያሰኝ አንድ ልዩ ሲቃ መሳ ሰውነቷን ወረራት ። አንዳች ጠጣር ነገር እንደ ተሰነቀረባት ያህል ጉሮሮዋን ተናነቃት ። በዚህ ስሜቷ መካከል — አሁን መንፈሱ ተረጋግቶና ተዝናንቶ ሳለ፣ ባለማወቅ የሠራሁትን ተናዝዠለት ምሕረት ብጠይቀው—"መቸስ ምን ይደረግ የኔ እኅት ፣ እንግዲህ የፈሰሰ ውሃ አይ ታፈስ ፣ ያለፈ ዐለፈ ፣ ለወደፊቱ ግና ከቶ እንዳይደግሚሽ" በማለት ሳይ ምረኝ ይቀራል ?' የሚል ሐሳብ መጣባት ።

ፍርሃትዋ ደግሞ እዚያው በዚያው ተናነቃት ። 'በይቅርታ ፈንታ ያ ቁጣ ድንገት ቢፈነዳስ ?' የሚል ፍርሃት ። የዚች ወቅት ፍቅርና ደስታ ወደ አስፈሪ ሞኝቅትና ሰቆቃ ትለወጣለች ። በፈገግታ ተውጠው የነበሩ ፊቶቹ የቁጣ እሳት ይተፋሉ ።

ፍርሃትዋ ተስፋዋን አሸነፈባት ። ለአጭር ጊዜም ቢሆን የሰፈነውን ውብ መንፈስ ድንገት መነጠቁ አሳሳት ። እንሰፈሰፋት ።

እንደ ብዙ ሰዓት ለረዘመ እፍታ አምጣ፣ እንደ አሁኑ በመሰለ ደኅና አጋጣሚ ሌላ ጊዜ ለመሞከር በመወሰን ፣ ካጐንበሰችበት ቀና ስትል ወደ ናጅ ዕንባ አቆርዝዘው ነበር ።

"በሱ እንግዲህ ፣ ተበላሁ ተጠጣሁ ልሒድ እንጂ ! " አሉ ቴዎድሮስ በአቆላማጭ ፈገግታ ታንጕትን እየተመለከቱ ፣ "ሌላ ዘንዳ አመሽሁ ብላ ጥሩ ወርቅ ደግሞ ፈቷን ኮሶ አስመስላ ትጠብቀኛለች። ሌላ ሐሳብ ያለኝ ይመስላታል ። "

ታንጕት ፣ ያንን የመሰለ ሌላ ዕድል ሳያጋጥማት ቀረ ።

—4—

ቆንስል ካሜሮን በምድረ ሱዳን በቱርኮች መኻል ክርሞ ፣ በመጨረሻ እንደ ዋዛ መመለሱ ፣ በቴዎድሮስ መንፈስ ላይ ተጨማሪ ማዕበል አስነሣ ።

ቆንስል ካሜሮን፣ ያን ያህል ጊዜ ቆይቶ በመተማ በኩል ተመልሶ ወደ ደብረ ታቦር ፣ ወይም እሳቸው ወደ አሱበት ቦታ ቀጥታ በመምጣት ፈንታ፣ ጕንደር ገብቶ ከአቡነ ሰላማ ጋር መሰንበቱን ቴዎድሮስ ሲሰሙ ቀደም ሲል ከደረሳቸው ወሬ ጋር ተርጣሬያቸው ይበልጥ ተጠናከረ። የረዘመልስ ይዞ ቢመጣ ኖሮ፣ ከእጁ አውሎ አያሳድረውም ነበር ። የደብዳቤ ያቸው መልስ ለጊዜው ባያደርስለት ስንኳ፣ በጎ ፈቃድና ቅን ሐሳብ ካለው ቀርቦ ምክንያቱን ለማስረዳት ችላ አይልም ነበር ። ቴዎድሮስ ፣ ሆዳቸውን እየቆረጠው ቆዩና ደብረ ታቦር መጥቶ እጅ የሚነሣ መሆኑን በግለጽና ፈቃድ በመጠየቅ አስቀድሞ ሰው ሲልክ ፣ ከሚሠፍሩበት ድረስ መጥቶ እንዲገናኛቸው አስታውቀው ወደ ጕጃም ተሻገሩ ። በሽፍታ የሚታወከውን አገር በማርጋት ፈንታ ፣ ቁም ነገር ያልሠራላቸውን አንደ የውጭ ቆንስል በሥነ ሥርዓትና በክብር ለመቀበል ሲሉ ደረብ ታቦር ተቀምጠው የሚጠብቁበት ምክንያት አልታያቸውም ።

ዳሞት ላይ ሠፍረው ሳሉ ደረሰባቸው ።

ቴዎድሮስ ፣ ከድንኳኑ ሠፈር ዳርቻ ከቋጥኝ ላይ ተቀምጠው በጦ ዛቢያቸው ላመል ያህል ዐልፎ ዐልፎ መሬት እየቆረቆሩ ፣ ወደ ተራራው የሚያዘልቀውን መተላለፊያ ባሻገር ይመለከታሉ ። ዐሥር ሺህ የሚሆነው ሠራዊት በሠፈሩ ተበታትኖ ፣ በየቡድኑ ተከማችቶ የዕለት ተግባሩን ብቻ የሚያከናውን ይምሰል እንጂ ፣ በአብዛኛው ነቅቶ የሚጠብቀው ካሜሮን ሲደርስ የሚፈጠረውን ሁናቴ ነበር ።

የረፋድ መንገድ ርቀት ላይ ሠፍሮ ማደሩ ወሬ ደርሷል ። ቴዎድሮስ እየጠበቁት ናቸው ። አልባሌ ለብሰው ፣ አልባሌ መስለው ብቻቸውን እንደዚህ የሚቀመጡትም ከባድ ሐሳብና ትካዜ ሲጫናቸው መሆኑን ብዙው ሠራዊት አሳምሮ ያውቃል ።

ደማቅ ቀይ የሆነው የአቡነ ሰላማ ጃንጥላ፣ ከሩቅ ብቅ ሰል የሁሉም ዐይን ወደዚያው አተኰረ ። ቴዎድሮስ ግን ፣ ለማየት የተጠየፉ ይመስል ከተቀመጡበት ብድግ ብለው ወደ ድንኳናቸው ገቡ ። ራስ እንግዳ ሰዎቹን ለመቀበል ወደ ኋላ ቀርተው ከውጭ ጠበቁ ።

ጓዝ ተራግፎ ፣ መንገደኞቹ እህል ውሃ ቀርቦላቸው ጥቂት ከዐረፉ በኋላ፣ ቴዎድሮስ ሊቀበሉዋቸው ወጡ። ሠራዊቱ ዙሪያውን ሰብሰብ አለ ። ቴዎድሮስ እንገታቸውን ቀልበስ ቀና አደረጉ ። "ደኅና ከረማችሁ ? ደኅና መጣችሁ ? ጉዞዋችሁ ደኅና ነበር ? ችግር አላጋጠማችሁም ?" በማለት በተቻላቸው መጠን ፈገግታ እያሳዩ የሰላምታ ጥያቄ አቀረቡላቸው ። በሕሊናቸው ግን፣ ቀደም ሲል ስለ ካሜሮን አድሮባቸው የነበረው የእመለካከት ና የግምት ስሜት አሁን እንደ ቁርጠት እያ።ማቸው ነበር ...

ቴዎድሮስ ፣ አቡነ ሰላማን በእንዳች ዐይነት ጥርጣሬ እንደ ተጠየፉ ሁሉ ፣ በቆንሲል ካሜሮን ላይ ቅሬታ ያደረባቸው የሹመት ደብዳቤውን ይዞ ለመጀመሪያ ጊዜ ከፊታቸው ሲቀርብ ነበር ። ቴዎድሮስ ከትሕት ናቸው ጋር ፣ በራሳቸው፣ በኢትዮጵያዊነታቸው ኩራት ይሰማቸዋል ። ቆንስል ካሜሮን ደግሞ ፣ በራስ መተማመን ከመኩራት ጋልፎ በራሱና በዘሩ ፣ ሌላውን ሁሉ ከሰማይ ላይ ሆኖ ቁልቁል የሚመለከት ሆኖ ቀረበ ባቸው ። ማራቅ ሳይፈልጉ ሁናቴው ገፈተራቸው ። አሁንም አቀራረቡ አልተለወጠም ነበር ። የበፊቱን ስሜት ቀሰቀሰባቸው .....

ካፒቴን ካሜሮን፣ ቀደም ሲል በቆንስል የሠራ ሰው ስለነበር ችሎታው ባያንሰውም "በካፊር" ጦርነት የተካፈለ ፣ ከሁለት መቶ ማይልስ የበለጠ በጠላት እጅ የተያዘ አገር በማቋረጥ ጅብዱ መፈጸሙ የታወቀለት ፣ በጀኔራል ዊልያም የጦር ክፍል ያገለገለ መኮንን በመሆኑ ፣ በራሱና በእንግሊዛዊ ዜግነቱ ግብዝነት ቢጤ የሚሰማው ነበር ። ይህንን ስሜቱን በቴዎድሮስ ፊት ስንኳን ለመደበቅ አልሞከረም ።

እረመኔ አገር ለመግባት የተጸየፈ ይመስል ምጽዋ ደርሶ ብዙ ወራት ከቆየ በኋላ ፣ እንደዚሁ ጕንደር ያሰኘውን ያህል ከርሞ ለመጀመሪያ ጊዜ ከቴዎድሮስ ፊት ሲቀርብ ያላየው ሁናቴም ይኸንኑ የሚገልጽ ነበር ።

"በግዛትዋ ፀሐይ ከማትጠልቀው ከታላቅዋ ብሪታንያና ከታላቅዋ ቪክቶሪያ በአበሻ አገር ተሹሜ የመጣሁት አዲስ ቆንስል ነኝ" አለ በመጠኑ ወገቡን ፣ ሰበር አድርጎ እጅ በመንሣት ደብዳቤውን እያቀረበ ። ሳሙኤል አስተረጕመለት ።

"እኛኑ ሀገራችንን የዎ ንጠራት ኢትዮጵያ ብለን ነው።ይህን የቁከርን አጠራር ምናለ ብትተዉት" ሲሉ ቴዎድሮስ ኮስተር ብለው አሉት ዋሉት ።

"ይኽ ደግሞ፣ ከታላትዋ ብሪታንያ ታላቅ ንግሥት ቪክቶሪያ የተላከልዎ ስጦታ ነው"አለ ካሜሮን፣ በኋላ በአሽከር አሲይዞ ያመጣውን ዕቃ እየዘረጋ ። ራሳቸው በእጃቸው የሚቀበሉት መስሎት ነበር ።

ላጋፋሪው እንዲሰጠው በእጃቸው እያመለከቱ ፣ 'ምነው ትልቅ ትልቅ ግለት አበዛብኝ ይኽ ሰው!' አሉ በአጠገባቸው ለነበሩት ።

"ታላቋ ንግሥት የላኩት ስጦታ ቢታይልኝ መልካም ፈቃድዎ ሆኖ" አለ ቆንስል ካሜሮን እንደ ወጋግራ ተገትሮ ።

የተሸፈነበት ሐር ተገልጦ በየተራ እየወጣ ታዬ ። አንድ ሽጉጥ ፣ አንድ ጉራዴ ፣ አንድ የፋርስ ምንጣፍ ፣ አንድ መጽሐፍ ቅዱስ ነበር ።

'እንደ ልጅ መጫወቻ የምወድ መሰልኩዋቸው' ለማለት ታጣቸውና ንዴታቸውን ዋጥ አድርገው ፣"መቸም መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ ባገሬ ሞልቶ ተርፏል ። ምሥጢሩን አይረዳውም ፣ ወይም የሚሰብከውን ራሱ አይፈጽመውም እንጂ ፣ ያገሬ ቄስ በየጕጡ ዘወትር እንዳነበነበው ነው ። ምንጣፍም ቢሆን የዓረብ ነጋዴ ያመጣዋል ። እኔ የፈለግሁት ይህንን መሥራት የሚያስተምሩልኝ ዐዋቂዎች ነበር" አሉ ወደ ሽጉጡና ወደ ጉራዴው እያመለከቱ ።"ለሁሉም ለስጦታው አመሰግናለሁ ። በተረፈ ደብዳቤው የሚለውን እንስማው ።"

እማርኛ የሚሞክረው ሙሴ ባርዴልና እንግሊዘኛ የሚችለው አቶ ሳሙኤል ተጋግዘው በመተርጕም እንደ ነገሩዋቸው ፣ የሁለቱ አገሮች መልካም ወዳጅነትና ግንኙነት እንዲኖራቸው የታላቋ ብሪታንያ ፍላጐት መሆኑን ፣ መልእክተኛዋ በኢትዮጵያ የከበሬታና የወዳጅነት አስተነጋገድ እንደሚደረግለት የቪክቶሪያ መንግሥት ተስፋ መሆኑን ከመግለጽና በመጨረሻም ለቴዎድሮስ ረጅም ዕድሜና መልካም ጤንነት ከመመኘት በስተቀር፣ ሌላ ይህ ነው ተብሎ የሚጠቁም ፍሬ ነገር አልነበረበትም ።

"መተሳሰብና መረዳዳት ከሌለበት በባዶው ወዳጅነት - ወዳጅነት ግለት ብቻ ምን ፋይዳ አለውና ? ሕዝቤን እንዳስተምርበትና አገሬን እንዳለማ በባለሙያ ዐዋቂዎች እባካችሁ አግዙኝ ! ብዬ ለላክሁት መልሱ የታለ ብለህ ጠይቀው" አሉ ቴዎድሮስ ። ደብዳቤው የተላከው ገና ፕላውዴን እንደ ሞተ ከመርዶው ጋር ነበር ።

"እንደዚህ ያለው ነገር በኛ አገር ደንብ ፣ ለፓርላማ ቀርቦ ተመክሮበት ነው የሚወሰነው" የሚል መልስ አገኙ ።

"ከሰንት ዓመት በላይ ባንድ ጉዳይ ?"

"ነርክሩ ጊዜ ይወስዳል" ተባለ ።

"ዛሬያ ነገር መቁረጥ ካልቻሉ ጠላ እየጠጡ የሚጨዋዉቡበት የኛው ሰንበቴ ይሻላል በሉኛ ።"

"የሕዝብ ተወካዮች ስለሆኑ፣መቸም መብታቸው መከበር አለበት።"

"ሌሎቹንስ ሕዝቦች ስለ መብታቸው ታግከሯቸዋላችሁ ?"

ቆንስል ካሜሮን፣ ጥያቄው ያልገባው መሆኑን በማመልከት ራሱን እነቃነቀ ።

"ማለቴ ሠራዊታችሁ ፣ ነጋዴዎቻችሁ ፣ ሚሲዮናዎቻችሁ ሲገቡ፣ ሕንዶችን ፣ ዓረቦችን ተዚህ በእኛው አካባቢ አፍሪካ የምትሉዋቸውን ምክር ትጠይቋቸዋላችሁ ወይ ማለቴ ነው ።"

"አሁን መቸም ለማሠልጠንና ለማስተማር ባለብን ኃላፊነት፣"

"ይህንን ኃላፊነት ማን ሰጣችሁ ?"

ቆንስል ካሜሮን ፣ ጥያቄውን ጥቂት አሰበበት ። በዲፕሎማሲ አነጋገር ለመጥለፍ የቀረበ መሆኑ ገብቶታል ።

"እንድ እረኛ ከብቶችን ማሠማራት እንዳለበት ሁሉ ፣ ገናና የሠለጠነ መንግሥት ኃላፊነቱ እንደዚሁ ይሰማዋል በራሱ ።"

"ለዎቹን ከብት አልካቸው ? ከአረመኔነትም አውርደህ ? ምድረ ማህራጃና ሽክ ተወዝፎ እየተሰደበ አገሩን ቢያስወስድ ለነገሩ እኔ ምን አስጨነቀኝ።ይኽንን እንተወው።እንደምትሉት ሕዝቤን የማሠልጠን ፍላጐት ታላችሁ እኔ ሠራዊታችሁን አልፈልግም ። ሰባኪዎቻችሁንም አልሻም ። ወገኔን የሚያስተምሩልኝ ሙያ ዐዋቂዎች እርዱኝ ነው ያልኳችሁ የነበር ። ቅንነት ካለ ዛሬያ ይኽ ምን ይገዳል ?"

"ዋታላቋ ቪክቶሪያ መንግሥት የተቻለውን ሁሉ ከማድረግ አይቦዝንም ። "

ቴዎድሮስ ኮስተርተር አሉ። 'ታላቅ' ማለቱ ምናለ ቢቀር ። እንዲያውም ግብዝነት ሆኖ ነው የሚቈጠርበት ። ደሞም ሁሉም ለየራሱ ትልቅ ነው ። ራሱን በራሱ የሚያዋርድ ብቻ ነው ትንሽ ። እሁን ይህን ጉዳይ እንተወውና ፣ የጠየኩት ርዳታ መቸ ይደርስልኛል! ብለህ ጠይቀው" አሉት አስተርጓሚውን ፣ ሳሙኤልን ።

"በጊዜው" ሲል ካሜሮን ትከሻውን ነቅነቅ እድርጎ መለሰ ።

"ምነው መይሳው ! ምን ዐይነት እጉል መልስ ነው ። ይህማ የዛሬ ዐሥር ዓመትም ይሆናል ። ያኔ ጅብ ከሔደ ውሻ ጮኸ መሆኑ ነው ።

ወገኔ በተሉ ተምሮ ካልጠነከረ ፣ ሀገሬን ያሰፈሰፈባት ጠላት መችፋታ የሚሰጥ ሆነና ! ይዋል ይደር አያሰኝም በለው ።”

“ይህንኑ አሳውቃለሁ ለመንግሥቴ” ሲል ካሜርን መለሰ ።

“እንዴት አርገህ ነው የምታሳውቀው ? መቸም ባሞራ እትልከው። ያሰብኩትን እንተ ካነግህ ዘንዳ ፣ እኔ የምፈልገው መልክት ይዘህ ሒደህ ለመንግሥት እንድታደርስልኝ ነው ። አዎ ፣ ላመጣህልኝ መልክት መልስና ለስጦታዉ ምስጋና ፣ እንደዚህም የሚላኩልኝ ሰዎች ጉዳይ እጣፈ መሆኑን ለንግሥት እጽፍላቸዋለሁ ።”

“እንዴት አድርጌ ራሴ እሔዳለሁ ጃንሆይ ? መንግሥቴ የላከኝ ከዚህ ሆኜ የቆንስላ ሥራ እንድሠራ እንጂ !” አለና ፣ ‘ ለእርስዎ እንድላላክ አይደለም’ ሲል ያሰበውን አቋርጦ ተወው ።

“የቆንስል ሥራ በሁለታችን መካከል ወዳጅነት ግበጀት ግለት አይደለም ? ወይስ ሴላ ሥራ አለህ ? ” ሲሉ በጥርጣሬ አመለካከት ጠየቁት ።

“እሱማ ነው !”

“ዛሬያ ወዳጅነታችንን የምታጠነክረው የኔን መልክት ስታደርስልኝ ነው፣ ነዉ የምለው ። ታለበለዚያ እንዲሁ ተዚህ መቆየትህ ምንም ጠቀሚታ የለውም ” አሉት ። እንድትቆይም አልፈልግም ማለታቸው ሙምር መሆኑ ካሜርን ተሰማው ።

ካሜርን፣ ቆንስልነት ተሹሞ ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣቱ በፊት ቤተ መጻሕፍት ሔዶ ፣ ሰዎች ጠይቆ ስለ ኢትዮጵያና ቴዎድሮስ ስለሚባለው መሪ የቻለውን ያህል ለመረዳት ሞክሮ ነበር ። ካገኘው መረጃ የቀረጸው አሰተሳሰብ ግን ከአጋጠመው ፈጽሞ የተለየ ነበር ። እርግዋ የአክሱም ዘመነ መንግሥት ፣ የአክሱም ሥልጣኔ የሚባል ነበር ። ይህ ግን ፣ ያለፈና ያለቀለት ፍራሹ ብቻ የቀረ ታሪክ ነው ። የጥንት መንግሥት ፣ የጥንት ሥልጣኔ ፍርስራሽ በሶርያም ፣ በኤፍራጥስ ጤግሮስም ፣ በካርቴጅም፣ በግብጽም ሞልቷል ። ኢትዮጵያን ከዚህ ሁሉ ልዩ የሚያደርግ ምክንያት አልታየውም ። ገፋ ግዛት አቋቁመው ሲዋጉ ከኖሩት መኳንንት መካከል አይለው የወጡት ቴዎድሮስ፣ የቀድሞውን ፍርስራሽ እየተመለከቱ ምናልባት የሚጸጽቱ ዐይነት ቢሆኑም ከብዙዎቹ የዐረብ ሼክዎች ፣ የአፍሪካ የጉሣ መሪዎች የተለዩ ሊሆኑ መቻላቸውን ካሜርን ፈጽሞ አልገመተም ነበር ። በዚህ ፈንታ፣ ብዙዎች የአፍሪካና የእስያ የሕዝብ መሪ ነን ባዮቹ አሻንጉሊት እንዳየ ሕዛን ለመንጠቅ የሚከጅሉትን ስጦታ እንደ ቀላል ነገር የሚቁጠር ፣ ያም ሆኖ ለይሉኝታው ያህል ምስጋናውን የሚገልጽ ፣ ኃይሉ ለእንግሊዝ ጦር ኃያል የደግፈኝ ከሚል ይልቅ ፣ ወገኑን በዘመናዊ ዕውቀት የሚያስተምሩለት ባለሙያዎች ዕርዳታ የሚ

ጠይቅ ፣ በዓለም ዙሪያ የተዘረጋው የታላቋ ብሪታንያ ግዛተ-አዲ እሱ ንም እንዳያጨፈልቀው ከሚጨነቅና ከሚለግመጥ ይልቅ ፣ በሥለጠነ መንግሥት እኩልነት የሚያምን አፍሪካዊ መሪ አጋጠመው ። ካሜርን ያላሰበውና የማይፈልገው ነገር ስላጋጠመው ደስ አላሰኘውም ነበር ። ፕላውዴን በምን ዐይነት አቀራረብ ተስማምቶ እንደናረ ሊገባው አልቻለም ። ‘የታላቋ ብሪታንያ ዜግነቴን ክብር ጥቂት በመዋት ይሆን’ ሲል አሰቦ ነበር ። ግን ወደያም ጠላ ፣ ስገቢው ፈታድ ፈጸሚ ከመሆን ሰል በቀ ፣ ሥርስት ራሱን ቴዎድሮስን ሊጋፈጥ እንደማይችል ስለወቀው በሆዱ ጥርሱን ነክሶ በእሽታ እጅ ነሥቶ ተለያየ ።

ቴዎድሮስ ፣ የካሜርን ሁናቴ ስላልጣማቸው ፣ ‘ ባንሩ ቅኝ ግዛት ስሩት፣ እንደ ፍየል ወጠጤ ልቡ ያበጠበት ትዕቢተኛ ሳያቸን እያቀርፐ ፣ ሲሉ ለባለሟሎቻቸው ቢናገሩም ፣ እንደ እንግድነቱ በወግ በሥርዓቱ ለማስተናገድ ፣ ያሰቡትን እንዲፈጽሞላቸው ሰግባበልም ሲሉ ግዥ ሸውን ሁለት ሽህር ፣ ዐሥር ሙክት ፣ ሦስት ገንዘ ጠጅ ፣ አምስት ግድጋ ጠላ ከደንኳኑ ድረስ እንዲላክ አዘዙለት ።

ካሜርን ፣ የቴዎድሮስን መልእክት ይዞ በመተግ በኩል የፈያው ከዚህ ሁሉ በኃላ ነበር ። ከአንድ ዓመት በላይ ቆይቶ ምንም የረባ ነገር ሳያዝ እንደ መጣ ተሰምቶዋቸዋል ። ግን ንዴታቸውን ውጠው በርጋታ ለመቀበል ሞከሩ ።

ሁናቴው እንደዚህ በረድ እንዳለ መቀጠል ሲችል፣አቡነ ሰላማ ሆን ብለው የፈሰጉ ወይም የታዘዙ ይመስል እሳቱን ለኩሱ ። ቴዎድሮስ የሰላምታ ጥየታቸውን ጨርሰው ከመቀመጣቸው በፊት ሰግሰለም መስ ቀላቸውን ቀሰረው ቀረቡ ። ቴዎድሮስ ወደዚያ ወደዚህም ዘወር እያሉ ያሳዩ ለመ ምሰል ሞከሩ ። አቡኑ ግን አልተበገሩም ። እጃቸውን እንደ ቀሰሩ ትንሽ ቆይተው ፣ “መስቀል ይሳለሙ እንጂ ! እግዜር ይፍታ !” አሉ እጃቸውን አስጠግተውና ሮህ ብለው ።

ቴዎድሮስ ደረታቸውን ገፋ ፣ በእጃቸው የጨበጡትን የወር ዘንግ ረገጥ፣ መላ ሰውነታቸውን ቁጥ ፣ ፈርጠም አድርገው አቡኑን ትኩር ብለው ተመለከቱዋቸው ።

“የክርስቶስን መስቀል ይሳለሙ እንጂ” አሉ አውንም ሙዝዝ ብለው ። ቆንስል ካሜርን ከወደ ኃላቸው ቁሟል ።

“ዉት ተሳልሚያለሁ አባቴ !” አሉ ቴዎድሮስ የፈዝ ፈገግታ እያሳዩ ።

“የክርስቶስን መስቀል መሳለም ደግሞ ቢቃኝ ይባላል ? ሲሆንማ ፣ እንደዚህ እንደምንተነፍሰው አየር ዘወትር፣ በአገኘነው ቁጥር ስንቀበ ሰው ጸጋውን ያጐናጽፈናል እንጂ ። ደሞም የአቡን ቡራኬ ...” ሲሉ አንጠልጥለው በመኩራራት ደመደሙ ።

ቴዎድሮስ ፣ አገጫቸውን በመዳፋቸው ዐቅፈው እንደ መሣቅ ቃጣ
ቸው ። “ ለመሆኑ መስቀል አዘውትሮ በመሳም ይጸደቃል ?”

“እህ ? መቸም - መቸም” አሉ አቡነ ሰላማ ትንሽ በመደናገር ፣ አቆብቁቦ የሚያዳምጠው የቴዎድሮስ ታማኝ ሠራዊት እንደማይ
ዳቸው በማወቅ ፣ “መስቀሉን መሳለም ማለት ፣ ከኃጢአታችን ቀ
ሰን ፣ ንስሐ አግኝተን ፣ ምሕረቱን ገበየን ማለት ነው ። ”

“ነው ? ነው ብለው ያምናሉ ?” ሲሉ ቴዎድሮስ ፍርጥም አድርገው
ጠየቁ ።

“ምን ጥርጣሬ አለበት ።”

“እንግዲያማ የርስዎን መስቀል በመሳም ተሆነ ፣ የጉንደር ሴት
ኧረ የሌላውንም ሁሉ ፣ እኔና ሠራዊቴ መቸም መቸም መብለጥ ስለማ
ንችል በከንቱ ነው የምንለፋው ። የገነት ሥፍራ ሞልቶ ነው የሚቆ
የን” አሉ ቴዎድሮስ የፈዝ ሣቅ እየቃጣቸው ።

“የሱ ቤት ለፍጥረቱ ሁሉ ይበቃል ። ደግሞ የጠፉትን በጎች ፈልጉ
ነው የተባልነው” አሉ አቡነ ሰላማ በመርታት አኳኋን ።

“ስለዚህም ነዋ ፣ እልፍኝዎ ለጉንደር ጋለሞታ ሰፈ የሆነው” አሉና
ቴዎድሮስ ኩታቸውን እንደ ማጣፋት አደረጉ። ሠራዊቱ አሽሙሩ ገባ
ቶት እንደ ማውካካት አለ።“ኧረ ! ለነገሩማ ምን አግብቶኝ ? ለሁሉም
የጁን ይስጠው እንጂ ! የርስዎ ሥራ ሌላ፣ የኔ ጉዳይ ሌላ ። ስላነሡብኝ
ብቻ ነው ። አሁንም ዐረፍ ይበሉ ። በጨንገድ ላይ ነው የቆያችሁት ?”
ቴዎድሮስ እንደ ቆሙ ቢሆንም፣ አጋፋሪው አቡነ ሰላማን ወደ መቀ
መጫቸው ሲመራቸው ዘርፋፋ ካባቸውን ሰባስበው ተቀመጡ ።

በጥያቄ መልክ የቴዎድሮስ አስተያየት በቆንስል ካሜሮን ላይ
ሲያርፍ ፣ ቀረብ ብሎ እንደገና እጅ ነሣ ። በብልጭልጭ ቁልፍ ፣ በሚዳይና
በሐር ጉንጉን የተንቆጠቆጠ ሰማያዊ የማዕረግ ልብሱን፣ ሁለት ክንድ
በሚለካ የእንግሊዝ ጐራዴ አጅቦታል ። ከተንቆጠቆጠ አለባበሱ ጋር
ከወገቡ ላይ ብቻ ትንሽ ሰበር ያለ እጅ አነሣሡ ፣ በቴዎድሮስ ፊት ልቆ ፣
ጐልቶ ለመታየት መፈለጉ በግልጽ ያስታውቅ ነበር ።

ከሠራዊቱ መካከል አንዳንዱ በማሽጓጠጥ ከንፈሩን ለጠጠ ።
ሌላው በመገረም በእጁ አገጩንና ጭንቅላቱን ያዘ ።

“ከታላቋ ንግሥተ ነገሥታት የተላከ የመልካም ምኞት ሰላምታ
ዩን አቀርባለሁ” አለ ።

“የንግሥትህን ሰላምታ በከበሬታ እንቀበላለን ” አሉ ቴዎድሮስ
አሁንም በተረጋጋ ሁናቴ፣ “እና ዋና መልክቱ ይኸው ብቻ ነው ?”

“ገጸ በረከትም አምጥቻለሁ ።”

“ቁም ነገሩ አላቂ ጠፊ ስጦታ ብቻ አይደለም ። ሌላስ ?”

ቆንስል ካሜሮን እያቅማማ ፣ እያመናታ ፣ “ መቸም ፣ መቸም ” አለ ።

“የለም ፣ ቆንስል ደበስበስ አታድርገው ጉዳዩን ። ሌላ መልክት አለህ ወይ ? ” ሲሉ ኮስተር ብለው ጠየቁ ።

“ለጊዜው ይኸው ነው ።”

“እንዴት ? የደብዳቤዬ መልስስ?”

“ይመጣል ጃንሆይ”

“እኔ በከበሬታ በደብዳቤ ለላኩት መልክት ፣ ያመጣህልኝ የቃል ሰላምታ ብቻ ነው ማለት ነው ?”

“ለጊዜው አዎ ! ”

“ለምና ?”

“ስላልደረሰ ነው ።”

“የደብዳቤው መልስ ካልደረሰ ፣ የቃሉ ሰላምታ እንዴት ሊደርስ ቻለ? ሁለቱም በሰው ነው የሚመጣው ። ወይንስ የቃሉን ሰላምታ ፣ ወይስ ይኸኛውን በአከናፍ የሚሉ መላእክት አቀበሉህ ?”

ካሜሮን፣ የሚመልሰውን ጥቂት ሲያስብ ፣ እንደ ተረታ በመቁጠር ሠራዊቱ ጥቂት እንደ ማውካካት አለበት ።

“መቸም ፣ በመንግሥታት መካከል ለሚከናወን ጉዳይ በጽሑፍ የሠፈረ ነገር ሁሉ ብዙ ጥንቃቄና ምክክር ስለሚያስፈልገው ነው ። የዘ
መናችን ዲፕሎማሲና ፖለቲካ በጣም ውስብስብ ነው ” አለ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ።

“ዲፕሎማሲና ፖለቲካ የምትለውን ቋንቋ ፣ እንደ ደብተራ ትብትብ አቡሻክር አታስመስለው ቆንስል ካሜሮን ! የኔ ጥያቄ ምሥጢር ፈች የማያስፈልገው ነበር ።ወዳጅን ከጠላት ለመለየት ፣ ወዳጅ የጠየቀውን ዕርዳታ እሺ ወይም እምቢ ለማለት ካመት በላይ ምክክር ያስፈልገዋል ? እንደዚህ በምክር ብቻ ዘመኑን ከፈጃችሁትማ እንዴት ሁናችሁ ነው የሠ
ለጠናችሁት ?” ቴዎድሮስ እንደ መሣቅ ቃጣቸው ። ከሠራዊቱ ዘንድ የመሣለቅ ሁካታ ተሰማ ።

የቴዎድሮስ አጠያየቅ ፣ ስለት ፣ የሠራዊቱ ሥላቅ ፣ የካሜሮንን የታ
ላቂ ብሪታንያ ዜግነት ኩራቱን ቆጠቆጠው ። “ወዳጅነት ሲባል እን
ደዚህ በደፈናው አይሆን ” አለ ።

"እህሳ ?" ሲሉ ቴዎድሮስ በመገረም ጠየቁት ።

"ወዳጅነት የሚረጋገጥበት ብዙ መለኪያ አለው ።"

"ምን ዐይነት መለኪያ ?"

ካሜርን መልስ ሳይሰጥ ዝም አለ ።

"የጥጥ ፣ የጨው ፣ የእህል ነጋዴ ፣ ያተርፈኛል ወይስ ያከስረኛል ያዋጣኛል ፣ አያዋጣኝም ' እያለ እንደሚላክበት ሚዛን ? የእናንተ የሠለ ናችሁት ወዳጅነት ፣ ንግድ መሰል መሆኑን ብሰማም አላመንኩም ነበር ።"

የአሁኑ አነጋገር ካሜሮንን የባሰ ቆነጠጠው ።"እንደሱ ማለቱ አደ ደለም" ሲል ኮስተር ብሎ ተናገረ ።

"እህሳ ?"

"ማለት ፣ በሠለጠኑ መንግሥታት መካከል በሚደረግ ግንኙነት መከበር ያለበት ደንብና ሥርዓት አለ " ሲል መለሰ ፣ ነገሩን ሰሞኑን ከአባ ሰላማ ጋር ወደ ተመካከሩበት ለማምራት እንዲመቸው ።

"እና ፣ እኛ ያልሠለጠነው ፣ ይህንን ደንብና ሥርዓት ለማክበር የቦ ታን አልሆነም ማለት ነው ?" በማለት በስላ ፈዝ ጠየቁት ።

"ይኸ አልወጣኝም ።"

"እህሳ ?"

"ግናስ . . . " ሲል እቋርጦ ተወው ።

ምንም መሪ ያውም ያንድ ጦሰቋላ ሕዝብ መሪ ቢሆንም ፣ በእንድ ጥቁር አፍሪካዊ ፊት እንደዚህ እንደሚሽቆጠቆጥ መደረጉ ፣ በሰላ እን ደበት መጠየቁ ፣ ጭርንቁስ በለበሰ ሠራዊት ፊት መሣለቂያ መሆኑ ግብዝነቱን ቢያፈላበትም ፣ነገርን በልስላሴ መያዝ የሚጠይቀው የዲፕ ሎማሲ ሙያው ሳብ አደረገው ። የእንግሊዝ መንግሥት የውጭ ፖሊሲ ፣ ያልሠለጠኑ ሕዝቦች መሪዎችን ከባላባቱ አንሥቶ በከበሬታ መሸንገል እንደሚያስፈልግ ያስጠነቅቃል ። ነገር ግን ቴዎድሮስ በአገሩ አባባል ፣ 'ሱሪው እስኪጠበው ትልቅነት እየተሰማው ነው' ሲል አሰበ ።

"ግናስ ምን ?"ሲሉ ቴዎድሮስ እንደገና በጥያቄ አፋጠጡት ።

"ጥቃቅን ጉድለቶች ግንኙነቱን ሊያበላሹት ይችላሉ ። ካልተ ረሙ ።"

"ለምሳሌ ?" ሲሉ አሁንም በመኰሳተር ጠየቁት ። ነገሩ አንዳች አገርማሚያ እንዳለው ገብቶዋቸዋል ። ካልደረሱበት ደግሞ አይተዉትም ።

"እኮ ጨርሰው እንጂ !"

ያበጠው ይፈንዳ በሚል ስሜት ፣ ደረቴን ነፋ ፣ አንገቴን ቀጥ አደ ረግ ። "ለምሳሌ የፈላሻ ሚስዮናውያንን ማሰርዎ መልካም አይደለም ።"

ቴዎድሮስ መላ ሰውነታቸውን ነዘራቸው ። ጥርሳቸውን ቅርጭም አድርገው ለቅጽበት አሳለፉት ። "እንዴት ?" ሲሉ በተገታ እንደበት ጠየቁ ።

"ማለት አገር ለማሠልጠን ፣ ሕዝብ ለመርዳት የመጡ የውጭ አገር ሰዎችን አስሮ ማንገላታት፣ የታላቋ እንግሊዝ መንግሥት በደግ እይመለከተውም ። ወሬው ደሞ በሞላ አውሮፓ ተዳርሷል ።"

ቴዎድሮስ፣ የጦር ዛቢያቸውን ርግጥ አድርገው በመደገፍ በግራሚ ትዝብት ትኩር ብለው ተመለከቱት ።"እንድ ዓመት ሙሉ የኔ ደብዳቤ የት እንደ ደረሰ ሳይታወቅ ፣ አሁን ከጥቂት ወር በፊት የሆነው እን ዴት ከእንግሊዝ መንግሥት ጆሮ ደረሰና ፣ እንዲህ ያለ ስሜት ፈጠረ? ይህም እዲስ ተአምር ነው " ሲሉ ሠራዊታቸውን ተመለከቱ ።

"ወሬኮ ከደብዳቤ ይፈጥናል ። "

"ይኸስ እውነትህን ነው ። ወሬኛው ከልቡ ስለሚፈጥንበት ። ይህንን እንለፈውና ፣ ወንጀለኛ ፣ ጥፋተኛ ፣ ወስላታ ባስር ፣ ብቀጣ በናንተ በሠለጠናችሁት ዐይን ጥፋቴ ተምን ላይ ነው ?" ሲሉ ጠየቁ ። ቴዎድሮስ ለዘብ ያለ እንጋገር ካሜሮን እየተደፋፈረ ሒደቱም ትክክል ቢሆን ነው ። የድንቁርና ድፍረት የሚያሳዩ ሰዎች እንደ እን ዳንድ አውሬ ዐይነት የፍርሃት ጀርባ ከሰጡዋቸው ዘለው ጉብ ይላሉ ። ፊት ለፊት ሲፋጠጡዋቸው ግን ያፈገፍጋሉ፣ ወይም ባሉበት ቁጥ ይላሉ ሲባል ሰምቶ ነበር ።

አሁንም የቴዎድሮስን ሁናቴ በዚሁ ተረጕመው ።"በሠለጠኑ ሕዝ ቦች ዘንድ ማንም ሰው ጥፋት ሠራ ቢባል ተመስክሮበት ሳይፈረድበት አይታሰርም ። በተለይ ደግሞ ፣ የሌላ ሀገር ዜጐች ከፍተኛ ጥንቃቄና ከበ ሬታ ሊደረግላቸው ይገባል ። እንዳገሬው ሰው መታየት የለባቸውም ። ያገራቸው መንግሥት በዲፕሎማሲ መንገድ በጣም ያስብላቸዋል ። ጥቃቅን ጉድለቶች የመንግሥታትን ግንኙነት ሊያበላሹ ይችላሉ ያል ኩት ስለይህ ነበር ። በሚስዮናውያኑ መታሰር የእንግሊዝ መንግሥት እንዳይከፋ በጣም ነው የምሠጋው" አለ ካሜሮን እንደ መንጉራደድ እየታጣው ።

ሁናቴው ቴዎድሮስን ከማናደድ ይበልጥ አስገረማቸው ።"እሱ አላካቸው ። ለመሆኑ ፣ ስለነዚህ ቀጣፊ ወንጌል ሰባኪ ነን ባዮች የንግሊዝ መንግሥት ምን አገባውና ነው የሚከፋው ?" ሲሉ ጠየቁ ።

"ሁለቱ የእንግሊዝ ዝርያ አለባቸው ። ሌሎችም ያው የአውሮፓ ነጮች ናቸው ።"

"እሃ !" አሉ በመገረም ሣቅ ፣ " ዘመድ ተዘመዱ አሀያ ታመዱ እንደሚባለው መሆኑ ነው ? ፈረንጆች እንደዚህ መሆናችሁን የታባቱ ዐወቅሁና ! "

"የቆዳ ቀለም መሳሳብ ሳይሆን ፣ በዓለም ዙሪያ የተዘረጋው ታላቁ የእንግሊዝ ግዛተ - ዐጼ ፣ በብዙ የዓለም ክፍሎች የሚፈጸመው ድርጊት ሁሉ ያሳስበዋል ። ታላቅነቱ ኃላፊነትን አብሮ ጥሎበታል ። "

ቴዎድሮስ ንዴት እንቅ አደረጋቸውና እንደ ምንም አመቋት ፣ " እሺ በጀ ! ግሩም ነው። ኃይለኛ ከተባለ የትም አገር ገብቶ እንዳሻው ሊሆን ይችላል ማለት ነው ። "

ካሜሮን፣ለመመለስ ተግ ሲል ቀደም ብለው ያቀዱት ይመስል አቡነ ሰላማ ለጠቅ ብለው ተናገሩ ።" መቸም ፣ እንደዚህ ያለው ትልቅ ኃላፊነት ፣ ከራሱ ከባለቤቱ ሳይሆን ከላይ ከእግዚአብሔርም በአደራ የሚሰጥ ነው ። ለምሳሌ ፣ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን በሌሎች አገሮች ምዕመናን ላይ ፣ ሥልጣን - ሰማያት ቢሰጣት ነው አገር ድንበር የማያ ከልላት ። "

ቴዎድሮስ አላስጨረሱዋቸውም ። ግን ደግሞ ንዴቱ እንዳቃጠላቸው በጩኸት አልገነፈሉም ። " አባቴ ! አባቴ ልበልዎ ? አዎ ይባላሉ ። ግን ስለ ክርስትናና ስለመንፈሳዊ ሥራ አሁን በድንገት ከሚያነሱሌላ ሌላ ጉዳይዎን ቢሠሩ ይሻላል ። እስቲ ልጠይቅዎ ! የእርስዎ የመንፈስ አባትና እንደ ፈረደብን የእኛም የመንፈስ አባት የሆኑት ፣ የእስክንድርያው ፓትርያርክ መጥተው ፣ በመንፈሳዊ አባትነታቸው እንዲያ በክብርና በፍቅር ተቀብለን ፣ ሃይማኖታዊ ድጋፋቸውን ስንጠይቅ፣እሳቸው ምን ነበር አጥብቀው የያዙት ነገር ? ስለ ቱርክ ፓሻ ትልቅነትና በጎ ሐሳብ አልነበረም ? አዎ ! ይኸው በሰልፍ ወጥቶ በየደረሱበት ያጀባቸው ሠራዊቴ ይመስክር ። አሁን ደሞ ለእንግሊዝ መንግሥት የታላቅነት ኃላፊነት ። ለስንቱ ነው የሚያድሩ አባቴ ? መቼስ አባቴ ልበልዎት እንጂ ። ትናንት ክርስቲያን ሆነው ለእስላሙ ቱርክ ፓሻ ። ዛሬ ደሞ እንደኛም ባይጠቁሩ ፣ አፍሪካዊ ሆነው ላውሮፓ ። በእምነት ሳይሆን በትልቅነት ብቻ ? ሌላውን ስንኳ እንተወው ። የግልዎ ጠባይ ተሆነ መቸስ ምናረጋለሁ ። በሀገሬና በመንግሥቴ ጉዳይ ግን ባይገቡ ይበጃል ። " ወደ ቆንስል ካሜሮን ዘወር አሉ።" አንተን ልጠይቅህ እስቲ መልስልኝ ?"

" መመለስ የምችለው ተሆነ ምንተዳዬ ። "

" እንተ ላመጣኸው ጉዳይ መልስ መስጠት አለብህ እንጂ ። ያፍህ ወለምታ ተሆነም ስሕተትህን ታምናለህ ። አይደለም ወንድሞች ! " ሲሉ በዙሪያቸው የቆሙትን በአስተያየት ጠየቁ ። ብዙ ጭንቅላቶች በእምንታ መልስ ተነቃነቁ ።

ካሜሮን፣ ምን ቸገረኝ በማለት አኳኋን ትከሻውን ሰበቅ አደረገ ።

"እሺ" አሉ ቴዎድሮስ አሁንም በትዝብት እያስተዋሉ ። "ላንድ አገር ባዳ የሆኑ ሰዎች ቢያጠፉም መታሰር መቀጣት የለባቸውም ብለሃል ። "

"ጥፋታቸው ካልተረጋገጠ በስተቀር" ሲል ካሜሮን ለማስተካከል ቃጣ ።

"እሱ ይሁንልህ ። ዛሬያ ገናና ትልቅ የምትለው ያንተ መንግሥት ፣ ያንተም ብቻ ሳይሆን ፣ የፈረንሣይም ፣ የሠለጠኑ የምትላቸው ያውሮፓ መንግሥታትም ፣ ድንበራቸውን ዐልፈው ፣ ባሕርና ውቅያናስን አቋርጠው ፣ ሌላውን ዐቅም የሌለውን ሕዝብ የሚያሥሩት ፣ የሚያንገላቱት ፣ የሚረግጡት ፣ የሚጨፈጭፉት ምን ባጠፉ ነው ? ቢያጠፉስ በሰው አገር እንሱን ምን ዶላቸውና ነው ? በራሱ አገር በራሱ ፈቃድ ሥራት ይተዳደራል እንጂ ። " ካሜሮን ወዲያው ስላልመለሰላቸው " እኮ አስረዳኝ እንጂ" ሲሉ አፋጠጡት ።

ካሜሮን አሁንም ትከሻውን ሰበቅ አደረገ ። "መቸም እንዳልኩት ታላላቅ መንግሥታትና የሠለጠኑ ሕዝቦች ኃላፊነት አለባቸው ። "

"ማን ሰጣቸው ይህንን ኃላፊነት ! "

"የሥነ ምግባራቸው ከፍተኛነት ፣ የዕውቀታቸው ዋልቀት ፣ ትልቅነታቸውም ጭምር ራሳቸው በራሳቸው ኃላፊነት እንዲሰማቸው ያደረጋቸዋል ። "

"ተሰማይ ቤት ተሰጣቸው አለማለትህ ባይሆን ተእነአባ ትሻላለህ" ሲሉ ቴዎድሮስ አቡነ ሰላማ ፈታቸውን ጭፍግግ አደረጉ ። "ዛዲያ ይህ ኃላፊነት፣ ለመርገጥ ፣ ለመግደል ፣ ለመዝረፍ ፣ አገር ለመውሰድ ጭምር ነው ? " በማለት ቆንስል ካሜሮንን እንደገና ጠየቁት ።

ሠራዊቱና ዙሪያውን የቆሙት ባለሟሎቻቸው ቃላቱን የሚቀበሉ ይመስል ፣ አመለካከታቸውን ከአንዱ ወደ ሌላው እያቀያየሩ ነገሩን በትኩረት ይከታተላሉ ።

"መቸም አንዳንድ ጊዜ" አለ ቆንስል ካሜሮን ፣ ጉዳዩን በጥልቅ ያስበበት ይመስል ግንባሩን ሽብሽብ አድርጎ ። 'ያልሠለጠነ ደንቆሮ ሕዝብ የሚጠቅመውንና የሚጐዳውን አያውቅም ። ሕግን እሳት ልጨብጥ ይላል ። እንስሳ ገደል ይገባል ። ወይም የእውሬ ምግብ ይሆናል ፣ ጠባቂ ከሌለው ። እና ፣ ከብት ለመግራት ፣ እውሬ ለግልሙድ እንደሚደረገው ሁሉ ' ሊል የተመኘውን ወደ ጎን ትቶ፣ "ለእነርሱ የወደፊት ደኅንነት ሲባል ፣ አንዳንድ ጊዜ ታዲያ ፣ ኮስተር መረር ማለት ያስፈልግ ይሆናል ። መጨከን ሳይሆን . . . "

"ምን !? " ቴዎድሮስ ንግግሩን ማስጨረሱ አላስችላቸው አለ፥ ራሳቸውን ገታ አድርገው ነገሩ እንደ ተእምር አስገርሞዋቸው፣ እንግ ቸውን በመዳፋቸው ደገፍ አድርገው ለጥቂት ጊዜ በሐሳብ ተመሰጡ ሲያስቡትም ነገሩ የባሰውን እርር ቅጥል አደረጋቸው ። አባቴስ ይህን ነገር ይስማሙበታል ?" ሲሉ አቡነ ሰላማን ጠየቁ ። አቡነ ሰላማ መልስ አልሰጧቸውም ። " እንዲህ ያለው የሥልጣኔ አስተያየ ባፍንጫዬ ይውጣ ።" ቴዎድሮስ ጣታቸውን በካሚሮን ላይ ቀሰሩ፥ "እንደናንተ ያልሠለጠነው ወገኔም ፣ እንደ ከብት ነው ማለት ነው፣ አይደለም ? " ሲሉ ጠየቁት ።

" እንደዚህ ማለቴ አይደለም " ሲል መለሰ ።

"ነው እንጂ ! ስም ባትጠራ በደፈና ብለኸው የለ ? ለካስ ፣ በዘመ ጅነት ፣ ወገኔን በሙያ ለማሠልጠን ርዱኝ ብዬ ለላኩት ደብዳቤ መልስ በማምጣት ፈንታ ፣ በጠላቶቼ መኻል ከርመህ ባዶ እጅህን የተመለስክው እንደምትሉት በኃይል እየረገጣቸሁ ለማሠልጠን እንዲመቻችሁ ኑሯል እኔ የዋሁ ይህን መቸ ዐውቄ ? በሉ ንሡ ውሰዱና ቀፍድዱልኝ " ብለው ከማዘዛቸው፣ በካሚሮን የትዕቢት አነጋገር ከመረው ጋር አብሮ ሲፀ ሽቅ የቆየው ወታደር ከመቅጽበት የፈጥኝ ቀፍድዶ ያዘው ።

"በምን ጥፋቴ ነው የምታሰረው ?" ካሚሮን የፍርሃት ጀርባ ከማ ሳየት አሁንም ፊት ለፊት መፋጠጡ ፣ ቴዎድሮስን እንዲያፈገፍግ የሚያ ደርግ ዘዴ መስሎ ተሰማው ። "ደግሞም የታላቋ ብሪታንያ መልክተኛ ነኝ" አለ ።

"ጥፋትህ ? አንድ፣ ሀገሬን ፣ ወገኔን እኔንም ቄምር በማዋረድ ተሳ ድበሃል ። ሁለት፣ ከጠላቶቻችን ጋር በመሆን ሀገሬንና ወገኔን የሚጉዳ ዱለታ ስታደርግ ከርመሃል ። ወይስ ሠልጥነናል የሚሉት ነጮች በጥ ፋት እይጠየቁም ? ወይዳችሁም ጠላችሁም ባገሬ ደንብ ትጠየቁበታ ላችሁ ። የታላቋ እንግሊዝ መልክተኛ ስለ መሆንህ ግን ሁሉም ለራሱ ታላቅ ነው ። 'እሳት ቢያንቀላፋ ገለባ ጉበኘው' አሉ ፣ ውሰዱልኝ ከፊቴ !" ሲሉ አዘዙ ።

ወታደሮች፣ ቆንስል ካሚሮንን እየገፋፉ ገለል ሲያደርጉት አቡነ ሰላማ የሚባርኩ ይመስል፣ መስቀል የጨበጡበትን እጃቸውን አሁንም ዘርግተው ተነሡ።"ጃንሆይ ፣ ጥፋተ ም ካለ በይቅርታ ፣ አለመግባባትም ከሆነ በመነጋገርና በመመካከር እንዲያልፉት በስመ አግዚአብሔር እለምንዎታለሁ ። ቁጣ ፣ ለምድርም ለሰማይ ቤትም እንደማይበጅ በመጽሐፍ ተጠቅሷል ። እና አሁንም ።"

"አባቴ መጽሐፉን ያውቁታል ?" አሉ ቴዎድሮስ በፈዝ ።

አቡነ ሰላማ ያልሰሙ በመምሰል፣ "ይቅር ተባባሉ ይቅር መባባሉ ነው ደጉ ነገር ።"

"ተጉንደር እልፍኝዎ ክህነት ለመስጠት ስንኳ ፣ እሞኛል ደክሞ ኛል የሚሉት ሰውዬ ፣ ያለወትሮዎ እየተጉተቱ የመጡት ለዚህ ናፖሬል ገባኝ ።"

"ቅድም መስቀል ላሳልምዎት ብለ እምቢ አሉ ። አሁን ደግሞ ታረቁ ፣ ተሰማሙ . . . የለም እንዲህ አይሁኑ ጃንሆይ ። ታለበለዚያማ ሰው የሚለው" አቡነ ሰላማ ድፍረትን ከቆንስል ካሚሮን መቅጸት ሞክረው መጨረስ አቃታቸው ።

"ምን ? ሰው ምንድን ነው የሚለው ? ይናገሩት እንጂ ! ለነገሩማ ባገሬ ፣ በወገኔ ፣ በኔ ላይ ከሚዶልቱት መካከል ዋናው እርሶ አይደሉ ? እንኳን እርስዎ፣ የርስዎ መንፈሳዊ አባት የተባሉት አቡነ ቄርሎስ ሳይ ቀሩ ፣ ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ ስለ ሰይድ ፓሻ አይደል ዘወትር የሚያ ስቡ የነበሩት ? ልጅም የሚወጣው ባባቱ ነው። ስለይህም ፣ ወደ ንግዱ ፣ አገር ወደ ግሻሻጡ ቢያደሉ አይደንቀኝም ።"

እንዱ ቆንስል ካሚሮን ሳይሆን ፣ በአሁኝው የከረረ የንግግር ልውውጥ ሠራዊቱ እንደ መደናገጥ አለ። ምንም ብዙ ቢወራባቸውም፣ ከተ ንት ሲያያዝ በመጣ ታሪክ መንፈሳዊ አባት ተብለዋልና ፣ ኃይለ ቃል ሲሰነዘርባቸው ማየትና መስማት ትንሽ የሚሰቀጥጥ ፣ ለጀሮ የሚ ከብድ ሆነቦት ። ከሰዒ ሁናቴ ይህንን የተገነዘቡት አቡነ ሰላማ ድፍ ረት አገኙ ።

"እኔ እንደሆነ ፣ ገና ለገና ቁጣ ፣ ግዞት ወይም እስራት ፈርቶ ከመ ንፈሳዊ ሥራዬ ከቶ ዝንፍ አልልም ። ሥጋዬን እንጂ ነፍሴን ቅንጣት እንደማይነኳት ዐውቃለሁ ። ሥጋዬ ለኔ ምኔ ነው ! ይልቁንስ እርስዎን ገዝቸ ፣ ከኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን እንዳልነጥልዎት ምክሬን ቢሰሙ ይሻላል ። "

"ወይኔ መይሳው ! ለማስፈራራትም ተቢቃን ?" አሉ አባ ታጠቅ ከቁጣ ይልቅ በመገረም ራሳቸውን እየነቀነቁ ። "እኔስ ተዛሬ ነገ ይኛ ልዎታል ብዬ ችየም ነበር ። እኔ ሞኑ ጠላቴን በጉያዬ አስቀምጬ ። እገር በግዝት የምሸጥ ከመስልዎ ያገኙታል ። ንሡ እመሩልኝ !" ሲሉ ድን ገት አዘዙ ። በካሚሮን ላይ የተረባረበውን ያህል፣ በቅርብ የነበረው ወታ ደር አሁን እንደ ማመንታት አለ ።

"ወቸው ጉድ !" ቴዎድሮስ የምሬት ሣቅ ከጀላቸው ፦" የፈረን መን ደር አህያ ይወረዋል እንዲሉ ፣ የስንቱ የጉንደር . . ." ሲናገሩት የታዘቡትን ቃል መልሰው ተዉት ። "ስንት ወይዘሮ የተሳለ ውን ፣ የሰዒድ ፓሻን

ባለጊል ከገደ መታዘ ፈራችሁ !" ሲሉ የቂቶች ወታደሮች ብዙም ሳ
ንነሱ ከብብ አድርገው ያዟቸው ።

"ገዘቻለሁ ! ገዘቻለሁ ! 'እጅን የሚያሳርፍብኝ ፣ በሰጣኒ ፣ ሙ
ደር ውጊ ከሙ አርጵሰ' ገዘቻለሁ ! እንዳትነኩኝ ገዘቻችኋለሁ ! ቁም
ርስንም አውግዣለሁ !" እሱ እስን ሰላግ ፣ ሳያስቡት ደንገት ሽጮ
ሰራቸው ከተሰሙደ እነጋገራቸው በላይ ቢሆኑም ፣ እንደ ፅዉድ እሰሙ
ሰላቸው እንጂ ለጊዜው ሰሚ አላገኙም ።

ግምኛውን ሰፈሩ ርጭ ያለ ጀተታ ሰፈነበት ። ብዙው ሠራዊት
ግን ፣ በደረሰው ሁናቴ እንዳች የሐሳብ ጀነም ሰል ተጫነበት ፣ ተጽናነ
ደም ወገን ከፍ እድርን የሚሠቀውት አልነበረም ። ከፈሉ በየግደሪያው
ተጋደም ፣ ዕድሉን ያነብበት ይመስል ከምኩብት ይቋተራል ። አሁ
ከልሳት ጻር ተቀምጦ ከነበልባሱና ከፍሙ ጋር የጀምታ ውይይት የሚ
ያደርግ ይመስላል ። በዚህ ጀተታ በዋጠው ሠልግ ፣ ሲያተምና ሲያ
ትራንር የሚሰግው የቁምደርስ በጥና ብቻ ነበረ ።

የተቃኘ ደረት ጅግት ላይሆን ሕይወት እንዳለው ፍጡር እያነ
የሚያንትራንር ፣ ሆድ እያባባ . . . .

ሦስተኛ መጽሐፍ

አባ ታጠቅ

የጽዮን ላይ እሬሳ

የቢያ እምበሳ

የኳሣ

በሙቶ ዓሙቱ ቢያነሳ

ስንቁን

ስንቁን ተሰቀሰውሳ ።

(ስደቱ መታፈሪያ ፣

('የተስፉ እግር ብረት')

ምዕራፍ ሰባት

ዐቀበት ሲወጣ ወደ ኋሊት እየሳበ ጊዜ የመውሰዱን ፣ ቁልቁለት ሲወ
ርድ ደግሞ ሳይወዱ የማንደርደሩን ያህል ፣ ቴዎድሮስ ግዕዝኛዊ ሠን
ግሥት ለመመሥረትና ለግጽናት ፣ አገር ለግደላደል ፣ በሠራዊትም ፣
በቤተ ክርስቲያንም አዲስ ሥርዓት ለመዘርጋት ፣ ሕዝብ ለግረጋጋት ፣
አዲስ ዐይነት ተስፋና ሕይወት ለማሳየት ፣ ከዐሥር ዓመት በላይ የፈ
ጀባቸው የተግባር ሕንፃ መፈራረስ ሲጀምር፣ እንደ ናዳ ተከታትሎ ሰመ
ውረድ ጊዜ አልወሰደበትም ።

ዳሞት ላይ ቆንስል ካሜሮንና አቡነ ሰላማን አስረው ከተመለሱ
ወዲህ ደግሞ፣ የፍራሽ ናዳው ፋታ የማይሰጥ ሆነ ። ቴዎድሮስ ያላሰቡት
የመጀመሪያው ናዳ የወረደው ደብረ ታቦር በገቡበት ዕለት ነበር። መጀታ
ቤቶች በበዙበትና ንጋዴውም ፣ ወታደሩም በሚሠማራበት አካባቢ ማም
ሻውን ከባድ እምባጓሮ ተፈጥሮ፣ ከዱላ ዐልፎ የተዉጨፈ ተኩስ ቀለጨ።
በግርግሩ መኻል ከአንዱ በተነሣው እሳት ሳቢያ ብዙ ቤቶች ተቃጠሉ።
በዚህ ምሽት በደብረ ታቦር ከተማ፣ የጠፋው ንብረት ፣ የሞተውና የቆ
ሰለው ሰው ከዚያ በፊት የማይታወቅ ዐይነት ነበር ። የደብረ ታቦር ነዋሪ
መዓት የመጣ መሰለው ። አንዱም የተረጋገጠ መነሻ አላገኘም ። የሚ
ያወራው በወሬ ወሬ የሰማውን ብቻ ነው ።

ምናልባትም ግዝቱ ተሰምቷቸው የአቡነ ሰላማን እስራት በሚ
ቃወሙና ቴዎድሮስን በሚደግፉ መካከል ፣ እንደ ዋዛ የተነሣው ክርክር
በሞቅታ ኃይል ወደ ተካረረ እምባጓሮ እምርቶ ሊሆን ይችላል ። በሌት
ምክንያት በወታደሮች ወይም በወታደሮችና በነጋዴዎች ምክንያት የተ
ፈጠረ የቅናት ጠብ ወደ ሌሎቹ ተጋብቶ ይሆናል። ምናልባትም ደግሞ
የአቡነ ሰላማን ግዝት አምነው የተቀበሉ ክርስቲያናች ባደረባቸው
ስሜት ወይም ቀደም ሲል በእስር ላይ የቆዩት የፈላሻ ሚሲዮናውያን
በኋላም ቆንስል ካሜሮን፣ በነገዙብም በሱብኪትም ያዘጋጇቸው ሆነ
ብለው የጠነሰሱት ሤራ ሊሆን ይችላል ። ወይ እንዳጋጣሚ ሁድም ተደ
ማምሮ ይሆናል ።

ያም ሆነ ይህ ፣ ብዙው ሰው ፣ አስቦም ሊያስብም ፣ ፈልጉም ሳይ
ፈልግም ፣ከሥረ መሠረቱ እንደ ተናጋ ሕንፃ የቴዎድሮስ ደጋፊና ተቃ
ዋሚ በመሆን ከሁለት እየተሰነጠቀ መጣ ። ትንሽ እምባጓሮ በተነሣ

ቁጥር ከሁለት ተከፍሎ ከተጨፋጨፈ በኋላ ተቃዋሚው ወገን የጎ
ደለውን ገድሎ ፣ የሞተበትን ትቶ ከደብረ ታቦር እየኮበለለ ሲወጣ ፣ ያኛው
እየተከተለ ሲያሳድድ ፣ በመካከሉ የአቅራቢያውና የአካባቢው ገበረ ፣
መንገድ መርተሃል ፤ አስጠግተሃል እየተባለ አብሮ ሲመታ ፣ ግጭቱ ፣
ጥፋቱ ምሬቱ ከቀን ቀን እየተስፋፋና እየከፋ ሔደ ።

የልብ ልብ እየተሰማው ፣ በሰሜንና በምሥራቅ ከወሎ ፣ በምዕራ
ብና በደቡብ ከጉጂም የሚመጣው ሽፍታም በሰላም ሊቋጣጠሩት የሚ
ችሉትን ግዛት እያጠበበው ስለ ሔደ፣ ሠራዊቱ በዚያው መጠን ቀለብ
ሲያጥርበት ወደ ዘረፋ ማዘንበሉ ሁናቴውን አባባሰው ።

ሠራዊታቸውም ሆነ አገር ያላወቀው ነጋዴ ፣ ከደብረ ታቦር እንዳይ
ወጣ ቴዎድሮስ በጥብቅ የደነገጉት ዘረፋውንም ፣ የወታደራቸውን ከዳ
ትም ለመግታት ነበር ። በየኬላውም ተቋጣጣሪ ዘብ ተደረገ ። ግን አል
ሆነም ።

ደብረ ታቦር ዙሪያውን አጥር እንደሌለው ሁሉ ፣ በየምሽቱ የሚ
ከዳውን ወይም ጨለማ ተገን አድርጎ ለመረበሽ ተኾልኮ የሚገባውን
ማገድ አልተቻለም ። እንዲያውም በተቋጣጣሪ ዘብና በእምቢተኛ መካ
ከል ያለማቋረጥ የሚደረገው ግጭት የደብረ ታቦርን ከተማና አካባ
ቢውን ጸጥታ ነሣው ። መርዶ ፣ ቀብር ፣ ጎዘን ፣ ለቅሶ የዘወትር ኑሮና
ትርሲት ሆነ ። የቴዎድሮስ ብስጭት በዚያው መጠን እያከለ ሔደ ።

አንዳንድ ሰዎች በድፍን ግምት የተስፋ ተስፋ እንዳደረጉት ራሳም
የተባለው ሰው ከእንግሊዝ መንግሥት ተልኮ መምጣትም ፣ በቴዎድሮስ
ላይ የተሻለ ሁናቴ አላስከተለም ። ራሳም ያመጣላቸውን የሩቁን አቅር
ቦና አጉልቶ የሚያሳይ መነጽር ስጦታ የወደዱለት ከመሆኑ በቀር ደህና
የትሕትና አቀራረብ ዐዋቂ ስለነበር ፣ ቴዎድሮስ ከሌሎቹ የተሻለ አክብ
ሮት አሳይተውት ነበር ። ዐልፎ ዐልፎም በሁለቱ መካከል ልዩ መተሳ
ሰብ የታየበት ጊዜ ነበር ። ነገር ግን፣ቀደም ሲል ለጠየቁት የባለሙያ እር
ዳታ ፣ "ይመጣሉ ግዴሎትም" ከሚል የተስፋ ቃል በስተቀር የሚ
ፈልጉትን የተረጋገጠ መልስ ሊሰጣቸው ስላልቻለ እንደ ሌሎቹ በመ
ጨረሻ እሱም ታሰረ ።

የውጭ አገር መንግሥታት በኢትዮጵያ ላይ ስላላቸው ዓላማ ፣ የቴ
ዎድሮስን ጥርጣሬ የሚያጠናክር ሌላም ተጨማሪ ወሬ ደረሳቸው ። ይኸ
ውም ከእስክንድርያ እስከ ምድረ ሱዳን የምድር ባቡር ዝርጊያ መጀ
መሩ ነበር ። ቴዎድሮስ ፣ ስለዚህ የባቡር ሐዲድ ጉዳይ ራሳምን ደጋ
ግመው ጠይቀውታል ።

"ወንድሜ ራሳም ፣ ይህንን የባቡር ሐዲድ ምን ልታረጉበት ነው ?"

"ንግድ ይስፋፋበታል ። ሰው ይመላለስበታል ። ይጠቅማል እንጂ
ምን ጉዳት አለበት ? "

"መጥቀሙንማ መቸ አጣሁት ፤ ጥቅሙ ለሌላ መሆኑን እንጂ !"

"ሌላ ምንም ስውር ዓላማ የለበትም ! ፣"

"አገሬን ለመውረር ሠራዊት የምታጓጉዙበት መሆኑን መቸ አጣ
ሁት ። እንተማ ዛዲያ ይኸንን አምነህ ልትነግረኝ ኑሮዋልን ? እንዲያው
ለነገሩ ፣ ተሰይድ ፓሻ የኔ ወዳጅነት አይሻላችሁም ነበር? ግን እናንተ
የምትፈልጉት ወዳጅ ብቻ ሳይሆን እሽከር ጭምር የሚሆናችሁን መሰ
ለኝ ። እኛ ሁለቱንስ እንሆናችሁም ። እሽከርነቱን እናውቅበት ። እይ
ሆንልን . . . ይሁንና፣ከሌሎች ሕዝቦች እንደ ለመዳችሁት ወገኔ በቀላሉ
የሚበገርላችሁ ይመስላችኋል ? ተሆነ እናያለና ! " ይሉታል በምጸት ።

ራሳም ፣ ጥርጣሬያቸውንና ሥጋታቸውን ሊያስተባብል ይሞክራል ።
ቴዎድሮስ ሳይቀበሉትም ፣ በብርቱ ሳይከራከሩበትም በሆዳቸው የቋ
ጠሩትን ቋጥረው ነገሩን የተዉት ይመስላሉ ።

ግን ዓላማቸውን ባዶ ሕልም ብቻ በማድረግ ፣ መገንባት የጀመ
ሩትን በመናድ ፣ በውስጥ አንድ አካል መሆን የያዘችውን ኢትዮጵያን
ለመገንጣጠል ከተነሡት ዓመፀኞች ጋር ፣ ከውጭ እንደ ሕንድ ፣ እንደ
አፍሪቃ ኢትዮጵያን ለመግዛት ከሚመጡ ወሪራዎች ጋር፣የመጨረሻ ጦር
ነት ማድረጋቸው እንደማይቀር ስለሚሰማቸው ፣ የሚያዋጣ እንደ መሰ
ላቸው መዘጋጀታቸውን ከጀመሩት ቆይተዋል ።

የዝግጅታቸው አንዱ ክፍል መቅደላ ነበር ።

የሰብል ዐይነት ሁሉ በአንድነት እንደሚወቃበት የአንድ ጐጥ
የጋራ አውድማ ሁሉ ፣ ወሎዬዊ ፣ ትግሬዉ፣ አማራዉ ፣ አሮሞዉ ፣ ከዐሥራ
ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ፣ ሲገናኝ ፣ ሲጣላ ፣ ሲፋለም ፣
ሲጻቀል ፣ ሲቀላቀል ኖሮበታል ። ለዚህም ዋናው መናኸሪያ በዋድላ
ደላንታ የሚገኘው የመቅደላ አምባ ነው ።

ለምሽግነት የሰጠ ፣ አማካይነቱ ያመቸ በመሆኑም ጦርነት ያሰበ
መኮንንና አዲስ የተነሣ ሽፍታ ተሸቀዳድሞ መያዝ የሚፈልገው የመቅደ
ላን አምባ ነበር ።

ቴዎድሮስ፣ ወደ ወሎና ሸዋ ሲዘምቱና ሲመለሱ ፣ ከወይዘሮ ወር
ቂት ሠራዊት አንሥቶ አፍላ ጉልበት የተሰማው ሽፍታ መሽጉበት እያ
ገኙ ደጋግመው ከአስለቀቁ በኋላ፣ በመጨረሻ ጠባቂ ወታደር በማስፈር፣
ቤትም ፣ ክትርም አሠርተውበት ነበር ። እየቆየም ፣ ዓላማቸው ከቀን
ወደ ቀን እየተሰናከለ ሲሔድ ፣ ከቋራ እስከ አንኮበር ሲያንከራትታቸው
ለኖረው ሕልማቸው የመጨረሻ መናኸሪያ መቅደላ አምባ እንዲሆን
የወሰኑ ይመስል ፣ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የታሪክ ቅርሶችና የክብር ዕቃ
ዎች እየተሰበሰቡ በዚያ እንዲቀመጡ ማድረግ ጀምረው ነበር ።

እንደ ጉንደር ከተማ ፣ ደብረ ታቦርም በአሱባልታ ፣ በወሬ በሚረ መበከል ከያዘ ወዲህ እያስጠላቸው ሔድዋል። ልጃቸው ዓለማየሁ በዚህ በሽታ መካከል እንዲያድግ አይፈልጉም ።

ከሁሉ በፊት ግን ፣ የጋፋቱ ሥራ መጠናቀቅ ነበረበት ።

ቴዎድሮስ ሐሳባቸውን እያውጠነጠኑ ፣ ምሬታቸውን እያብሰ ለሰሱ ፣ ብቻቸውን በየመስኩ ፣ በየዱሩ ይዘዋወራሉ ። ዛፉን ፣ ዝግባውን ፣ ዋርካውን ፣ ጥዱን ፣ ወይራውን በስስት እየተመለከቱ ፣ ቁጥቋጦ ውን እያሰሱ ፣ አበባውን እያደነቁ ፣ ለዚህ እህል ፣ ለዚያ እህል ፣ ለግ ሎሽ ለመስክ የሚሆነውን መሬት ያስተውላሉ ፣ ወይም ደግሞ ከእንድ ቦታ ላይ ይቀመጡና ከሩት ፣ ከአድማስ ጀምሮ እስከ አጠገባቸው መስክ ድረስ ወይናቸው የሚደርስበትን ሁሉ ይቃኛሉ ። ከሰማዩ ጋር የተጋ ጠመ የሚመስል ተራራውን ፣ ከሥሩ የተጋደመ ረባዳውን ፣ ከእንድ በኩል የተንጣለለ ሜዳውን ሌላ ሌላውንም ሁሉ በተራ በተራ ያዳር ሱና ፣ ያስተውሱና ፍዝዝ ትዝዝ ይላሉ ። አገር ፣ እናት ሀገር ፣ እትብት ፣ ሕይወት የሆነች አገር ልትገዛ ? ልትወስድ ? ላትናር ፣ ላንናር ?

መንፈሳቸውን ሰቀቀን ተጭኖት ፣ ወደ ቤት ወይም ወደ ድንኳና ቸው ሲመለሱ ፣ ጥቂትም የሚያጽናናቸው ልጃቸው ዓለማየሁ ነበር ።

“ አባዬ !” ይላቸዋል ፣ ጉልበታቸውን ተደግፎ በመቀመጥ ።

“ወዬ ዓለሜ ! ፣”

“እስቲ ተረት አጫውተኝ !”

“ምን ዐይነት ተረት ልጅ ዓለም ። ?”

“ የጦርነት ! ደስ ደስ የሚል !” ከዕድሜው በላይ ንቁ የሆነው ዓለማየሁ የአራዊትም ይሁን የሰው ፣ አብዛኛውን ጊዜ መስማት የሚ ወደው የውጊያ ታሪክ ነው ።

“ጦርነት ምን ያረግልሃል ። ጦርነት መጥፎ ነው” ይሉታል ጉን ጩን በቁልምጫ ቆንጠጥ እያደረጉ ።

“ዛዲያ አንተ ውልጊዜ ለምን ውጊያ ትሔዳለህ ?” ሲል ይጠይቃ ቸዋል ።

“ ወድጀን መሰለህ ? ‘በጥባጭ ካለ ግን ጥሩ ይጠጣል’ ሆናብኝ ነው እንጂ” ሲሉ በቅሬታ ይተነፍሱና ፡ ስለ ሰላምና ስለ ጦርነት ፡ ስለ ሀገርና አንድነት ፡ ስለ ምኞታቸውና ስለ ሥጋታቸው ሊያወያዩትና ሊረዳላ ቸው ከሚችለው ዕድሜ ገና ባለመድረሱ ፡ ግን የልጅነት ፍላጐቱን ለመረ ጃም ፡ ሳያውቅቅ የሚያስደንቀውን ፡ ሳያሰልስ የሚያስገርመውን ፡ ከጀግንነት ጋር ርኅራኄ ፡ ከድፍረት ጋር ብልሃት የሚያሳየውን በሐሳባ

ቸው እየመረጡ ያሜውቱታል ። ግን የልጅ ፍቅርና የልጅ ጨዋታ ብቻ ውን ፡ የሕይወታቸውን ባዶ እየሆነ መሔድ ፡ ሊተካላቸውና ሌላ ፍላ ጐታቸውን ሊያሟላላቸው አልቻለም ። ተፈጥሮዋቸው እጅግ ሰፊና ውስብስብ ሰብአዊ ግንኙነቶችን ይፈልጋል ። ዓለማየሁ በመጠኑም ቢሆን ልባቸውን ለተወሰነ ጊዜ የሚያሞቅላቸውን ያህል ፡ ይህንን ውብ ልጅ ያገኙባት እናት፡ ጥሩ ወርቅ ደግሞ ፡ ከዕለት ዕለት ልባቸውን የናትር ውርጭ የምታለመታ ሆነች ።

የፍቅር ፍላጐታቸውን በማርካት ረገድ ፡ ወትሮም እምብዛም የነ በረችውን ያህል ዓለማየሁን ከወለደች በኋላ ደግሞ ግዴታዋን ተወጥታ ያበቃች ይመስል የሚስትነት ፡ የሴትነት ድርሻዋን እርግፍ አድርጋ ተወችው ።

አንድ ቀን ቴዎድሮስ፡ውጭ ውለው እልፍኝ ሲገቡ ጥሩ ወርቅ የል ጃገረድ ሱሪ ታጥቃ ቆየቻቸው ። እንዳጋጣሚ ፈቅደዉ ነበርና በትዝብ ትና በመገረም እየተመለከቱ ፡ “ምነው ? መንገደኛ ነሽ እንዴ?” ሲሉ ጠየቋት ።

“ባልሆንስ ምነው ? ነውር አለበት ?” ስትል መለሰችላቸው ።

“አረ አልወጣኝም” አሉ ቴዎድሮስ ስሜታቸውን ዋጥ አድርገው... ከተዋበች ጋር ከቆረቡ ወዲህ ያን ዕለት ለመጀመሪያ ጊዜ ፡ ከጋ ብቻ ውጭ ሌላ ሴት ዘንድ ሔዱ ። የሚፈልጉትን ያንድ ለእንድ ፍቅር ለማግኘት ባለመቻላቸው እያደር ሌሎች ዕቁባቶች አስቀመጡ ። ከእንድ ሁለት መለኪያ የማያልፍ ከነበረው መጠናቸው በላይ አረቄ መጠጣት ጀመሩ ። ጥሩ ወርቅም ፡ እንድ ዐይነት መከላከያ ጋሻ ያዘጀች ይመስል ሱሪ መታጠቋን ቀጠለችበት ።

ቴዎድሮስ ፡ እንደ ዓላማቸው ሁሉ የግል ሕይወታቸውንም ጭጋ አለበሰው ። የዓለማየሁ ግጽናናትና ግጫወት የመንፈሳቸውን ጩኽ ሊያቃልል የማይችል እየሆነ ሔደ ።

እንዲያውም ፡ ዓለማየሁ ነፍስ እያወቀ ሲሔድ፡ የአባቱ ሐሳብና ሥቃን በሊጋ ሕይወቱ ላይ የተጫነ ይመስል ፡ ወይም ደግሞ እንደ አባቱ ደብረ ታቦርን መጸየፍ የጀመረ ይመስል ፡ እንደ ዕድሜ እኩያዎቹ ብዙ መጸየፉ ሩንና መጫወቱን ተወው ። በገጽታው ላይ ከልጅ ፍገስታ ይልቅ ፡ ሐሳብ

እንደሚያመዝንበት ቴዎድሮስ ብዙ ጊዜ አስተውለዋል ። ይህም ሆኖ ፣ ውጭ ውለው ሲመለሱ ፣ የውስጥ ስሜቱን እንደ ምንም በፈገግታ አል ብሶ ከበር ላይ ይቀበላቸው ነበር ። አንድ ቀን ይህንንም አስታጉለ ።

"ምን ሆንክ የኔ አካል ?" ጉንበስ ብለው ጉንጩን እየደባበሱ ጠየ ቁት ።

"ምንም አልሆንኩ አባዬ !" ዓለማየሁ ፊቱን ለማሳየት ያልፈለገ ይመስል አንገቱን ቀና አላደረገም ።

"ዛዲያ እንደ ሽማግሌ ብቻህን ምን አፍዝዞ አስቀመጠህ ? በል ተነሥ !"

ተነሥቶ ፊቱን ሲያስተውሉት ፣ አንድ ነገር እንዳገኘው እርግጠኛ ሆኑ ። ዕንባው የደረቀበት በሁለት ጉንጮቹ ላይ ጥንድ ትልም ሠርቶ ነበር ።

"እናትህ መታችህ ?" በማለት እንደገና ጠየቁት ፣ በማቆላመጥ እኳኋን እጁን ጨብጠው ወደ አልፍኝ ሲያመሩ ።

"አረ አልነካችኝም !"

"ዛዲያ ከልጆች ጋር ተደባደብክ ?"

"ብደባደብስ የኔ እጅ በሶ ጨብጧል ?" ሲል ዓለማየሁ መለሰ በተወጠረ ፈገግታ ።

"የኔ አንበሳ ! ጉበዝ መሆንክን መቸ አጣሁት ። ብዙ ሆነው ገጥ መውህ እንደሆነ ብዙ ነው እንጂ ።"

"ለምን ብዙ ቢሆኑስ እኔ እፈራቸዋለሁ ?"

"ጐሽ ግልገል አንበሳዬ !"

"ለምን ሺህ አይሆኑም ! " አለ በልጅነት ድፍረት ።

"እሺ ፣ የኔ አካል ዛዲያ ለምን አለቀስክ ?" አሉት ቴዎድሮስ እልፍኝ ገብተው ከተቀመጡ በኋላ ፣ በጉልበታቸው መኻል አጣብቀው እያቆላመጡ ።

"አላለቀስኩምኮ አባዬ !" ካጣብቂያው ፈርቅቆ ለመውጣት በቀ ልድ መልክ ታገላቸው ።

"ዛዲያ ይኸ ዕንባ ተየት መጣ ?"

"እንዲያው ነው ።"

"አንድ ነገር አግኝቶሃል ? ።"

"ምንም አልሆንኩ እያልኩህ !"

"ውሸት !"

"እውነቴን ነው !"

"እስቲ ሙት በለኝ !" አሉት ቴዎድሮስ በውሸት ፍተሚ ።

"ለምን ትሞታለህ አባዬ ?"

"እውነቱን ተነገርከኝ ፣ እንኳን ሞት ጉንፋንም ባጠገቢ ዝር አይል ። እና ፣ እስቲ 'ምንም አልሆንኩ ሙት' "በለኝ !" የዓለማየሁን ጉንጭ እንደ መቆንጠጥ አደረጉት ። "በልኮ" ዓለማየሁ እንዲመታው የዘረጉለትን እጃቸውን ጨብጦ ዝም አለ ። ለመግል አለመፈለጉ ያስታወቅ ነበር ።

"በል እንግዲያው የሆንከውን ንገረኝ ። "

"እኔማ ምንም አልሆንኩ !"

"እዛዲያስ !"

የመጣበትን ልቅሶ ለመግታት ሰውነቱን ወጥር ከአትግማና ከተ ጨነቀ በኋላ ተነፈሰው ። " ሰዎች የሚጠሉህ ለምነው አባዬ ?" ሲል በቦዘዙ ወይኖቹ እየተመለከተ ጠየቃቸው ።

"መቸም ሰው ሁሉን ሰው አይወድም ። ሁሉ ሰውም አይወድደ ውም ። አንተስ አንዳንድ ጊዜ የግትወደው ልጅ አለ አይደለም ? ግን ሰዎች እንደሚጠሉኝ በምን አወክ የኔ አካል ? ዛሬ ነው ?"

ዓለማየሁ ጥቂት አመነታ ።

'ያባትክን ጥፋት ነጋ ጠባ እየሰማህ ስታንባ ኑረሃል ማለት ነው ?' ብለው በልባቸው ቴዎድሮስ በእዘኔታ ከንፈራቸውን መጠጡ ። ዕንባ ቆጠ ቆጣቸው ። "እሺ ዛሬ ያስለቀስህን ብቻ ንገረኝ ። ታለበለዚያማ የመከ ረኛ አባትህን ስንቱን ጉድ ታወራው ብለህ ፣ የኔ አካል ። ፍርጃ ነው !"

ዓለማየሁ ያፈረበት ይመስል ፣ አንገቱን ጥቂት ደፉ አድርጎ በዕለቱ የደረሰበትን ነገራቸው ።

ከምሳ በኋላ ወደ መስክ ወጥተው ለመጫወት ፣ ከሦስት ጓደኞቹ ጋር ሆኖ ፣ ፈረንጆቹና ኢትዮጵያውያን ከሚጠበቁበት ሰፊ አጥር ግቢ አጠ ገብ ሲያርሱ ውሻ የሚከተላት አንዲት ሴት ያገኛሉ ። ስንቅ አድርሳ መ ለስዋ እንደሆነም እንጂ አገልግል ይዛለች ። ሊተላለፉ ሲሉ ውሻው ያጉ ረመርምባቸዋል ። አንደኛዉ ጓደኛቸው በትሩን ይቃጣበታል ።

የሐር እጅ ጠባቡ የቀለም ድምቀት ዐይኑን ስቦትም ይሁን እንጂ ፣ በትር የቃጣበትን ልጅ ትቶ ዓለማየሁን ለመንከስ ይሞክራል ። ዛዲያ መቸም ዝም ብሎ አይነክስ ! ወይ ሴትየዋ ውሻውን አልያዝችለት ። ዓለማየሁ ፣ በትሩን ዘርግቶ ከተከላከለ በኋላ በመጨረሻ እንድ ሁለት ጊዜ ይለምጠዋል ።

ሴትዮዋ ፣ዓለማየሁ እንዲነከስ ትፈልግ የነበረ ይመስል ፣ ውሻው ከጼላው ወደኋላ ሲያፈገፍግ ጩኸትዋን ትለቀዋለች ። በእሪታ ሰማይና ምድሩን ታደባልቀዋለች ። እርግማኑንና ስድቡን ታወርድበታለች ። አላፊ አግዳሚውም ፣ እየቆመ ለሴትዮዋ ያግዛል ። እስረኞቹም በእጥሩ ላይ ሆነው ከሴትዮዋ ጋር በግበር ብዙ ይጨዋጨዋሁበታል ።

በመካከሉ ጓደኞቹ ጥለውት ሲሮጡ ፣ ዓለማየሁ እንዳች ዐይነት እልህና ንዴት ድርቅ አድርጎ ይዞት ፣ መለፍለፉ እስኪታክታቸው ድረስ ያስጨርሳቸዋል።"ግን ተነሡ ፌትኮ አላለቀሰኩም ፣ አባዬ !" አለ ዓለማየሁ የሆነውን ተናግሮ ሲያበቃ ።

"ጉሽ የኔ ግልገል ። ዛሬያ እንደ ሴት እንባ ልታሳያቸው ናሯል !" ሲሉ በማደፋፈር ፊቱን እባበሱት ። "ምን ምን እያሉ እንደ ተሳደቡ እኮ አልነገርከኝም ? ። "

ዓለማየሁ መድገሙ ቀፍፎት ፣ እባክህ ተወኝ በሚል አስተያየት ተግጠናቸው ።

"ንገረኝ እንጂ ምን አሳፈረህ ? በእደባባይ ተዘርቶ አገር ምድሩ የሰማውን ? "

"ጨካኝ የጨካኝ ዘር አለችኝ " አለ ዓለማየሁ የልጅ መልኩን ጭፍግግ አድርጎ ።

"ደሞስ ሌላ ?"

' እንደ አባትህ አረመኔ ፣ ነፍሰ ገዳይ ነህ ' አለችኝ ።

ቴዎድሮስ በምሬት እንደ መሣቅ ብለው ራሳቸውን ነቀነቁ። " እሺ ሌሎቹስ ምን አሉኝ ?"

' ተስረኞቹ አንዱ ፣ 'አትፍረዱበት ፣ ሰውነቱ ጠንክሮ እንደ አባቱ ጭከናውን በሰው ላይ እስቲፈጽም ድረስ በእንስሳ እየተለማመደ ነው ' ሲል ፣ የነበሩት ሁላ ተሣሣቁብኝ ። ሌላም ሌላም ብለዋል ። "

ቴዎድሮስ ፣ ቆዳቸውን ለመላጥ የፈለጉ እስኪመስል ድረስ በሐሳብና በጭንቀት ፊታቸውን በመዳፋቸው ፈተጉት ።"እኔንስ መቸም እንዳሻቸው ያሉኝን ይበሉኝ ። እንደ ሐሳቤ ፣ እንደ ዓላማዬ የልቤን የሚያውቅ

ይፍረዱኝ ፣ ይፍረድብኝ ። እኔ እንደሆነ ከዚህ በኋላ ምንም ግድ የለኝ ። ግን አንተን ደሞ ምን አርግ ነው የሚሉ የኔ አካል ? ለዐዋቂ ሰውም ቢሆን ፣ ያንዱ ጥፋት በዘር ወደ ሌላው ተላልፎ አያስጠይቀውም ። አያስወቅሰውም ። ባገራዉ አጉል ልማድ በደም ታልተፈለገ በስተቀር ። ዛሬያ ግና እርም ያህል ሕፃን ቁም ስትል ሲያሳዩ ሌላው ቢቀር ጡር አይፈሩም?" ከአደጋ የሚከልሉት ይመስል ጭምት አድርገው አቅፈውት ቆዩ ። "ለመሆኑ ሴትዮዋን ታውቃታለህ ?" ሲሉ ጠየቁት — በመጨረሻ ። በእሱታ መለሰላቸው። "እንዴት ያለች ናት ?" እንደ መሰለው ሁናቴዋን ገለጸላቸው ።

"በሽተኛም ተሆነች እንዳሻት። ታልሆነችም የርዕ. ስድብና ርግማን ለኔ ንስሐ ሆኖ ቢታዘዝልኝ ነው ። አንተን ማስደንገጥዋን ጠላሁት እንጂ የርኂንስ እችለዋለሁ፣ሰሞኑን ደሞ መለስ ብላልኝ ሰንብታ ነበር ። ድንገት ምን ነካት ?" አሉ በመገረም ።

"ማናት አባዬ ?"

"ስምዋማ ምንትዋብ ትባላለች ። ለምን እንደዚህ ሆነች ለሚለው ግን ፣ ለልጅ የማይጥም ረጅም ታሪክ ነው ። ምናልባት ስትደርስ ወደፊት ታውቀው ይሆናል ። "

ግን አባዬ . . . " ዓለማየሁ ጀመረና በፈራ ተባ አቋርጦ ተወው ።

ዓለማየሁ፣ ቴዎድሮስ ስለ ዓላማቸው ከሚነግሩት ረቂቅ ጉዳይ ይልቅ፣ በሐሳቡ ጉልቶ የሚታየው ቀን የደረሰበትና ከብዙ ሰዎች የሚገነዘበው ክፉ አመለካከታቸው ነበር ። በልጅ ምርጫው ፣ "እኔና አንተ ለምን ሌላ አገር ሔደን ብቻችንን አንኖርም አባዬ ?" ሲል ድንገት ጠየቃቸው።

"ደብረ ታቦር አስጠላህ?" አሉትና ፣ የሚያደርጉትን ግን ፣ ወዲያው በሆዳቸው ወሰኑ ።

— 2 —

ወደ መቅደላ የሚሔደውና ከደብረ ታቦር የሚወጣው ሰው ሁሉ ሰላመ ነግት እንዲዘጋጅ ቴዎድሮስ ባስታወቁበት ወቅት፣ ታንጉት ክፋኛ አም ዋት ሰንብቶ ነበር ። ገብርዬ ሲነግራት ቀስፎ በያዘ ውጋትዋና እንደ እሳት የሚጋረፍ በሚመስል ትኩሳትዋ መካከል፣ እንደ ምንም እያታሰተች ተነ ሥታ ጓዝ ማሰናዳት ጀመረች ።

"አሁን ዛዲያ ምን እያረግሽ ነው ?" ሲል ገብርዬ ጠየቃት፣ በመ ገረምና በመደናገጥ ።

"ሒዱ ተብሏል አላልክም ?" ስትል መልሳ ጠየቀችው ።

"ዛዲያ እንደዚህ ሆነሽ መንገድ ልትነሽ ኑሮዋል ? ስለ ወደፊቱ ነገርኩሽ እንጂ !"

"ደኅና ነኝ ። ምንም አልል" አለች ታንጉት ፣ የመቅደላውጉዞ የሥ ጋትዋ አንድ መገላገያ ሆኖ እየታያት የጊዜው ሕመ ምዋን ቻል አድርጋ።

የቴዎድሮስ ጥረት ሁሉ በዚህም በዚያም እየተበላሸባቸው ፣ ሰቀቀና ቸውና ብስጭታቸው በዚያው መጠን እየከፋ መሔዱን ታንጉት ስትመ ለከት፣ ጥፋትዋን ተናዝዛ ይቅርታ የማግኘቱን ሐሳብ ተስፋ ከቈረጠችበት ቆይታለች ። ከሚስተር እስተርንም ሆነ ከሌላ ምሥጢሩ ወጥቶ ፣ የቴዎ ድሮስ ቁጣ የሚሰነዘርባትን ቀን ነበር በጭንቀት የምትጠብቀው ። ይህም ጭንቀት በጤንነትዋና በሰውነትዋ ላይ ለውጥ አስከትሎ ነበር ። ያለ ወትሮዋ ብዙ ጊዜ ራስ ምታት ይነሣባት ጀምሩዋል ። ጉንጭዋ ላይ በሚ ያምሩት ስርጉዶቿ ፈንታ የመጠውለግ መሥመሮች ጕልተው ይታያሉ። ትንሽ ትልቁ ነገር ብስክስክ ያደርጋታል ። ደግነቱ ገብርዬ አብዛኛውን ለዘመቻ ስለሚንቀሳቀስ፣ውናቴዋ በሁለቱ ግንኙነት ላይ ስለሚያመጣው ለውጥ የመገንዘቢያ ርጋታ አልነበረም ።

ቴዎድሮስና ጥቂት የጦር አበጋዞቻቸው ፣ ጋፋት ቀርተው ታንጉትና ሌሎቹ መቅደላ መቀመጣቸው ፣ ከፊት መራቅ ከልብ መራቅ ነውና ከልብ መራቅም ፣ ከቁጣም ሆነ ከፍቅር ስሜት ራቅ ማለት ነውና ፣ ምሥጢርዋ ተቀብሮ ፣ ከጊዜ በኋላ ተረስቶ እንዲቀር የሚያደርግ መልካም አጋጣሚ መሰላት ። ሕመ ምዋ ብርቱ መሆኑ ቢሰማትም፣ እንደ ምንም ቶሎ መራ ቱን መረጠች ።

"እሆሆ ! ኧረ ተይ ! ስንኳን በኩበት ቢቃሬዛም አትችይ !" አላት ገብርዬ በእጁ እንደ መከልከል እያደረገ ።

"እችላለሁ አልኩህ!" ታንጉት ጓዝ ማሰናዳቱን በእልህ ተያያዘችው።

"ተይ ስልሽ ? ተይ !" አለ ገብርዬ በቁጣ መልክ ።

"እንተስ ያባ ታጠቅን ትእዛዝ እምቢ ማለትህ ነው !" አለች ፍር ጥም እድርጋ ።

ገብርዬ ፣ ምክንያቷን ሊገምት ባይችልም፣ድርት ብላ መነሣትዋ ደስ አላለውም ። "ተመንገድ ላይ እንድ ነገር ብትሆኝ፣ አባ ታጠቅ የሚወ ቅስ እኔን ። እንዲያውም መታመምሽን አልነገርኩትም ። ታንቺ ጋራ ተመጨቃጨቅ እንዲያውም አሁኑኑ እነግረዋለሁ ። ራሱ ይወስናል ።"

ቴዎድሮስ ማምሻውን ከነገብርዬ ቤት መጥተው ፣ ሁናቴዋን ከአ ዩና ፣ ግንባርዋን በመዳፋቸው ዳስሰው ትኩሳትዋን ከገመቱ በኋላ ፣ "ለመሆኑ መቸ ነው የጀመራት ?"ሲሉ ጠየቁ ።

"ሦስት ቀን ሆናት" አለ ገብርዬ ።

"ዛዲያ ለኛ አልነገርከኝም ?"

ገብርዬ አንገቱን ደፋ አድርጎ ዝም አለ ።

"ባንተ ቤት እኔን ተጨማሪ ሐሳብ ውስጥ እንዳልገባ ብለህ ነው። አይ ደለ ? ደግ አላደረግህም። "ወደ ታንጉት ዘወር አሉ ። "መንገዱን ስትድኝ ትደርሺበታለሽ ። ነገ ጧት ግን ፣ ተቻልሽ በኩበት ታልቻልሽ ቢቃሬ ዛም ቢሆን፣ ጋፋት ሔደሽ ሐኪም ብላንክ አይቶ ያክምሻል ።"

የሕክምና ችሎታ ያለው ዶክተር ብላንክ ፣ እስከ ጥቂት ወራት በፊት ድረስ ከሌሎቹ ፈረንጆች ጋር ደብረ ታቦር በእስር ላይ ነበር ። የጋ ፋቱ ባለሙያ ሚስተር ዋልድሜየር ፣ ከጥቂት ወራት በፊት ሚስቱ ወን ጌለ በጠና ታመመችና ፣ ዶክተር ብላንክ ጋፋት በአጠገብዋ ሆና እያከማት እንዲሰነብት ቴዎድሮስን ለመነ።ሊቀ መኳስ ቤል ከኢትዮጵያዊት ሚስቱ የወለዳትን ወንጌለን ፣ ቴዎድሮስ ለዋልድሜየር ራሳቸው የጻሩለትና እንደ ልጃቸው የሚያይዋት ስለሆነች ያለማሙንታት ፈቀዱለት። ዶክ ተር ብላንክ ፣ ወንጌለን እያከመ ጋፋት ሲሰነብት ፣ በብረት ግቅለሜው

እሳትና በሌላም በሌላም የሚያርሰውን የእደጋ ቁስል በማከም ረገድ ብዙ ስለረዳ በዚያው እንዲቆይ ተደረገ ። በዚያው የጋፋት ሐኪም ሆነ። ቴዎድሮስም፣ የአስረኛነቱን ጉዳይ ትተው ‘ሀገራችሁ አለ እንደምትለው ትልቅ ቤት እሠራልሀና ወገኔን ሁሉ ታክምልኛለህ ። የኔንም ሰው ጥበቡን ታስተምርልኛለህ ’ ይሉት ነበር ።

በበነጋው ጧት፡ቴዎድሮስ እንደገና ወደ ገብርዬ ቤት መጥተው ታጎ ጉትን በታሪካ አሸክመው ወደ ጋፋት መንገድ ሲጀመር ፣ “ጥሩ ወርቅን ሸኝቼ እኔም እመጣለሁ” ብለውት ገብርዬን፣ ወደ ቤተ መንግሥት አመሩ።

ቴዎድሮስ፣ የገዙውን መሰናዶ በአጠቃላይ ቃኘት እያረጉና ፣ ከቤቱ ግድግዳ ጥግ ከቋንጣ ወንበር ላይ ተቀምጠው ጥሩ ወርቅን በታኩተ ትዝ ብት ተመለከቷት ። ጥሩ ወርቅ እስከ ልብ አልግው የመንገድ ልብስ ዋን ለብሳ ፣ እጉርዋን በሻሽ ዐሥራ ፣ የኮርቻ በቅሎዋ ስትሰናዳ ፣ ፊትዋን አኮሳትራ በንቀት ታስተውላለች ። ትልልቁ ጓዝና የሞንት ከብቱ ተደም ሲል ተነሥቶ ጉዞ ጀምሯል ። የቀሩት የጥሩ ወርቅ ደንገጡሮችና እጃቢ ወታደሮች ብቻ ነበሩ ። ሁሉም ነገር መዘጋጀቱን ባልደራሱ እጅ በመንግት ሲያስታውቅ ፣ ጥሩ ወርቅ እንደ መንግት ታጣትና ቅሪ እንድትባል የምትጠብቅ ይመስል አመናታች ።

ዓለማየሁ ፣ በልጅ ባሕርይ እንደ ዋዛ ከወዲያ ወዲህ ይበል እንጂ ሐሳቡ በወላጆቹ መኻል ተንጠልጥሎበት ነበር ። ነገሩ በትክክል ባይገ ባውም የግታ ከርክራቸውን ከሞላ ጉደል አዳምጧል ። አሁንም በመ ካከላቸው ዝምታ የሰፈነበት ውጥረት ይሰማዋል ። እንዳንድ ጊዜ ስንኳ ተሣሥቀው ሲለያዩ ቢያይ፣ ምንኛ ደስ ይለው እንደ ነበር ያስባል ።

“ዛዲያ እህል ቀምሰሽ ብትነሽ እይሻልም ?” የሚል የአባቱን ድምፅ ሲሰማ ፣ ዓለማየሁ ዝም ብሎ ያዳምጥ ጀመር ።

“እላሰኝኝም” ስትል ጥሩ ወርቅ መለሰች ።

“ስላሰኝን ሳይሆን ፣ ለሆነለት መንገድ በባዶ ሆድ መጀመር ደግም እይደለ !”

“ሰዎቹ ይቁረሱ” አለች ጥሩ ወርቅ አሁንም እንደ ተኮሳተረች ።

ቴዎድሮስ ግን፣ይህንን ሐሳብ እንዳልሰማ ያህል ችላ ብለው ዐለፉት። ምክንያቱም ደንገጡሮቹም ሆኑ እጃቢዎቹ ጥሩ ወርቅ ሳትቀምስ ፣ ቆር ላችሁ ሒዱ ቢባሉ ፈቃደኛ እይሆኑም ። እዲስ ነገር ይሆንባቸዋል ። ከፊ ታቸው ራቅ ስትል፣ሰዎቹም ለራሳቸው ወስፋት ሲሉ እህል እንዲቀምሱ ሲጠይቋት፡እሺ ትል ይሆናል ብለው በመገመት ሁሉንም ባንድ ዐይነት በባዶ ሆድ መላኩ የተሻለ መሰላቸው ።

“እሺ እንግዲያውስ ፣ ፀሐይ ሳይበረታ በረሃውን እንድትሻገሩ ብት ነሡ ይሻላል” አሉና ቴዎድሮስ ከተቀመጡበት ተነሡ ።

ጥሩ ወርቅም ተነሣችና ክንድዋን ወደፊት ዘርግታ ‘ይሽው’ አለች ።

“ምኑ ?” ሲሉ ጠየቁ ቴዎድሮስ፣ የንገሩ አዝማሚያ ቢገባቸውም ።

“የስረኛ ፣ የግሥተኛ ወጉ ይሟላልኛ !”

ቴዎድሮስ ራሳቸውን ነቀንቁ ። ዐይናቸውን እንደ መቆጥቆጥ አደ ረጋቸው ። “ምነው ሁልጊዜ ክፋው ብቻ የሚታይሽ ? ክፉ ክፉውን ብቻ የምትናገሪ ?”

“እኔ ምናሰብኩት ። ከእስረኛ ጋራ አምባ የምጓዝ ተሆነ ፣ ማሰሪ ያው ለምን ይቀራል ብዬ ነው” አለች ጥሩ ወርቅ ፣ ላመል ትክሻዋን ሰበት አድርጋ ።

“ተዚህ ሥራችንን ስንጨርስ ሁላችንም እንመጣለን እያልኩሽ ! ተተጋዝነ ያው አብረን ነው ።”

“ዓለማየሁ ለምን ተኔ ጋር አይሔድም ዛዲያ ?” ስትል ፍርጥም አድ ርጋ ጠየቀች ።

“ትናንት ማታኮ ተነጋግረንበታል አሱን ፣ ጥሩ ። ተኔ ጋር ቆይቶ እንመጣለን ። ”

“ተዚህ ሁላ ምናለ አገሬ ብገባ ?”

“ታገርሽ አይደለም ያለሽው ? መላ ኢትዮጵያ አገርሽ ማይዶል ? ጮኮ ብቻ መመልከቱን ብንተወው ምናለበት?” አሉ ቴዎድሮስ በምክር ዐይነት ።

“እኔ የምፈልገው ባባቴ መቃብር ላይ እየጸለይኩ የቀረኝን ዕድሜ ለመጨረስ ነው ። ”

“ግዴለሽም የትም ሆነሽ ብትጸልይላቸው ይደርሳቸዋል”አሉና ቴዎድሮስ ፣ ‘ስሜንን ይዘሽ ልትሸፍችብኝ—’ሲሉ በሆዳቸው አሰቡ ።

“እንግዲያው እሺ ተልጂ ጋር ልሒድ” ስትል ጥሩ ወርቅ እንደገና ጠየቀች ።

“አብረን እንመጣለን ብዬሻለሁ ።”

“ምን ይሠራል ተዚህ ቀርቶ ?”

“ምናለ ባታደርቂኝ፡ጥሩ ? ወንድ ልጅ ታባቱ ጋር እይቀመጥም ?”

“ተናቱስ ጋር አይናርም ?” ድርቅ አለች ጥሩ ወርቅ ።

ቴዎድሮስ፡ትዕግሥታቸው እያለቀባቸው ሔደና፣ “ምን ሊግር ? አሉ ባልታ ? ነገር ? የለም አልፈቅድም” አሉ በቁጣ ።

የጥሩ ወርቅ የተለመደ አልሀም አብሮ ጠጠረ።" ተዚህስ ምን ሊግር?"

"ሌላው ቢቀር ፣ እኛን ለመግዛት የሚመኙት ፈረንጆች ኃይል ያገኙበት መሣሪያ ሲሠራ ቢመለከት ይሻለዋል ። ታሉባልታ " አሉ ቴዎድሮስ ፍርጥም አርገው ።

"እስቲ ልጁ ይጠየቅ አልሔድም ይል እንደሆነ ?" አለች ጥሩ ወርቅም በበኩሏ ፍርጥም ብላ ።

"የሚበጀውን እኔ ዐውቃለሁ ።"

"ልጇን ከናቱ የሚለዩት በግድ ነዋ?" አለች ጥሩ ወርቅ ፣ እንደ ግል ቀስም እንደ መጮህም እየቃጣት ።

ቴዎድሮስ ፣ በሠቀቀን ራሳቸውን ነቀነቁ ። ከንፈራቸውን እንደ ጦንከስ አደረጉ ። "ምን ሆነሽ ነው ከቶ እኔን ከፉ ለማሰኘት የምትጥሪው ጥሩ ወርቅ ? ምናለ ሐሳቤን ብትረጂልኝ ?" አሉ በምሬት። በድንገት ወደ ዓለማየሁ ዘወር ብለው፣ "እሺ፣ መሔድ ትፈልጋለህ? ተኔ ጋር መቆየት ?" ሲሉ ጠየቁት ።

ዓለማየሁ ፣ በጭንቀት አመለካከት ዐይኑን በሁለቱ መካከል ካንከራተተ በኋላ ፣ ለመቆየት መምረጡን በመግለጽ አኳኋን ወደ አባቱ ተጠጋ።

"ይኸው ?" አሉ ቴዎድሮስ የዓለማየሁን ራስ እያሻሹ ።

ጥሩ ወርቅ ፊቷን የባሰ በማጨፍገግ "ምን ቸገረኝ" አለችና ወደ በቅሎዋ አመራች ።

"ላማት እንጂ የኔ አካል !" አሉት ቴዎድሮስ ዓለማየሁን ።

መንገደኞቹ ጉዞ ሲጀምሩ ግን፣ ቴዎድሮስ ሁናቴውን የበለጠ ለማብረድ ሲሉ ሐሳባቸውን በመቀየር ፣ ከዓለማየሁ ጋር ሆነው የአንድ ሰዓት መንገድ ሸኙዋቸው ።

—3—

እንዲሔድ የታዘዘው ሠራዊት ተጠቃልሎ ወደ መቅደላ ወጣ። ኢትዮጵያውያን እስረኞችም በሙሉ ተላኩ ። የቀሩት ፣ ወደዚህም ወደዚያም በአፋጣኝ እንዲዘምቱ የሚደረጉት የጦር አበጋዞች ከተወሰነ ሠራዊት ጋር ፣ ለጋፋቱ ሥራ የሚያስፈልጉ ሰዎች ፣ ፈረንጆቹ እስረኞች ብቻ ነበሩ ።

መሻቹም፣ ጋለሞታውም፣ነጋዴውም እያደር ገበያ ሲያጣ በየ አግጣጫው ተበታተነ።የእስረኛ ስንቅ አቀባዮችም አንዳንዶቹ ወደ መቅደላ ዘለቁ ።

ሌሎቹ ፣ "እንግዲህ እንዳሻው እንጂ" እያሉ ወደ ትውልድ ሠፈራቸው አመሩ ። ደብረ ታቦር ከተማና ጋፋትን ጨምሮ አካባቢው በአጭር ጊዜ ውስጥ ጸጥታና እርጋታ ሰፈነበት ።

ቴዎድሮስ የፈለጉትም ይህንኑ ነበር ። በሐሜት ፣ በአሉባልታ፣ በወሬ፣ በመሸታ አምባጓሮና በሌላም የማይረባ ነገር ሁሉ ፣ ሐሳባቸው ሳይከፋፈልና በየዕለቱ ሳይበጠጥ የጋፋቱን ሥራ ለማከናወን ፋታ ሰጣቸው።

ከፈረንጆቹ እስረኞች ጋር ያላቸው ግንኙነትም ፣ ወደ ዕርቅ ወይም ወደ ስምምነት ባያዘነብልም ከበፊቱ ረገብ አለ ።

ሰንሰለቱ ወለቀላቸው ። ዘብ በዐይነ ቁራኛ እየተከተላቸው አንዳንድ ጊዜ ከታሰሩበት ግቢ እየወጡ እንዲዘዋወሩ ተፈቀደላቸው ። አንዳንዶቹን በተለይ ራሳምንና ካሜሮንን ቴዎድሮስ ወደ ጋፋት ይዘዋቸው ይሔዱና ሥራውን በማሳየት ምክርና እስተያየት ይጠይቃሉ ። ቅሬታቸውን አብረው መግለጽ ግን ቴዎድሮስ አልተዉም ። " ዛሬያ በዚህ ዐይነቱ ሥራ የበለጠ ሠልጥናችሁበታልና እርዱኝ ብላችሁ እምቢ አላችሁኝ ፣ ያፋርደና ! " ይላሉ ።

"እረ እምቢ አላልንም" ሲል ራሳም ይመልሳል ።

"በጊዜው ደርሶኝ ታልጠቀመኝ ያፍ ድለላው ምን ይረባኝና ። ባገሬ ላይ ክፉ ዐይናቸውን ለጣሉባት ጠላቶቼማ ፣ ይኸውና ተካይሮ እስተአሉ ። ወይ ነዶ !"

"በጊዜው ይደርሳል አባ ታጠቅ ።"

"መቸ ነው የሚደርሰው ? አገሬ ተተዋረደች በኋላ ? ጅብ ተሔደ ውሻ ጮኸ" አሉ ።

ሚስተር ራሳም ፣ ነገሩ እንዳይካረር በማለት ጭውውቱን ወደ ሌላ ጉዳይ ለማምራት ይሞክራል ። ቴዎድሮስ ግን፣መልሰው ወደዚያው ይስቡታል ።

"እዩ አቶ ራሳም ፣ ለምሳሌ፣ ያመጣህልኝ የሩቁን አቅርቦ ፣ ረቂቁን አጉልቶ የሚያሳየው መነጽር መልካም ነው ። ዛሬያ ፣ ዕውቀትና ኃይል ታላገኘሁ ጠላቴን በሩቁ ማየቱ ምን ይረባል ? ለዚህ ነው ያመጣህልኝ ? ወይስ አገርህ በጥበብ የደረሰችበትን እንዳደንቅበት ? ግዴለም ፣ ታሁን ቀደምም በሰው ርዳታ እንዳልኖርን ሁሉ አሁንም ራሳችን እንወጣ ዋለን" ይሉታል ። አነጋገራቸው ግን ፣ የቁጣ ኃይለ ቃል ሳይሆን፣ እንደ ተዳፈነ እሳት አንጀት አንጀታቸውን እያቃጠለ የሚወጣ ምሬት ነበር ።

ይህም ሁሉ ሲሆን ፣ ስለ ፈረንጆች እስረኞች ጉዳይ ቴዎድሮስ ከመጨረሻ ውሳኔ ላይ አልደረሱም ። ባንድ በኩል ከእንግሊዝ ጋር ጣቡ ገፍቶ የሚመጣ ከሆነ በማለት ሐሳባቸው ያተኮረው በመድፎቹ ሥራ ላይ ነበር ። በወይን ቁራኛ እየተጠበቁ እስከ ቆዩ ድረስ የእስረኞቹን ጉዳይ ምን ጊዜም ሊቆርጡት እንደሚችሉ ያውቁታል ። በሌላ በኩል ደግሞ፡ራሳምከሌሎች በተሻለ የአቀራረብ ችሎታው ዘወትር የሚነግሯቸውን እየሰሙ ምናልባት የሚጠብቁት መልካም መልዕክት እንደሚመጣ ቅንጣት ተስፋ ማሳደራቸው አልቀረም ።

ፈረንጆቹ እስረኞች በበኩላቸው ስለ ወደፊት ዕድላቸው ያስባሉ ። ይወያያሉ ። የሚያስደስተው መልካም መልእክት ድንገት ደርሶ ቴዎድሮስ በዕርቅና በሰላም ይለቃቸው ይሆን ? ወይስ ቁጣው ጽዋውን ሞልቶ ሲፈስስ ፣ አንድ ቀን ከዚህ ዓለም ያሰናብታቸው ይሆን ? የእንግሊዝ ጦር መጥቶ ያስለቅቃቸዋል ? ወይስ ከዚያ በፊት ቴዎድሮስ እልሁን ይወጣባቸዋል ? በተለይ አብዛኛው ሠራዊት፡ ኢትዮጵያውያን እስረኞችና ዋጋ ያለው ዕቃ ሁሉ ወደ መቅደላ ከተላኩ ወዲህ ፣ ፈረንጅ እስረኞችም አንድ ቀን ወደ መቅደላ እንዲወጡ መደረጋቸው እንደማይቀር በመገመት በጣም ሐሳብ ይዟቸው ፣ ምን እንደሚሻል ነጋ ጠባ ይወያዩበት ገቡ ።

ከመካከላቸው ሚስስ ሮዜንታል ብቻ የተለየ ሐሳብና ስሜት ታስ ታምግለች ።

ራሳም ፣ የእስተሳሰራቸውን ታሪክ እንደ ሰማ ፣ አለዝቦ መክሮ ሊያ ቀራርባቸው ቢሞክርም ፣ ሮዜንታል በፊት በስሜት እንዳልተዋሐደቻቸው ሁሉ ፣ አሁንም በአካል እንጂ በመንፈስ ልትተላቀል አልቻለችም ። በምክራቸው አትካፈልም ። በሚመካከሩበት ጊዜ እንደ አጋጣሚ በመ ካከላቸው ብትገኝም ፣ የምታስበው ስለ እስረኝነታቸው የጋራ ዕድል ላይ ሆን ስለ ራስዋ ብቻ ነው ።

ጥሩ ወርቅ ፣ መቅደላ ወጥተው ቴዎድሮስ ብቻቸውን መሆናቸው ፣ ታንጉት የምትባለው የገብርዬ ሚስት ታማ እየታከመች ጋፋት መቀመጥዋን ሮዜንታል ስትሰማ ፣ ደግሞ በብቸኛ ስሜቷ ላይ የተምታታና የተቀላቀለ ሐሳብ አደረባት ። መቅደላ አምባ መጋዙ ፣ እንደዚሁ ወደ አውሮፓ ከመሔድ የባሰ ሆኖ አልታያትም ። እንዲያውም የተመኘችውን የማታገኝ ከሆነ ፣ ሕይወትዋን በግዞት ማሳለፍ አንድ ሰም ያለው ሰማዕ ትነት መስሎ ተሰማት ። ከዚያ በፊት ግን፣ አንድ የመጨረሻ ዕድል ለመ ሞከር ፈለገች ።

ደብረ ብርሃን ሥላሴ መቃብር ቤት ለእስተርን እየነገረች ያጻፈችው ታንጉት የምትባለው የገብርዬ ሚስት ነበረች ። ቴዎድሮስ አሳድጓታል ሲባል ሮዜንታል ትሰማለች ። ታዲያ ስለ ቴዎድሮስ ከሌሎች የበለጠ ምስጢር በምን ዐወቀች ? ግንኙነታቸው ምንድን ነው ? ማወቁ እንደ

መላ ሊያስገኝላት የሚችል መሰላት ። በዚህ ላይ ቴዎድሮስ አብዛኛውን ጊዜ የሚያሳልፉት በጋፋት ነው። ጋፋት ሒዳ ለመሰንበት ቁርጣ ተነሣች።

አንድ ቀን ጧት ፣ አሞኛል ብላ ለቁርስ ሳትነሣ ቀረች ። ምላ ሳትበላ በዚያው ዋለች ። ራትም እምቢ አለች ። ሴሊቱን ከአንቅልፍዋ በነቃች ቁጥር እያቃሰተች አደረች ። በበነጋው የባሰባት መሰለች ። ሚስተር ራሳ ምና ቆንስል ካሜሮን ደባብሰው አዩዋት ። ከማቃሰትዋ በስተቀር ትኩ ሳት የለባትም ። ግን ሁለቱን ቀን ከንጹሕ ውሃ በስተቀር እህል በአፍዋ አልዞረም ። መቸም ሰው በጤናው እህል ሰለማያስጣላው ሥጋት ገባቸው ። በሦስተኛዉ ቀን ፣ ከረሃብ ድካምና ጥውለጋ ጋር ፣ ዐይ ንዋን ስልምልም ፣ ሰውነቱዋን ዝልፍልፍ ስታረግባቸው እንደ መደና ገጥ አሉ ። ‘‘እ . . . እ . . . እባካችሁ ጋ . . . ጋፋት ከዶክተር ብ - ብላንክ ዘንዳ . . .’’ ስትል በሚያቃስት ድምፅ ተማጠነች ።

ራሳም፡ ለምኖ ቴዎድሮስን አስፈቀደና ሮዜንታል በቃሬዛ ወደ ጋፋት ተወስዳ ፣ ሰፋ ሰፋ ያሉ ክፍሎች ባሉት በሚስተር ዋልድሜየር ቤት በማረፍ ሕክምናዋን ቀጠለች ።

የጋፋት የብረት ማቅለጫዉ የተተከለው ከወንዙ ጻር ሲሆን ፣ መኖ ሪያ ቤቶቹ የተሠሩት ደግሞ ከጻንቱ አፋፍ በእንድነት ክምችት ብለው ነው ። ጉጡ ዙሪያውን በግንብ ታጥሮ አንድ ትልቅ ግቢ ሆንዋል ። ከዚህ ግቢ የሚኖረው ሁሉ ሳይገናኝ ስለማይውል ፣ ሮዜንታል ከታንጉት ጋር ለመገናኘት ብዙ ቀን አልፈጀባትም ። የፈለገችውም ይኸንኑ ነበር ።

ታንጉት ፣ ሕመምዋ ተሽልዋት ፣ ሰውነትዋ ጠንክሮ ወደ መቅደላ እስክትሔድ ፣ ለቴዎድሮስ ምግብ በማበሳሰል እየረዳች ከቤት ወጣ ገባ ማለት ጀምራ ነበር ።

ዶክተር ብላንክ ፣ የበሽታዋን ዐይነት ለይቶ ባይደርስበትም ፣ ሮዜን ታል እንደ መጣች ማምሻዋን እህል ቀመሰች ። በበነጋው ከአልጋ ተነ ሣች ። በሁለተኛው ቀን ከቤት ወጣች ። በዚሁ ቀን ቴዎድሮስና የጋፋት ባለሙያዎች በአንድነት ምሳ ከሚበሉበት ፣ ከግቢው መኻል ከሚገኘው የድንጋይ ቤት ውስጥ ታንጉትና ወንጌለን ምግብ ሲያስናዱ አገኘቻቸው። ከዚያው በተቻለ መጠን ታንጉትን አልለያት አለች ።

ሮዜንታል ፣ ምኞቷና ስሜቷ ብቻ እየገፋፋት ፣ ነገሩን እንዴት እንደ ምታዉጣጣ ፣ ወይም የምትፈልገውን እንዴት በእርጋታ እንደምታገኝ አላወቀችበትም ። ነገር ፍለጋ የመጣች ይመስል ከሥር - ከሥርዋ እየ ተከታተለች ታነበንባለች ። ቴዎድሮስን የትና ሙች ተዋወቅሽው ? ዝም ድና አላችሁ እንዴ ? ጠባዩን በቅርብ ታውቂዋለሽ ? ምን ይወዳል ? ምን ይጠላል ? ታሁኑዋ ሚስቱ ጋር እንዴት ነው ? ለምን መቅደላ ላካት? ዛዲያ ካለሲት ብቻውን ይኖራል ? እንዳንዱ ጥያቄ ታንጉትን ያሥቃታል።

እንዳንድ ጊዜ መልስ እየሰጠች ፣ አብዛኛውን ግን በአንድ ጆሮዋ የገባውን በሌላው እንደምታፈስሰው ያህል ችላ ብላ ሥራዋን ትቀጥላለች። ብዙ ጊዜ ሁለቱም በመገረም ይመለከቱዋታል ።

ሮዜንታል ፣ በሁኔቷቸው እየበሽቀች ስትሔድ ፣ ጥያቄ ማነብነቡን ትታ ወደ እሽሙርና ሽሙጥ ገባች። ስለ ሐበሻ ሕዝብ ክፋት፣ ስለ ቴዎድሮስ ጭካኔ፣ ስለ ጦር አበጋዞቹ ትዕቢት፣ስለ ጋፋት ፈረንጆች ክዳት የሰማችውን ፣ የተሰማትን ፣ ሐሜትና አሉባልታ ታወርድ ጀመር ። በስሜት ግፊት እንጂ የምትናገረውን እያሰበች አልነበረም ። ታንጉትና ወንጌለ ቋት እስኪላቸው ድረስ ታግሠዋት ቆዩ ።

ተሲዓት ሲታረብ ፣ “ ወይዘሮ ሮዜንታል ፣ በይ እንግዲህ ቤት ሔደሽ ብትቆይ ይሻላል” አለቻት ወንጌለ ።

“ለምን ?” ስትል ሮዜንታል በቁጣ መልክ ጠየቀች ።

“እኔ አባ ታጠቅ ለምሳ መምጫቸው ደርሷል ” በማለት ታንጉት ለጠቅ አደረገች ።

“ቢመጡስ ?”

“ተዚህ መቆየት አይፈቀድልሽማ !” አለቻት ወንጌለ ።

“እናንተ ትቆዩ የለም ?” ሮዜንታል በማሽጓጠጥ ከንፈርዋን አጣመመች ።

“እኛ ባለሟል ሠራተኞች ነን ። አንቺ ለሕክምና ተፈቅዶልሽ ብት መጭም እስረኛ መሆንሽን አትርሽ” አለች ወንጌለ ፣ ፍርጥም ባለ እነጋገር ።

ሮዜንታል ፣ ከአጠገባቸው ለመገኘት የነበራት ፍላጐት በመታገዱ ብቻ ሳይታወቃት ንዴትዋ ወደ ቴዎድሮስ ተሸጋገረ ። “እሀ እስረኛ ! እረ አንድ ደንቆሮ ጥቁር እንዴት ቢደፍር ነው፣ነጭ አውሮፓውያን የሚያስረው ! ነገ ዋጋውን ያገኝ የለ !” አለች ።

“ጥቁርም ቢሆን ሰው ነው ። ከአጠፋችሁ በሥልጣኑ ሊያስራችሁ የማይችልበት ምህኛት የለም ። በዕውቀት በኩልም ተሆነ ተማንኛች ሁም ቢበልጥ እንጂ አያንስም” ስትል ወንጌለ መለሰችላት ።

“ነጭና ጥቁር እኩል ሰዎች ! ጥቁር ተነጭ እኩል ቢሆን ነው ፣ እኝ ግሊዝ ፣ ፈረንሣይ ፣ ፖርቱጋል ፣የአፍሪካንና የእስያን ሕዝቦች ረግጠው ፣ ቀጥቅጠው የሚገዙት በይኛ ! ” ሮዜንታል ፣ በየጉድባው ኢትዮጵያዊ ወንድ ያላንከባለላት ይመስል ፣ የመኳንንቱን ገላ በሕልሟ ያልዳሰሰችውን ያህል ፣ ግግኘት ያልቻለችውን ፣ አውን በማጥላላት ፈዝ ክት ክት ብላ ጣቀች ።

“ያቅም ጉዳይ ነው እንጂ ሁሉም ያዳም ዘር ነው” አለቻት ወንጌለ አውንም ፍርጥም አድርጋ ።

“ውይ ረስቸ አንቺም ለካ አለሽበት ። ዛሊያ ምን ታረጊ ? ራስሽን አታጣጥይው መቸስ ። ክፋቱ ተዚህም ተዚያም አለመሆንሽ ነው ።”

“እኔ ባባቴም በናቴም አላፍርም ።”

“ብታፍሪበትስ ምን ታረጊው ኖሩዋል ። መርጠሽ ፣ ፈልገሽ አልተረገዥ ። ለመሆኑ ወፍጮ ላይ ነው ?”

ታንጉት፣ የራስዋ እናት ዲታላነት ትወላ ስሜቷን ነዝሮት ይሆናል። ወይም ደግሞ ፣ ሮዜንታል ከአጓጉል ጥያቄ ጀምሮ ያለማቋረጥ ስታወር ደው የቆየችው የስድብና የሽሙጥ መዓት፣ የትዕግሥት ጽዋዋን ሞልቶባት ይሆናል። የሁለቱን ምልልስ ስትከታተል እንደ ቆየች ሮዜንታልን አላስ ጨረሰቻትም። በጥፊ ስታጉናት ሮዜንታል የጓሊት ተፈናጥራ ከግድግዳው ጋር ተላተመች። ከዚያም እላት ድንገት እንደ ገረፋት ያህል፣ፊቷን በሁ ለት እጅዋ በመሸፈን ለጥቂት ጊዜ እንደ በድን ደርቃ ቆየች። ታንጉትም፣ ወንጌለም ካሉበት አልተንቀሳቀሱም ።

“ለርሷ አግዘሽ ነው ?” ስትል ሮዜንታል ጠየቀች ፣ ፊቷን አውንም እያሻሸች እንደ ጣዕር በሚመስል ድምፅ ።

“ይኸ ምላስሽ ገና ተሌላ ያደርስሻል !” አለች ታንጉት ።

“ዋ ! እኔ እሻልሽ ነበር !” በማለት ሮዜንታል ዛተች ።

“ምን ?” ታንጉት ወይንዋን እያጉረጠረጠች ተጠጋቻት ።

“ልንገርሽ ?” አለች ሮዜንታል ወንጌለ እንድትሰማው የግትፈል ገው ይመስል በሹክሹክታ ፣“እየሽ ፣ ሚስተር እስተርን ባይናገርምኮ የደ ብረ ብርሃን ሥላሴውን መታብር ቤት ጉድ እኔም ዐውቀዋለሁ። ዝም ብዬ ነው እንጂ ! ! ”

ታንጉት ነፍስዋን አላወቀችም ። ለቅጽበት ተወርውራ ሥጋ ስት ከትፍበት የነበረውን ካራ መዝዛ ሔደችባት ። የቴዎድሮስ ቁጣ የሚወ ርድባት ከሆነ፣ሌላው ጉድ ሳይወጣ በነፍስ ገዳይነት ብትቀጣ ይሻላታል። እስተርን የማይናገር ከሆነ ለወንጌለ አብራ ገደለቻት ነው የሚባለው ።

ሮዜንታል ፣ ወደ አንድ በኩል በመፈናጠር የመጀመሪያውን አም ልጣ ፣ ታንጉት ለሁለተኛ ጊዜ እጅዋን ዘርግታ ስትሰነዝርና ወንጌለ ለመገላገል መኻል ስትገባ አንድ ሆነ ።

የወንጌለ ጩኸት በግቢው ሲያስተጋባ ፣ መጀመሪያ ከደረሱት መካ ከል አንዱ ዶክተር ብላንክ ነበር ። በእስቸኳይ የሕክምና ሥራውን ጀመረ ።

ቴዎድሮስ ከብረት ማትለጫው ምድጃ አጠገብ ወዲያ ወዲህ እያሉ ሥራውን በመከታተል ጊት ፣ ከደብረ ታቦር ይዘዋቸው የመጡትን ሚስ ተር ራሳምንና ቆንስል ካሜሮንንም በማላየት ላይ እንዳሉ የአደጋው መል ክት ደረሳቸው ። ከግቢው ሲደርሱ ከዋልድሜየር ቤት በራፍ በርክት ያሉ ሰዎች ተከማችተው አገኙ ። ከእንድ በኩል ቤቶቹ " የጋፋት ልጆች" ደፍልሚያ የተፋጠጡ ይመስል ተከማችተው ቆመዋል ።

ቴዎድሮስ ፣ ውስየ ገቡና ዶክተር ብላንክ ሕክምናውን እስኪጨርስ እየተንቀራጠሙ ወጡቁት ። " ተክንድዋ ላይ መሆኑ በጀ ። ደረቷን አልነ ካውም ። ይቶሎ የሚድን ነው " እሉ ዶክተር ብላንክ ፣ እስኪጨርስ ሕክምና ሠሚድረግ ሻሹን እስር ሲጨርስ ። ውናቴያቸውን እይቶ ሰሚታ ይል መሆኑ ነበር ። እንዲመጣ በእጃቸው አመለክቱት ።

ቴዎድሮስ፣ ከአልጋው ጠርዝ ላይ ተቀመጡና ፣ " ምንድን ነው ሶሆ ነው ወንጌል ?" ሲሉ ጠየቁት ።

ሮዜንታል፣ ከምግብ ቤቱ መጥታ ፣ በሆነ ባልሆነ ነገር ስትጨቀጭ ቃቸው ፣ ያንንም ያንንም ስታማ ማርፈድዋን ፣ ከዚያም እርሷን ከወፍጮ ላይ የተፈጠርሽ ነሽ ብላ፣ ስትሰድባት ፣ ታንጉት በጥፊ የመታቻት መሆ ኑን ከተረከችላቸው በኋላ ፣ " ሮዜንታል ምን እንዳለቻት አላውቅም፣ ታንጉት በካራው ልትወጋት ስትል ፣ ልገላግል ገባውና ፣ ግን ታንጉት ዐውቃ አይደለም" ስትል ጨረሰች ።

ቴዎድሮስ፣ ከጐጆው እንደ ወጡ እሳት የጉረስ፣ እሳት የለበሰ ዐይ ናቸው በቆንስል ካሜሮንና በሚስተር ራሳም ላይ አፈጠጠ ። ቀጥሎ ፣ ወደ ታንጉትና ወደ ሮዜንታል ተወረወረ ።

ታንጉት ፣ እጆቿን ከደረትዋ ላይ አጣፍታ ከወደ ዳር በመቆም፣ ሮዜ ንታል ምሥጢርዋን አውጥታ ቅጣቱ አስኪወርድባት ተስፋ ቆርጣ ትጠብቃለች ።

ሮዜንታል፣ ፈንጠር ብላ ከድንጋይ ላይ ያርቃ ተቀምጣለች ። እንደ ሰውነቷ ፣ አስተሳሰቧም በድንጋጤ ያርቆባት ነበር ። ካራው ከፊቷ ላይ ብልጭ ሲል የታያት የሞት ትርዒት አሁንም ሁለመናዋን እንዳፈዘዘው ፣ እንደ ቀሰፈው ነው። ከሞት ፍርሃት ጋር ስትጋፈጥ የመጀመሪያ ጊዜዋ ነበር ። አሁንም አሁንም እንደ ማንቀጥቀጥ ይላታል ። በምላስዋ የምትመኘውን ለማግኘት ስትሞክር ፣ ከናካቴው ሕይወትዋን ልታጣ እንደ ነበር ድንጋጤዋና ፍርሃትዋ ብልጭ አድርጐ አሳያት። ምኞት ሊደ ርስ የሚችለው ደግሞ በሕይወት ሲኖሩ ነው ። አሁንም የቴዎድሮስን በቁጣ የሚነድ ፊት ስትመለከት ፣ የምታውቀውን ብትናገር ምን እንደ ሚያስከትልባት መገመት ስላልቻለች ፈራች ። ተሸማቀቀች ።

በስፈነው ውዋረት መካከል ሚስተር ራሳም ከተሰመደ የእክብሮት ለገላለጹ ጋር፣ " መቸም አባ ታጠቅ ፣ እንደሚያውቁት የዕለት ጥሮት በወዳጆችም መካከል ቢሆን" እያለ ለማብረድ ቃጣ ።

" ቢቅ!" አሉት ቴዎድሮስ እንደ ነጐድጓድ በሚያስተጋባ ድምፅ ። እኒገራቸው ለእርሱ ብቻ ላይሆን ደብረ ታቦር ለቀሩት እስረኞች፣ ጥረ ታቸውን ላልተረዱት የላሕር ማዶ ሰዎች ሁሉ ጭምር ነበር ። " ቢቃች ሁን እንጂ ! ወዳጅነቴን ብትንቁት ቻልኩ።አሁን ደሞ የቀረኝን አንድ ሥራ ሌታዘቡኝ ተነጣችሁ ?"

ዶክተር ብላንክ እንዳልውሎወንጌል ጉዳት ቀላል ቢሆን ፣ በጉዳት ልጁትና በእስረኞች መካከል የቆየውን መቃቃር የበለጠ እክብርት ከሚ ሰጠበት ደረጃ መድረሱ በግልጽ ያዚታውቅ ነበር ።

" ድብረ ታቦር ያሉትን ጨሥራችው ቸንክሩና መቅደላ ውስጡኝ፣ እውነት " ሲሉ እጅጉ ወዲያው ረገብ ባለ እንደዘት፡ " እትሞሙኝ እቶ ራሳም ። ተኔ ጥፋት የለም ፣ የተቻልኝን ያህል ችያለው" አሉት ።

ራሳም ለመግታት ቢጉሽመውም፣ ቆንስል ካሜርን ቲመናነር በዚ ነቱን ወደራት አስቀደመ ።" የማይቋጫውትን ኃይል መጋፋት ብልህነት አይመስለኝም ።"

" ግደ.ለህም ፣ የደንቆር ጅልነት ነው ። ግን ደሞ ፂቾና ጉራ የአብ ራተኛ ብቻ ነው ። አደምለህ ።" አሁን - አሁን የካሜርን ትዕቢት ከሚ ያስቆጣቸው ይልቅ ፣ ሳይታረም እንዳደገ ጉረምሳ ብልግና የሚያከርግ ቹው እየሆነ ሔድዋል ።

" ባዶ ዛቻ አይደለም ። የታላቅዋ ብሪታንያ ኃይል ከአጥናፍ አጥ ናፍ ተዘርግቶ የሚገኝ ግልጽ ሐቅ ነው ። ይህንን መካድ አይቻልም ።"

" ዛዲያ ይሁና ! ማን ይፈራል ብለህ ነው ? እኔ መይሳው ? አል ሰማህም ፣ ትንሹ ዳዊት ጉልያድን በወንጭፍ እንዳሸነፈው ? ምናለበት ታንቱ የበለጠ ታሪክ ባላውቅም ፣ ትልቅ ነኝ ብሎ የተመካ ሁሉ ፣ ትልቅ ሆኖ እንደማይቀር ባለም ላይ የደረሰ ብዙ አለ ። እናንተሳ ሮማውያን ገዝተዋችሁ አልነበረም ? እነሱ ደክሙ ፣ አሁን ደሞ በፈንታችው እናንተ እንርገጥ ትላላችሁ ። ግሪክም በዘመንዋ እስተ ሕንድ ደርሳ ነበር። ዛሬ ደሞ ቱርክ ሊ"ጫወትባት ደርሷል ። እና ትልቅ ነኝ ብሎ መደንፋቱ ዋጋ የለውም ፣ ወዳጄ !" ቴዎድሮስ ባለ ጉዳዩን በማሰናበት እንደ መራመድ ሲሉ አሁንም ቆንስል ካሜሮን ቀበል አደረገ ።

" ግንኩ መታዩት ያለበት ያለፈ ታሪክ ሳይሆን ፣ የዛሬው የኃይል ሁኔታ ነው ። ይህ ነው ሐቁ !" አለ ግትር ብሎ ።

‘ የዛሬ የኃይል ’ በምትለው አላምንም ብየሃለሁ ። እኩልነት ያኔ ነጻነትና ዕድገት ፣ ይህንን ነው እኔ የማምነው ። ውሰዱልኝ እባካችሁ ! ነገር ታክቶኛል።’’ቴዎድሮስ ጠቋሚ ጣታቸውን ወደ ታንጉት በማመልከት ፣ ‘‘ካራ መማዘዝ ተጀመርሽ በርትተሻልና እንግዲህ አንቺም መቅደላሽን ውጭ ’’ ካሉበኋላ ፣ ወደ ብረት ማቅለጫው ለመመለስ በሮዜንታል አጠገብ ሲያልፉጸጥ ባለው አካባቢ አንድ ድምፅ ሰሙና ዘወር አሉ ። ሮዜንታል ምራቋን ጢቅ ያለችበትን አፍዋን እንዳሞጠሞጠች ዐይናቸው ያዛት ። በመጠየፍ ፊታቸውን ጨፍግገው ፣ ‘‘ባለጌ ! ይሽ ኑሮዋል ሥልጣኔያችሁ !’’ ብለው ሌላ ቃል ሳይጨምሩ መንገዳቸውን ቀጠሉ ።

በንዴት መልክ ወንድ በጥፊ ተማትተው ፣ ክንዳቸውን ጨበጥ ሲያደርጉዋቸው ከደረት ላይ ወከክ እንደሚሉት የሀገርዋ ሴቶች ልማድ፣ ሮዜንታል ጨርሶ በታወከና በተበጠበጠ ስሜታ፣ለመጨረሻ ጊዜ አስተ ያዬታቸውን ለመሳብ ሳይታወቃት ያደረገችው ነበር ። ስሕተትዋ እንደ ገባት፣‘‘ ቴ- ቴዎድ’’ እንደ መጣራት ቃጣት ። ያስጨረሳት አልነበረም ። ወታደሮቹ ለጉዞ ወዲያው ሲያጣድፉዋቸው ዕንባ ዐይንዋን ሽፍን አደረገው ።

ጓዙ ሁሉ ተጭኖ ፣ ታንጉት ከከብት ላይ ከመውጣትዋ በፊት ገብርዬን ለመሰናበት ጉንጭዋን ሲስማት፣ ከአንገቱ ላይ ተጠምጥማ ተንሰቀሰቀች ። ስንት ዘመቻ ሲሔድ ፣ ስንት ጊዜ ሲለያዩ እንደዚህ ስትሆን አይታት አያውቅም ።

“ምነው ሆድ ባሰሽ ? እኛም በቅርብ መምጣታችን አይቀር ። የሚያስፈልግሽ ነገር ሲኖር ሰው ላኪ” አላት ።

“እኔ ፈራሁ ገብርዬ” አለችው ከአንገቱ ላይ እንደ ተጠመጠመች ።

“ምን አስፈራሽ ?”

“እኔ እንጃ !”

“ፈረንጆቹ አንድ ነገር እንዳያደርጉሽ ብለሽ ነው ? በሮዜንታል ምህኖት! ግዴለሽም አይዞሽ ። እነሱ የሚታሰሩት ለብቻቸው ። እናንተ የምትኖሩት ሌላ ሥፍራ ። ምን አገናኝታችሁ ። ደሞ ስንት የኛ ሠራዊት እያለ ?” ሲል የፍርሃቷን ምንጭ ያወቀ በመሰለው መንገድ አበረታታት ።

ታንጉት ፣ እንደ ምንም ከአንገቱ ተላቅቃ እንባዋን እየጠራረገች ጭንቀቷን በቀልድ ለማመቅ፣ “እናንተ ግን ዋ” ስትል አስጠነቀቀች ።

“ለምኑ ?”

“ሚስቶቻችሁን ሁላ ልካችሁ የምትሠሩት ምን ይታወቃል ?” አለች የሚተናነቃትን ለቅሶ ከቀልድ ጣቅ ጋር ቀላቅላ ።

“ቤት እንደ ሽክላ ጠፍጥፈን እንዳንሠራ ነው ? ወይስ እንደ መናከሰማይ ይወርድልናል ብለሽ ?” ሲል መለሰላት ።

ወደ መቅደላ ከሚወስደው ዋና መንገድ እስኪገቡ ድረስ ገብርዬ ቁጭ በወይኑ ተከተላቸው ። ካለወትሮዋ የተሰማት ሞንቀት ፣ ሥጋት አሳድሮበትም ይሁን እንጃ እርሱንም ቀፍፎት ነበር ።

— 4 —

ወራጅ ወንዝ ፣ በመስክ ፣ በሸለቆ በቁልቁለት ፣ በገደል ፣ የተለያዩ ሕይት እንዳለው ሁሉ ሕይወት በመቅደላ በተለያየ መልክ ይንቀሳቀሳል ። ጊዜ ፣ ለአንዳንዱ ረጋ ብሎ ለሌላው ነውጥ ሆኖ ፣ አንዳንዱን እንሳፍፎ ሌላውን አስጨንቆ ይፈስሳል ።

በመቅደላ አምባ ላይ ብዙ ዐይነት ነዋሪዎች አሉ ። ሠፈራቸውም እንደ ዐይነታቸው የተለያየ ነው ። ከአምባው አናት መኻል ላይ የቴዎድሮስ ዋናው ማረፊያ ቤት ፣ ዕቃ ቤት ፣ የእህል ጉተራዎች አሉበት ። በእነዚህ ዙሪያ ጠባቂዎች የሚኖሩባቸው ጎጆዎች ተንጠባጥበዋል ። ትንሽ ፈቀቅ ብሎ ከዳፋታው ገብታ ላይ የአምባው አዛዥ ግቢና የሠራተኞች መኖሪያ መንደር ይገኛል ። ከዚህ መንደር በስተምሥራቅ ከአምባው ልሙጥ ገደል በኩል ፣ በአሻገር ከተንታ አሮሞች ጉዋ ትይዩ የእስረኞች ሰፈር ነው ። በውስጥ በርከት ያሉ ቤቶች የሚገኙበት እጅን ዳንዱ ግቢ በጨፈቃና በእሾህ ጥቅጥቅ ብሎ የታጠረ ሲሆን፣ ከየአጥሩ ውጭ የተረኛው ዘብ ጎጆ አለ ። በስተደቡብ የስላምጌ መስክ ፣ ወደ በሽሎና ወደ ጀንዳ ሸለቆ መረማመጃ መደብ መስሎ ተዘርግቷል ። ቀደም ሲል በዚያው ከነበሩት ባላገሮች በስተቀር የእስረኞች ቤተ ሰቦችና እሽከሮች ፣ በኋላም ከደብረ ታቦር እንዲመጡ የተደረጉት ወታደሮች እያረሱ ፣ ከብት እያረቡ ወይም ቀለብ እየተሰፈረላቸው የሚኖሩት በስላምጌ ስለሆነ፣ችዎችም ያሉ መንደሮችና የተበታተኑ ጉጆዎች በብዛት ይገኙበታል ።

ጠቅላላው የመቅደላ አምባ ክልል መውጫና መግቢያ ኬላዎች ቤታመኑ ወታደሮች ሌት ተቀን ይጠበቃል ። የቀረው ሰዉንጂር ሰንኳ የሚያሳግት ገደልማ ስለሆነ ጠባቂ አያስፈልገውም ነበር ።

በዚህ ክልል ውስጥ እያንዳንዱ ነዋሪ፣ እንደ ሕይወት ዕጣ ፈንታው የየዕለት ውሎውን ይገፋል ።

ለእስረኛውጪት መዝዒያ ሲከፈትለት ወጥቶ መናፈስ ፣ አቅራቢ ካለው ስንቁን ተቀብሎ ፣ ከሌለው በባዶ ሆዱ፣ ምናልባት ድንገት ከሰ ሚወርድለት ምሕረት በተስፋ ወይም ስለሚመጣበት የመጨረሻ ቅጣት በጭንቀት እያለመ መዋል ነው ።

ለንውረኛው ዘብ ፣ ስንቅ ቆመካፈል ፣ የመግለጫ ጥቅም የመቀበል ፣ እንዲያም ሲል የእስረኛ ሚስት ወይም ሌላ ቤት የማግኘት ዕድል ነው።

ለሐቀኛው ዘብ ፣ የጥበቃ ተግባሩን በሚገባ ሲፈጽም ከመዋሉ ሌላ፣ ሆዳባሻው ፣ ተስፋ ከመቁረጡ የተንሣ ነካ ያደረገውንና ሌላውንም እሰ ረኛ ሁሉ እንደ ወዳጅ ፣ እንደ ንስሐ አባት የማጽናናት ጥረት ነው ።

ለእምባው ነባር ገበሬ ፣ ከበሬው ጋር ማንጉራጉር ፣ ከሞረር ጋር መታገል ፣ ላቡን ከጥቁር ዐፈር ጋር እያዋሐዱ ቸር ቀን እንዲመጣ ከመመ ኘቱ ጋር ግምሻውን ቤቱ ሲመለስ ፣ በባለጌ ወታደር ሚስቱ ተደፍራ ፣ ጉተራው ተሟጦ እንዳይጠብቀው መሥዕት ነው ።

ከባሎቻቸው ተለይተው ለመጡት እንደ ታንጉት ሳሉት ሴቶች ደግሞ ፣ ከእንድ ቤት ሌላ ቤት ፣ እየተገናኙ ማውጋት ፣ መገባበዝ ፣ ግግት፣ በየራስ ቤት መፍተል ፣ መስፋት ፣ እንዲያም ሲል ልብ ከፈቀደው ወታ ደር ወይም ሎሌ ጋር የተፈጥሮ ፍላጉትን በስርቆት መወጣት ነው ።

እነዚህ ሁሉ የእምባው ነዋሪዎች የጋራ ሕይወት ደግሞ አላቸው። እስረኛም ይሁን ባላገር ፣ ወታደርም ይሁን የመኮንን ሚስት ፣ ከመልክ ተኛ በስተቀር የውጭው እንደግይገባ ሁሉ፣ እንደ ፈለጉ ከክልሉ መው ጣት እይችሉም ። እስረኞችም ከየግቢያቸው ብት አይሉም ። ታማሻቹ ዘበኞች ፣ ከጥበቃ ከሌቸው እምብዛም ርቀው አይሔዱም ። ለሌሎቹ ነዋሪዎችም ከእንዱ ጉብታ ላይ ከተተከለው ከሥላሴ ቤተ ክርስቲያን፣ ከዚህ ደብር በታች ቅዳሚ ቅዳሚ ከሚውለው ገበያ በስተቀር የተለያዩ ትን ሠራተኞች የሚያገናኝ ማኅበራዊ መድረክ አልነበረም ። በእንድ ዐይነት አጋጣሚ ዘልሎ ወይም ተጠልፎ ፣ ከእንዱ ወደ ሌላው ከሚገ ባው በስተቀር የእያንዳንዱ ኑሮ የሚታቀበው በተከለለለት ሰፈር ውስጥ ብቻ ነው ።

ምኒልክ ከከዳ ፣ ወርቂትና የጦር አለቆቿ አምባውን ለመያዝ የተደጋገመ ሙከራ ከአደረጉ ፣ የቴዎድሮስን የአንዲት ኢትዮጵያና የአንድ መንግሥት ሥልጣን የሚታወሙት እየበረቱና እያየሉ ከሔዱ ወዲህ ደግሞ፣ በአምባው ውስጥ ለመዘዋወርም ሆነ ከልሉን ለማለፍ ጥበ ቃውና ቁጥጥሩ በጣም እየጠነከረ ሔዱ ነበር ።

የእንቅስቃሴ ግድብ ባለበት በዚህ መካከል ግን ወሬዎች እንደ ነፋስ ይዛመታሉ ። አምባውን ያጸረሳሉ ፣ ከአንዱ ጉጅ ውስጥ የሆነውን ከመቅጽበት መላው ሠፈር ይሰማዋል ። የአንዱ ሠፈር ዜና ፣ ከፈረሰኛ

በሚያስንቅ ፍጥነት ከወዲያኛው ግዱ ሠፈር ደርሶ ይገኛል ። ከአምባው ውስጥ የሚወጣው ብቻ ሳይሆን፣ከአምባው ክልል ውጭ የሚመጣውም እንደዚሁ ነው ። ኪሳ እያግደውም ፣ የመንገድ ርቀት እያዘገየውም ።

ቴዎድሮስ፣ ጋፋት ሳይና በአካባቢው የሚሠሩትና የሚሆኑት ሁሉ በየቀኑ ይመጣል ። ይደርሳል ። የእንግሊዝ ጦር ሲመጣ ነው ፣ ምኒ ልክ እንኮበር ገብቶ ኃይሉን ያጠናክራል ፣ በዝብዝ ካሣ እየበረታ መጥ ቷል ፣ ጣሰው ጉበዜ በወርቂት ላይ አይሳል ፣ ዳሞት ጨርሶ ለይቶለታል ፣ ወሬ ያለ ማቋረጥ ያጉርፋል ። መብረቅ እንደሚያወርደው ፣ ነጉድጓድ እንደሚያንጉዳጉደው ፣ የነፋስ ሠረገላ እንደሚሽከመው ፣ በአንድ ዐይ ነት ሥውር ኃይል የሚንቀሳቀስ ነው የሚመስለው ።

ግን ይህ ሁሉ፣ ሥውር ኃይል አልነበረበትም ። የውጭ አገር እስረ ኞች በተለይም የቆንስል ካሜርንና የራሳም ሥራ ውጤት ነው ። ከመ ገን ተለይተው ፣ ከአገራቸው ርቀው በባዕድ ሕዝብ መካከል በእስር ላይ የሚገኙት የውጭ አገር ሰዎች ፣ መልእክት የሚያስተላልፉበት ፣ ወሬ የሚያገኙበት አውታር አበጅተው ነበር ። 'ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል' እንደሚባለው ፣ ፈጣን የወሬ ቅብብሎሽ ወዶ ቀረው እምባው ነዋሪም ተጋባ ።

የወሬ ዘመቻውን ፈጣንነት የሚጠቀምበት እንዳለ ሁሉ የሚጉዳ በትም አለ ። የእምባው ምክትል አዛዥ ለመሞት የበቃው በወሬ ጠንቅ ነበር ።

በመቅደላና በአካባቢው እንደ ሽፍታውና እንደ ወንበዴው ሁሉ፣በዘ መኑ፣ጅብ በጣም በርክቶና አስቸግሮ ነበር ። የጅብ መንጋ በመስከረሚ እያቸነፈ ፣ በረት እየሰበረ ፣ ከብት ከመናጀት ዐልፎ ቤት እየገባ በሰውም ላይ ጉዳት ማድረስ ስለ ጀመረ ፣ ሁሉም ቤቱን በመቀርቀሪያ ክሮችም አድርጎ እየዘጋ ነበር የሚያድረው ።

ከወንድነቱ ይልቅ በትዕቢቱ ፣ ከአስተዳደር ችሎታው ይልቅ በጨ ካኝነቱ ፣ ከመስጠቱ ይልቅ በመንጠቁ የሚታወቀው የእምባው ምክትል ዙም የቀኛዝማች ቢሠውር ቤት አንድ ቀን በሚገባ ሳይዘጋ ቀርቶ ይሁን አይታወቅም ፣ ሴሊት ባልና ሚስቱ እንደተኙ ፣ ሕይወት ያለው ሽክም ተጫነባቸው ። ብሩክታንትን ከአርዊ እንዳዳነው ጊድርጊስ ፣ በወንድ ነቱ የተማመነችው ሚስቱ ቀስ አድርጋ ጉንተል አደረገችው ። እጅሬ ቢሠ ውር ግን፣እንቅልፍ የወሰደው ይመስል ትንሩሹን ውጠ ዝም አለ ። ደግግ ጉነተሰችው።ስንኳን ፈክሮ ከእውሬ ጋር ሊተናነቅላት ቀርቶ እንዱ በድን ደርቆ ቀረ ። ለሦስተኛ ጊዜ በጉንተላ ልትቀሰቅሰው ስትሞክር፣ መልሶ ልግዛግ አደረጋትና ከሸረራት ሐር በቀጠነ ድምፅ፣ "ዝም ብልሽ ተኝ" አላት ።

ባልና ሚስቱ፣ በሴሊት ልብሳቸው እንደ ተሸፈኑ ከሥር አድፍጠው ሕይወት ያለው ግዙፍ ሽክም ከላያቸው ላይ እየተገላበጠባቸው ፣ መጻና በሚመስል ነገር እየደባበሳቸው ፣ በዐይናቸው እንቅልፍ ዝር ሳይል ጉህ ቀደደ ። የንጋት ብርሃን በግድግዳው ፣ በበሩና መስኮቶቹ መጋጠሚያ ስንጥቅ በኩል ሠርጾ ገብቶ ዐይን መለየት ሲያስችል ፣ እንደ ታቦት በዙ ርሃትና በጭንቀት ተሸክመውት ያደሩት ሕያው ነገር ዱብ ብሎ ከላያ ቸው ላይ ወረደ ። እምቀው ያቆዩትን ትንፋሻቸውን በመጠኑ አቃል ለው ፣ ፈታቸውን በከፊል ቀስ አድርገው ገልጠው ፣ ሲያስጨንቃቸው ያደረውን ጉድ ተመለከቱ ። ለመውጣት ፈልጎ የሚያነፈንፈው ፣ ጅብ ሲሮህ ፣ ዘሎ ጓዳ ውስጥ በመሸጕጥ የታወቀው የመንደሩ አውደልዳይ ወደል ውሻ ነበር !!

የሚስትየዋ ጣቱ እንደ ፊኛ ፈንዳ ። " አንቺ ነሽ እንጂ ፣ እኔ በፊቴ ንም እሱ መሆኑን ዐውቂአለሁ ። አሁንም ክፈችለት ይውጣ" አለ ቀኖ ኝች ቢሠውር ነገሩን ያቃለለ በመምሰል ።

የቢሠውር ሚስት፣ በኋላ እየማለችና እየተገዘተች እንደ ተናገረችው ከሆነ ፣ ጧት ገብር ሲወጡ እንደ ዋዛ ያሜጠቻት ለአንዲት የቅርብ ጓደ ኛዋ ብቻ ነበር ።

ግን በእንድ ቀን ውስ በመቅደላ አምባ ሙሉ ተዳረሰ ። ግምሻውን የአምባው ዋና ዙም፡"ቀኛዝማች፣ ጅብ እንቅልፍ ነሥቷችሁ አደረ እስ፡ ዛሬማ ከቤት ሊያስወጣን እኮ ነው !" ሲሉ ከፈዝ ጣቱ ጋር አነሡበት።

በተቂት ቀናት ውስጥ ስለ ባልና ሚስቱ አዳር ብዙ ዐይነት ገጣዉ ታሪክ ታከለበት ።

ወትሮውንም ፣ በጠባዩ ምክንያት የሰው ፍቅር የተነፈገው ቀኛዝማች ቢሠውር በቤተ ክርስቲያን ፣ በገቢያ ፣ በግጎበር፣ በዝክር፣ የሰው ፊት ማየት የማይችል ከመሆን ደረሰ። ጥርስ ሳይገለጥ ደማቅቢታል ። ንግግር ሳይደረግ ቃላት ሳይሰሙ ይፈዝበታል ። ምናልባት ሁናቴውን ያጉላው የራሱ የቢ ሠውር የንፍረት ስሜት ይሆናል ። ከእርሱ ፊት ሰዎች የተያዩ ፣ ከንፈ ራቸውን ላመል ያህል ቧርቀም ያደረጉ ፣ በሹክሹክታ የተጨዋወቱ ሴላው ቀርቶ የእክብርት ሰላምታ ያቀረቡለት እንደሆነ ፣ የተግለልቋበት፣ በእንዳች ዐይነት ሥውር ዘዴ ያሸሚጠጡት ይመስለዋል ። ይህ ሁሉ ሳያ ፍሰው ግንም ሰው እንደ ጦር የሚፈራው የእረኛ ዘፈን ወዲያው ተከተለ፡

"አሆ ለሌ አሆ ለሌ
አህያ መጣች ተጭና እንስራ፣
አያ ቢሠውር ውሻ አስፈራራ ።
አሆ ለሌ አሆ ለሌ
አህያ መጣች ጢሻ ለጢሻ ፣
ወንዱ ቢሠውር አዘለ ውሻ ።
አሆ ለሌ አሆ ለሌ
አህያ መጣች . . . "

እረኞቹ እስከዚህም ተዳፍረው ከፊት ለፊቱ ላይ ባይዘፍኑበትም ባሉበት አካባቢ፣ እንዳጋጣሚ ሲደርስ ገና በሩቅ ይሰማዋል ። እረኛ ግላደ ፉና መደባደቡ የባሰ መላለቂያ እንደሚያደርገው ስለሚያውቅ ያልሰማ መስሎ ያልፋል ። በጎፍረት ጦር የባሰውን የሚወጉት ለርሱ የሚያስቡ የሚመስሉት ናቸው ። የታማኝነት ውለታ ማግኘት የፈለገ ሎሌ ለብቻው ጢጋ ብሎ ፣ "እረ ዛሬ ጌቶች ? . . . " ሲል የሰማውን ያቀብለዋል ። ከሚስቱ በላይ በድብቅ የሚጉበኝት ገረድ፣ "እረ ምንድነው ነገሩ ም" ስትል ከማድቤት ፣ ከጉረቤት፣ ውሃ ስትቀዳ የሰማችውን ትነግረዋለች ።

ቀኛዝማች ቢሠውር ፣ በመቅደላ አምባ ከልል ነዋሪዎች በግልጽም ሆነ በሥውር የሚዘንብበት የፈዝ፣የሐሜትና የሥላቅ ውርደት ከቁኛ ቢለ ማውም፣ የባስ ያስጨነቀው ወሬው ለቴዎድሮስ መድረሱ ነበር ። ዋለም አደረ መድረሱ ደግሞ እንደማይቀር ይታወቀዋል ። ፍርሃትና ፈሪነ እንደ ዐይነ ምድር የሚጸየፉት ቴዎድሮስ ነገሩን በዋዛ አያልፉትም ። እስር ቤት ባይከቱት ስንኳ ወይ ያግዙታል ። ታስዚያ እዋርዱው ይሽ ሩታል ። እስከ አሁንም የአምባው ምክትል ዙም ሆኖ የቆየው፣ በቴዎ ድሮስ ዐይን ግምት ውስጥ ገብቶ ሳይሆን፣ የአምባው ዋና ዙም ራስ እን ዳለ ስለሚደግፉትና በቴዎድሮስ ዘንዳም ተደማጭነት ስላላቸው ነበር ።

ከውሻው ወሬ ወዲህ ግን፣ የእርሳቸውም አስተያየት የተለወጠበት ይመስላል ። እንደ ሌሎቹ በግሥድ ባይሣለቁበትም ለግራቱ እንደ ፈለጉ ዐይነት በሁናቴያቸው ተቆጥበውበታል ። ይህንን ሁሉ ሲያስብ የሚደር ስበት አስከፊ ዕድል ይታየዋል ። መዘባበቻ ከመሆን ዐልፎ የወደቀ ግንድ ምጣር ይበዛበታል ነውና ቁጭቱን ፣ ቂም በቀሉን የሚወጣበት ሁሉ አሰፍስፎ ይጎሣቢታል ።

ይህ ከመሆኑ በፊት ነበር ፣ ቀኛዝማች ቢሠወር ከቤቱ ወረድ ብሎ ከሚገኝ የዋርካ ዛፍ ላይ አንድ ቀን በጠፍር ተንጠልጥሎ የተገኘው ።

—5—

አንድ ባለጉዳይ ፣ ከታንጉት ማረፊያ ቤት የመጣውም ቀኛዝማች ቢሠወር ሳይፈታ እንደ ተቀበረ ሁሉ፣ ዐርባውም ሳይመጣለት ዐልፎ ፣ ስለእርሱ መወራት እየቀረና እየተረሳ ከሔደ በኋላ ነበር ።

ታንጉት ፣ ከታዛ ተቀምጣ ጥጥ ስትፈትል ፣ ከየት በኩል እንደ መጣ ያላስተዋለችው አንድ ሰው ድንገት ከራቷ አጠገብ ደርሶ ሰላምታ በማት ረብ እጅ ነሣ ። የተለመደውን መልስ ሰጠችውና በመገረምና በመጠየት መልክ አስተዋለችው። የውጭ መንገደኛ በመቅደላ አምባ ውስጥ ስለማ ይተላለፍ፣ግረፊያ ወይም ማደሪያ የሚፈልግ እንግዳ ሊሆን አይችልም። አለባበሱና ሁናቴው ደግሞ ወታደር ቀመስ ይመስላል ። እግረ መንገዱን እንዴት ሰነበታችሁ በማለት የሚጠጣ ውሃ ለመጠየቅ ሰው መምጣቱ አዲስ ነገር ባይሆንም፣ ታንጉት ሰውየውን ከዚያ በፊት አይታው ስለማ ታውቅ ጥቂት ግር አላትና በሆድዋ ራስዋን ጠየቀች ።

“ደሞ ማን አባቱ ልኮብኝ ይሆን ፈጣሪዬ ?”

ባል ወይም ውሽማ ዘመቻ ሲሔድ፣ካለቦለዚያም ከአጠገብ ራቅ ሲል ራስ መጥቶ ወይም ሁነኛ ሰው ልኮ የፍቅር ርጥባን መለመን የተለመደ ነበር ።

ገብርዬ ስለሚወደድ ፣ ስለሚከበርና ስለሚፈራ ፣ እንደ ሌሎቹ ሴቶች ታንጉት ብዙ ባትደፈርም ዐልፎ ዐልፎ ሞካክረዋታል።ደጀጠኙና አላማኙ የበዛባት ግን፣ መቅደላ አምባ ከመጣች በኋላ ነበር። እንደ ፈለጉ መውጣትና መግባት በመከልከሉ ምክንያት ከባልዋ ወይም ከወዳጅዋ የተለየች ሴት ድጋሚ የማታገኘው ይመስል ፣ መቅደላ እንዲቆይ የተላከው ወንድ የሕይወቱ ፍጻሜ እንደ ተቃረበ ቆጥሮት ከጊዜ ጋር ለመሻማት የቈረጠ ይመስል ፣ ከተለመደው የጎብረተሰብ ሥነ ምግባር ውጭ የውሲብ ፍላጎት በረከተ ። ባል ይኑራት አይኑራት ወንዱ አይታት ደስ ያለችውን ሴት ዐይን ሳያሹ ሰው ልኮ መለመን የተዘወተረ ሆነ ። ለመግደርደር ካልሆነ በቀር ከልብ ሳያንገራግሩ እሺ እያሉ ፈቃድ መፈጸም እየተለመደ ሔደ። ነውር መባሉ ቀረ። በአንዳንድ አካባቢ ፣ እንዲያውም እያደር የአስረሽ ምችው መልክ ያዘ ።

በዚህ ሁሉ መካከል ታንጉት የተላከባትንም ፣ ራሱ የመጣውንም ፣ እየገመጸች ፣ እያስፈራራች ከመለሰች በኋላ እንዳትሞል አንድ ጊዜ ብቻ ፈጽማዋለች ። ለዚሁም ረዘም ላለ ጊዜ ከገብርዬ ብትለይም የተ ፈጥሮ ስሜቷ አሸንፏት ሳይሆን፣ ልመናው በትርብ ባልንጀራዋ በኩል መጥቶ እንደ ውጋት ነጋ ጠባ ፋታ ስለ ነሣት ነበር ። ቤተ ክርስቲያን ሲሔዱ፣ ከቤተ ክርስቲያን ሲመለሱ ፣ ቡና ሲጠጡ ፣ እንዲያው ሊገናኙ በቻሉ ቁጥር ሁሉ ፣ “ግዴለም ብዬ ቃል ገብቸለት ፣ አባይ ታደርጊኝ ታንጉት ? አሁን ማ ይሙት የቆረብሽ አትመስይም ? አሁን ይሽ ሁላ አንቺ ብቻ ጨዋ ፣ ጥሩ ተብለሽ እኛን ልክስክሶች ፣ ወራዶች ለማለት ነው ? ባሎቻችን ለእኛ ሲሉ ደብረ ታቦር ላይ እየጸሙ የሚጠብቁን መሰ ለሽ ? ተይ ታንጉት ። እረ እጎትሽን አታሳፍሪኝ ! አታስቀይሚኝ ! ደሞ ደስ የሚልሽ ሰው ነው ። በኔ ይሁንብሽ ” እያለች ብታስቸግራት ለመገ ላገል ያህል በመጨረሻ እሺ አለቻት ።

ሰውዬው በተቀጠረው ቀን ፣ ሰዉም ከብቱም በየቤቱ ከተከተተ በኋላ ጨለማን ተገን አድርጎ መጣ ። ባልንጀራዋ እንደ ነገረቻትም ሰውየው መልኩም ቁመናውም ያማረ ነበር ። ነገር ግን የአምባ ጊዮርጊሱ ድርጊት ጸጸት ፣ የደብረ ብርሃን ሥላሴ መቃብር ቤት ምሥጢር የመውጣቱ ሥጋት መንፈሷን አኮማትሮ እንደ ያዘው ስለ ነበር ፣ እንደ ዕላ ተወጣችው እንጂ የፍቅር ጨዋታውን አልተደሰተችበትም ። ሌላ ጊዜ ላትደግመው ወስናለች ።

ሰውየውን እየተመለከተች ይሽ ትወላ በሐሳብዋ ውልብ ሲል ንዴት ቆንጠጥ አደረጋት ። ነገር ግን፣ የመጣበትን ጉዳይ ላታረጋግጥ እንግዳ ሰዉ በቁጣ መቀበል ነውር መሆኑ ተሰማትና ገታ አደረገችው ። በተዘዋዋሪ መንገድ እንደ ዋዛ መጠየቅ የጀመረችው፣ሰውየው በእንግድነቱ ዐረፍ እንዲል ተነግሮት፣ ደንገጡርዋ በለጡ እንደ ታዘዘችው እህል ውሃ አቅርባ ሁለት ሦስት ጊዜ ከጐረሰና ጠላውን እንድ ጊዜ ከተጐነጨ በኋላ ነበር ።

“ተዚህ ነዋሪ ነህ ?”

“አዎ ! ይሽው ሁለት ዓመቴን ይዣለሁ ። እስረኛ ጠባቂ ነኝ ።”

“ታሁን ቀደም አይቸህ አላውቅም ።”

“ተሠፈራ ብዙም አልወጣ ።”

“ዛዲያ ዛሬ ምን እግር ጣለህ ?”

“ተርበዎ ተልኬ ።”

“ቱኔ ? ራሱ መምጣት አቅቶት የሚልክብኝ ሰው ደሞ ማነው ?” አለች ታንጉት ፣ የተገረመች በመምሰል በሆድዋ ግን ፣ የጠረጠረችው ጉዳይ መሆኑን እያሰበች ።

ሰውየው ከሚያላምጠው እህል ጋር ትንሽ አቅማማ ። ‘እለቃ’ ሲል መለሰ ።

“እለቃ ? እለቃ ምን ተስኖት ?” ታንጉት የሥላሴ ደብር እለቃ ማለቱ መሰሏት ነበር ።

“የለም ። እለቃ አክሊሉ ።”

“አክሊሉ ? አክሊሉ ?” ፊቷን ጨፍግግ አድርጋ ከራስዋ ጋር ተጠ ያየቀች ። ደብተራ አክሊሉ መቅደላ አምባ የታሰረ መሆኑን ብታውቅም ፣ ስለ ሰውየው መልእክት ያደረባት ግምት ሌላ ስለ ነበርና‘እለቃ’ የሚለው ማዕረግም ለጀሮዋ አዲስ ስለሆነባት ለጊዜው አልተያያዘላትም ።

“ተፈረንጆቹ ጋር አብረው ተይዘው የታሰሩት ” ሲል አረጋገጠላት ።

"ደብተራ አክሊሉ ?" ካሰበችው መልክት ጋር ስታጋጠመው የመ
ገረምና የፈዝ ሣቅ መጣባት ። ትክክለኛውን ምክንያት ባታውቅም ደብ
ተራ አክሊሉ ከነገሩ ሁሉ ከጉርምስናው ጀምሮ በሴት እንደማይጠረ
ጠር ጉንደር ሳለች ሰምታ ነበር ።"ወይ አይመነኩስ ወይ አያገባ እንዲሁ
ባሕታዊ መሰል ነው " ነበር ወይዘሮ ደብሬ ያሏት ። በጃጀ ስሚታቸው
ድንግል ካልገሥ'ኩ ብለው የተሞሸሩት ሽማግሌ ፣ በጫጉላ ቤት ስለ
ሆኑት የሰማችው ድንገት ትዝ አላት ። መቆየት ብዙ ጉድ ያሳያል ይባል የለ!

"እዎ እመቤቴ" ሲል መልክተኛው በድጋሚ አረጋገጠላት ።

"እሺ ምን ብሎ ?" አሁን ረጋ ማለት ጀመረች ።

"እንዲረዱዋቸው ይፈልጋሉ ።"

ባንድ በኩል የተጠየፈችው ጉዳይ ባለመሆኑ ፣ በሌላ በኩል ግት
ያመጣባት ፈዝ በመቀጨቱ ፣ ደስታም ቅሬታም ተቀላቅሎ ተሰማት ።
በፈዝ አንቱታ ፣ "ምን እንድረዳቸው ነው ? ስንት አጠራቸው ?" ስትል
ጠየቀች ፣ የወይኒው በደል ትዝታ የቀሰቀሰባትን ንዴት እንደ ምንም ቻል
አድርጋ ።

"አረ ሞልቷል ።"

"እዛዲያስ ?"

"ከስር እንዲወጡ ።"

"ምን ?" ስትል እንደ መጮህ ቃጣት ፣ ጆሮዋ የሚሰማውን ማመን
አቅቷት ።

"ማለቴ እንዲያመልጡ ።"

"በስማም ወልደ መንፈስ ቅዱስ ! ጆሮ አይሰማው ጉድ የለ ።"
ጆሮ ግንድዋን በሁለት መዳፍዋ ከደነች። "አንተ የታጠቅ ዘብ ሆነህየታ
ጠቅ አስረኛ እንዲያመልጥ ነው የምትለው ?" ፊቷ ሁሉ ተለዋወጠ ።

"ማለቴ እንዲወጡ" ሲል አነጋገሩን መልሶ አረመ ።

ግን አላዳመጠችውም ። መላ ሐሳብዋ ተመልሶ የሚያየውና የሚሰ
ማው፣በእነ ደብተራ አክሊሉ ተንኰል ምክንያት ወይኒ በሰነበቱበት መን
ደር የተፈጸመውን የግፍ ጭፍጨፋ ፣ ደባርቅ ላይ የደረሰውን ዕልቂት
ነበር።ደባርቅ ላይ ሞታ መገኘቷን የሰማችው ያይኔ አበባ ሁለመናዋ መጣ
ባት ። " አሁን ነግሬ ላሲዝህ ?" አለች በጥያቄ ሳይሆን በቁርጠኝነት
ዛቻ ።

"ምን ዐጠቅሞታል ?" እርሷ ስትነድ ፣ ሰውየው የሚያደነዝዝ ዕፅ
እንደ በላ ዐይነት የረጋ ውሃ መሰለ ።

የሰውየው አለመደንገጥ ከንዴቷ መንጥቆ ወደ ሐሳብ አስገባት ። ያ
ከይሲ ደብተራ ያላንዳች ምክንያት ባጋጣሚ ብቻ እንደዚህ ያለ ድፍረት
አልላከባትም ። አንድ ነገር ቢጨብጥ ነው ። ምን ነገር ? የመልክተኛ
ውን ህልውና ለጊዜው ረስታ ፣ መልሱን ጠርጋ የምታወጣው ይመስል
ግንባርዋን በጣትዋ ፈተገች ። በዚህ ተማምኖ ይሆናል የምትለው አን
ዳችም ግምት አልመጣላት አለ። "ለመሆኑ እንዲህ ያለ የድፍረት ሐሳብ
ይዘህ ስትመጣ ትንሽም አትፈራ ?"ስትል በመገረም ዐይነት ጠየቀች ።

"እይ እሱማ መቸስ ፣ ግና ጉዳዩ የሁላችሁም መሆኑን ንገር ስላሉኝ
ነው እንጂ"

"የሁላታችን ?"

"እም ! እርሳቸው ከአምባው ቢወጡ ለርስዎም እንደሚበጅ፣ ካለበለ
ዚያ ግን . . . "

ታንጉት ፣ ሰውነቷን አንዳች ነገር ውርር አደረጋት። "ካለበለዚያስ?
ጨርሰው እንጂ !! "

"ዝርዝሩን አልነገሩኝም ። ለሁሉም ዛሬ ማታ ራሳቸው የሚመጡ
መሆናቸውን ንገር ብለው ነው የላኩኝ ። "

"ምን ?" ስትል አሁንም እንደ መጮህ ቃጣት ።

መልክተኛው የመጣበትን ጉዳይ የጨረሰ ይመስል ለመሔድ ተነሣ።

"እስቲ ደጇን ይርገጣት ! አንተንም አስቀፍድጇ ነው የማሳድርህ"
ስትል ዛተች ። በሆድዋ ግን እንደማታደርገው ይሰማት ነበር ። አንዳች
ፍርሃት ተለቀቀባት ።

መልክተኛዉ እንዳለው ፣ አክሊሉ የመጣው ምሽቱ ገፍቶ ፣ ሰዉም
ከብቱም ለአዳሩ ከተከተተ በኋላ ነበር ። ታንጉት 'እስቲ አባቴ!' እያ
ለች ደግማ ደጋግማ ራስዋን በራስዋ እያታለለች ብትቆይም ፣ ደንገጡርዋን
በለጡን አሰናብታ ብቻዋን ተቀመጠች ።

ገርበብ ያለውን መዝጊያ ገፍቶ ፣ እንደ ጨለማው የጠቆረ በርኖስ
ለብሶ አክሊሉ ሲገባ ፣ ሆን ብላ የጠበቀችው ይመስል ሳትደነግጥ እንደ
ዋዛ ነበር የተመለከተችው።እርሱም እንደምትጠብቀው ያረጋገጠ ይመስል፣
"እንደምን ሰነበታችሁ ? ደኅና ከረምሽ ወይዘሮ ታንጉት ?" የሚል ሰላ
ምታ አቅርቦ ፣ ሳይጋበዝ ከእንዱ ቋንጣ ወንበር ላይ ተቀመጠ ።

ለሰላምታው መልስ ሳትሰጠው ረዘም ላለ ጊዜ ዝም ብለው ተፋ
ጠጡ ።"የመጣህበትን ተናገር እንጂ ፣ የዐመጽ ሰይጣን !" አለች ታን
ጉት በመጨረሻ ቅርጭም ባደረገችው ጥርሷ መካከል ። በጥቁር በርኖስ

ተጠቅልሎ በተለመደው ኩርምት ያለ አቀማመጡ የሚርገበገበው የጢፍ መብራት ሲያንአባርቅበት ፣ በእርግጥም ሥጋ የለበሰ አንዳች ዐይነት ጥልማሞታም ጋኔን መሰላት ።

"ለሰድብኩ አልመጣሁም" ሲል አክሊሉ መለሰ ፣ ከንፈሩን በባር ናሱ ክሳድ እንደ ሸፈነ ።

"እትናነሩኝ ለማለትም ቢታህ ?" አለች በመዛት ዐይነት ።" ያን ሁሉ ሠርተህ ?"

"የኔ ጥፋት የተባለብኝ ከሌላው መች ይብስና ።"

የአነጋገር ዳር ዳርታው ገባት ፣ "ከማን?"

"ከአንቺው ።"

"ምን ?" መስማት ፈለገች ። መስማቱንም ፈራችው ።

"ይኸ ሁሉ ሕዝብ ፣ ፈረንጁ፣ ተዚህ ታስሮ የሚሠቃየው በማን ምህ ኛት ሆነና ?"

"እኔ ?" ስትል በማስተባበል ድርቅና ጠየቀች ።

"ደብረ ብርሃን ሥላሴ መቃብር ቤት ይመስክር " አለ አክሊሉ በፈዝ ቃና ።

"እህ! ፈረንጆቹ ነገሩህ ? ለምን ለእባ ታጠቅ አልነገሩትም ዛዲያ?" የታንጉት አነጋገር ጥያቄ ሳይሆን የሞንቀት ክርክር ቢጤ ነበር ።

"ለወይን ምስክር ምኑን ይነግሩኛል ። የቴዎድሮስን ጉድ ስትዘክዝኪ ተዚያው ነበርኩ ፣ ከመቃብር ቤቱ ። ለቴዎድሮስ አለመንገራቸውም የሆነ እንደሆነ እኔ ለምኛቸው ነው ። ላንቺም ስል ፣ ለእኔም ሙንገድ አገ ኝቢታለሁ ስል ነው ። ተያይዞ መጥፋቱ ምን ፋይዳ አለው ብዬ !"

"ለተለምር ነው ፣ የእኛ አዛኝ ቅቤ አንባች !" አለች ታንጉት እንደ እባት በሚያቃተል ብሽቀት ።

"አልዋሽም ፣ ላንቺ አዝኜ ሳይሆን ራስሽ ለራስሽ እንደምታዝኚ በማወቅ ነው ።"

"እንዴት ?"

"ቴዎድሮስ ፣ ምስጢሩን ቢያውቅ እንዴት እንደሚሆን መቸም ታውቂያለሽ። ፈረንጆቹን ነጋ ጠባ ቁም ስቅል ያሳያቸው የነበረው ማን እንደ ነገራችሁ ንገሩኝ እያለ አይደል ? በኔ ልመና ነው እምቢ ያሉት። ንብርዬም ቢሆን ፣ እምባ ጊዮርጊስ የሆነውን ቢሰማ ደስ ይለው መሰለሽ ?" አለ አክሊሉ እንደ ዋዛ ቢያስመስለውም አጠያየቁን ረገጥ አድርጎ ።

"ምን ሆነ ደሞ ?" ስትል ታንጉት ጠየቀች ፣ ምን ግለቱ እንደሆነ ግን ሆድዋ እያወቀ ።

"እቴ 'ሁሉን ቢናገሩት ሆድ ባዶ ይቀራል ' ተብሏል ።"

አክሊሉ የማስጠንቀቂያ ውሱን ቋጥሮ፣ ታንጉትም የመፍቻው መልስ ጠፍቷት ለጥቂት ጊዜ ዝም አሉ ። ዐልፎ ዐልፎ ከሚሰማው የአዕዋፍና የከብት ድምፅ በስተቀር ፣ ዙሪያቸውን እንደ ሸፈናቸው ጨለማ ጸጥታ ሰፍኗል ። ታንጉት ግን ለገብርዬ ልጅ ለመውለድ ባደረባት ጉጉት ከስንት ዓመት በፊት የሆነው ነገር ወደፊት ከሚንበለበለው ፣ ከሚያቃጥለው የገብርዬና የቴዎድሮስ የቁጣ እሳት ጋር በሐሳብዋ ሲታያት፣ በአካልዋም በመንፈስዋም መላ ሰውነቷ ማዕበል እንደ መታው ጀልባ ተናጋ፣ተናወጠ። "ዛዲያ ምናርጊ ነው የምትለኝ አሁን !" አለች ታንጉት ቆይታ - ቆይታ ጭንቀትና ሠቀቀን አንቆ ባስቀረው ደክማ ድምፅ ።

"ብዙም አላስቸግርሽም እቴ ታንጉት ። እንዲያውም አንቺን ራስ ሽን ላስቸግርሽ አልፈልግም ። ቀላል ነገር ነው የምጠይቅሽ ። አገልጋይ ሽን ስጭኝ ፣ እንዳባት ፣ እንድገባት ።"

ጥያቄው ስላስገረማት ፣ አትኩራ ለመመልከት የፈለገች ይመስል ታንጉት ፊቷን ወደፊት ሰገግ አደረገች ። "ምን ልታረጋት ?" ስትል ጠየቀችው ።

"አይዞሽ እቴ ታንጉት ! የምነግራትን ታረገች ቀላል ነው ። ቀና መንገድ ። ይህንን አስጠንቅቂልኝ ብቻ ። ታለበለዚያ ተመልሰን ሁለ ታችንም ጣጣ ውስጥ ነው የምንገባው ። ተዚህ በተረፈ አልሸጣት፣ አልለውጣት ፣ ሌላስ ምን እንዳላረጋት ብለሽ ነው ?" ሲል ይብቆት የኖረውን ምሥጢሩን በሚያጋልጥ ፈዝ ፈገግ አለ ። ታንጉት ሳትወድ ሣት መጣባት ።

"ለመሆኑ ፣ ለመሆኑ" አለች ታንጉት ፣ ባንድ በኩል እንድ ያልደ ረስበት ምሥጢር በመኖሩ ፣ ራስዋን የምታጽናናበት እንዳች ዐይነት እሽናፊነት እየተሰማት ። በሌላው በኩል ያወቀውን ካወቀ ፣ ዕድላችን ተቆራኝቷልና 'ያበጠው ይፈንዳ' በሚል ግዴለሽነት፣ "የመትደላውን እንዴት ሳትሰማው ቀረህ ?"

"ተዚህም ጉድ ነበር ! መስማት ስላላስፈለገኝ እልሰማሁትም ። ትልቁን ነገር ይዤ፣በትንሹ ምን እታከተኝ ! ተዚህ የሚሠራው ተራ ነገር ነው ። ደሞስ ምን ያስገርማል ? እና በቅርጫ እባባላችን ፣ 'ትልቁ መደብ የደረሰው ፣ ሌላ ዕባ አይጥልም ።'ስለዚህም የምትዪውን አልተከታተል ኩም፣አልሰማሁም ።" አክሊሉ በዚያ አስተያየቱ እጨንቁር ተመለከታት።

"አየ፣ እንዲያው ነው እንጂ" አለች ታንጉት ፣ ያነሣችውን ጥያቄ በማቃለል ።

አክሊሉ ፣ ጉዳያቸው እንዳለቀና ታንጉትም እንደ ተሰማማች ቦጣ ስመሰል ለመሔድ ተነሣና ፣ እንግዲህ በጊዜ ወደ መቃብሬ ልመለስ ፣ ተጎ ኮለኛ ዘብ ፈትሾ ደሞ እንዳያጣኝ ። ሰበብ ነው የሚፈልገው ። ልጅቷ ግን ከረፋዱ ላይ ጀምሮ ተሰናድታ ብትቆየኝ መልካም ነው ። ልጅቷ ንን ነገ ፀሐይ ሳይጠልቅ ነው የምንጀምረው ። ብዙ ጉዝ እያስፈልጋ ትም ። አንድ አገልግል ብጤ ፣ ለቁስለኛ የሚሆን ምግብ ፣ የተገኘውን ዐይነት፣ የሚያስቸግርሽ ተሆነ ፣ ተኔም አመጣዋለሁ ። ተዚያ ፣ ጋቢዎ ፣ ድግም፣ለርሷ የሚሆን ልብስም እንዲያው እንደ ሆነው ዐይነት" ሲል እንደ መሰናበት ዐይነት እጅ ነሣ ።

"እስቲ ሌላ ነገርም ልጠይቅህ ? እውነቱን የምትናገር ተሆነ ?" ስትል ታንጉት ፣ የጀመረችውን ገፋችበት ።

"የማውቀው ነገር ተሆነ ።"

"ወይዘሮ ደብሬን ግን ነው የገደላቸው ?" ታንጉት ስማቸውን ስትጠራ ፣ ውናቴያቸው ከዐይነ ሕሊናዋ ድቅን አለባትና እንደ መጋረጃ ዐይነት መዳፏን ከፊቷ ላይ ሸፈነች ።

"ወሬውን ሰማሁ እንጂ በእውነት የማውቀው ነገር የለኝም ። እሳ ቸውን ምን ብዬ እጠናወታቸዋለሁ ! ተሳቸው ነገር የለኝ ። ነገሬ ተሌላ ። ባንችም ላይ ቢሆንምኮ ክፋት የለኝም ። ነገሬ ተሌላ ። እንዲያው መቼ ለፊያ ሆንሽ እንጂ ።"

"ዛዲያ ግን በክፉ ያስባቸዋል ! እርሳቸው የሆነ እንደሆነ ለሰው ክፉ ማሰብ ቀርቶ እንዲያው ስቷቸው ክፉ አይናገሩ ።"

"ብዙ ወዳጅ ያለውኮ ጥቂት ጠላት አያጣም ። ለማንኛውም እኔ ወይዘሮ ደብሬን በክፉ የማስብበት ምህኛት አልነበረም ።"

"ምሥጢርክን ስለሚያውቁብህ ነዋ !"

"ስለኔ የሚያውቁት ነገር አልነበረም ። የተገናኙት ከእቡነ ሰላማ ጋር ነበር ።"

"ያው ነው" አለች ታንጉት ፣ ድርቅ ባለ አነጋገር ።

"የምታምኝኝ ተሆነ ነገርኩሽ !"

"እምነት ! እምነት አልከኝ ደብተራ አክሊሉን ?" ለመሔድ መነሣቱን ስትመለከት ፣ " እህል ውሃ ሳትል !" አለችው ታንጉት ፣ ልማድ ለመፈ ጸም ም በፈዝም መልክ ። ይህንን ስትናገር ለትጽበት እንድ ሐሳብ ብልጭ አለባት ። መልክተኛው እንደ ነገራት ፣ድፍት የምታደርግ መርዝ ከምግብ ጋር አዘጋጅታ ብትጠብቀው ኖሮስ ? አክሊሉ ከሞተ የሚያስፈራራበት ምሥጢርም አብሮ ይቀበር ነበር ። ግን መቸም መሠሪ ነውና አስቀድሞ ካልተቀመሰለት ምግቡን አልጋበዝም ቢልስ ? ደግሞስ እርሱ እንዳለው ፈረ ንጀቹ ግን እንደ ነገራቸው እስከ አሁን ሳይገልጹ የቆዩት ስለ ለመናቸው ከሆነ ሲሞት ቢለፈልፉስ ? ለሁሉም አክሊሉ እምቢ ግለት እንዳትችል እድርን ጉዳዩን አግሥሮ ለመሔድ ከተነሣ በኋላ ፣ መላ ግሰላሰሉ ጅብ ከሔደ ውሻ ጮኽ ዐይነት መሆኑ ተሰማት ።

"ግዴለም አትቸገሪ ። እንደ ዱሮው በደኅና ጊዜ ትጋብኝኛለሽ ። ለእሁኑ ግን ፣ አገልጋይሽ የምንግራትን ሁሉ በትክክል እንድትፈጽም በሚገባ አስረጅልኝ ። የሚበጀው ለሁለታችንም ነው " አለና አክሊሉ በበርናስ የተሸፋፈነ ሰውነቱን እያጥመለመለ ተሰናብቶ ወጣ ።

አክሊሉ ላቀረበው ጥያቄ የተረጋገጠ መልስ ባያገኝም ፣ ታንጉት የእሽታ ወይም የእምቢታ መልስ ባትሰጥም ፣ በሁለቱም ዘንድ ጉዳዩ እንዳለቀለት የተሰማቸው ይመስል በዝምታ ተለያዩ ።

በበነጋው ፣ጀንበር በምዕራብ ግዘንበል እንደ ጀመረች ፣ እንዲት ልጅ እግር ሴት ፍትግ ስንዴ የያዘ ዕንቅብ በራስዋ ተሸክማ ፣ ዋንድ ትከሻዋ እንጀራ በሥጋ ወጥ ያሰበት አገልግል እንግታ ፣ በጀርባዋ ልብሰ ልብስ የተከተተበት ከረጢት አዝላ ፣ በወረደሉ በኩል ወደ አደው የመቅደላ መውጫ በር መጣች ።

"ተመለሽ የት ነው የምትሔጅው ?" ሲል ዘቡ ደነፋ ።

"ተባሉ ዘንዳ ነዋ !" አሰች ልጅ እግርዋ ሴት የደኅግት መሆንዋን ለመግለጽ ዕንቅቡን ከራስዋ እያወረደች ።

"የምን ባል ?" ሲል ዘቡ ጠየቃት ። መልካም ድግስ ፣ እንደ ቀረበለት እንግዳ ቁመናዋንና ልጅ እግርነቷን በፈገግታ እየተመለከተ ።

"የምን ባል ? የሕግ ባሌ ነዋ !"

"ዛዲያ እኔ ስለ ባልሽ ምን አስቸገረኝ እቴ ? ወንድ እንደሆነ ሞል ቷል ። ተኔ ጀምሮ " ይረቱን ነፋ አድርጎ አስመረቃት ።

"ያሳልፋኝ ይልቅስ !" አለች በተኮሳተረ አነጋገር ።

"የት ?" ዘቡ ሊያሾፍባት ከጀለ ።

"የት ? " እንደ ተነገረችው ፍጥጥ አድርጋ ተመለከተችው ። "ተባሉ ዘንዳ ነዋ ! ከመሐመድ በሽር ወንበያዎች ጋር ሲዋጋ ለቆሰለው የቴ ዎድሮስ ወታደር ስንት አታደርሽም የምትለኝ ተሆነ ምን ቸገረኝ ። ለራስ እንግራለሁ" አለችውና የምትመለስ ለማስመሰል ጓዟን ሰበሰበች ።

"እቴ አስቲ ታግሽ ፣ እትቆሚ" አለ ዘቡ ግራ ተጋብቶ ። ታች-ታቹን በወረደሎች መንደር ከመሐመድ በሽር ሙናሮች ጋር ሰሞኑን በተደረገው

ውጊያ ብዙ ወታደር መሞቱን ሰምቷል ። ብዙ ቁስለኛም ወደ መቅደላ እምባ ገብቶዋል ። በየመንደሩም ፣ በየጉጦም የቀረ ሊናር እንደሚችል ያውቃል ። ግን ስንት ለግቶበል ወደ ውጭ የሚወጣ ሲያጋጥመው ገና የመጀመሪያ ጊዜ ነው ። ውሳኔው አስቸገረው ።

"ዛዲያ አሳልፈኛ !" አለችው አሁንም በተኮሳተረ አነጋገር ።

"እሺ ! እሺ ! እቱ" የያዘችውን ምግብ በአፍንጫው እያነፈነፈ በእድናቆት ከንፈሩን መጠጠ ። "እስቲ በደኅና ያገናኝችሁ ። ታልሆነም መቸም ፣ እስተዛዛኝ እሆንሻለሁ " አለና ፈገግታ አሳይቶ ሸኛት ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ የወታደር ልብስ የለበሰ ኮሳሳ ቢጤ ሰው እየተጣደፈ ወደ ዘቡ በር መጣና፡"አንተ የቴዎድሮስ ዘብ ነህ ?" ሲል በቁጣ ጠየቀ ።

"ብሆን ነው እንጂ ዛዲያ ተዚህ የምጠብቀው ።"

"እንዲት ልጅ እግር ሴት በዚህ አልወጣችም ?"

"ልጅ እግር ሴት ? ሴት ! " ዘቡ በድንገት ቢታወሰውም ጸንሩን እያከከ የሚያስብ መሰለ ።

"በዚህ በኩል እንደ ወጣች ሁነኛ ሰው ነግሮኛል ። "

"እንዲት ሴት ባሳን ለመጠየቅ ወጥታለች መስሎኛል " አለ በማ ቅማማት ።

"ባል ? ባልሞማ እኔ ነበርኩ " ሲል ሰውየው ከት ብሎ ሣቀበት ። "የቴዎድሮስን ወታደር ሚሽት ፣ ማንም ሽፍታ እያስኮበለለ ሲወስዳት ዝም ብላችሁ ታያላችሁ ማለት ነው ? ወይ ነዶ !" ራሱን ነቀነቀ ። "መቸስ ምናረጋለሁ ላለቃየ መንገር እንጂ !" ወደ መጣበት የሚመለስ ይመስል ዞር አለ ።

"እኛ መቸስ ምን ዐወቅን ብለህ ወንድም ። እሷው እንደ ነገረችን ነው ያሳለፍናት ። አሁንምኮ ፈጠን ብለህ ተሔደክ ትደርስባታለህ ። ብዙ አትርቅም " አለና ዘቡ መንገዱን በእጁ አመለከተው ።

"ለነገሩ ነው እንጂ የት አባትዋ ታመልጠኛለችና ! እኔ አባ ድፋው ሱሪ አልታጠኩማ !" እያለ ሰውየው ቁልቁለቷን ተንደርድሮ ወረደ ።

መተኪያ እስኪታጣ ድረስ እጥረት የደረሰ ያህል ፣ ራሳቸው እንደ ተራ ወራቶኛ ድፍት ቀና የሚሉበት ዕር መግሪያ ሥራ ፣ በጎሞት በጎ ልና በሸንበት ቀን የሚቆም ቢሆንም፣ ቴዎድሮስ ግን ፈጽሞ ዐርፈው

ውለው እያውቁም ነበር ። ከጊዜና ኪሥፍራ ጋር እሽቅድድም የገጠሙ ይመስል ያለማቋረጥ ይንቀሳቀሳሉ ።

እየባሰበት የሔደው የሽፍታውም ነገር ፋታ የሚሰጥ አልነበረም ። ከጋፋትና ከደብረ ታቦር የግማሽ ቀን የማይርቅ መንገድ ድረስ እየመጣ ለመዝረፍ የደፈረ ሽፍታ ሞልቷል ። እንዳንድ የአካባቢ መን ደሮችም የቴዎድሮስን ወታደር ብቻውን ካገኙ እየገደሉ እስከ መደበት ለማቅረብ ይመጣል ። በዚህ ሁሉ መካከል ቴዎድሮስ በቀላሉ መንቀ ሳቀስ የሚችል መጠነኛ ሠራዊት እስከትለው ከጋፋት አራቱንም ግዕ ዘን መጉብኘት ፣ መፈተሽ የማያስርጥ ተግባራቸው ሆነ ።

በዚሁ ሁሉ ጉዞዋቸው ፣ ወትሮ ከተለመደውና ባለሟላቸው ከሚይ ዝላቸው ነናጥ ፣ ራሳቸው ከሚታጠቁት ጉራዴና ሽጉጥ ጋር ከእንግባቸው የማይለይ አዲስ መሣሪያ ነበራቸው ። ይኸውም ራሳቸው ያመጣላቸው የሩቁን አቅርቦ የሚያሳይ መነጽር ነው ። ስጦታውን መጀመሪያ ሲያ በረክትላቸው፡ "ምነው የመይሳው ልጅ ! ዐይን በሽተኛ ነው አሏችሁ ?" ብለው ያሳጥላሉትን ያህል ፣ ከዚያም ጠቀሚታው ተነግሮዋቸው ከዐይና ቸው ላይ ተከለው ወደ ግዮ ከተመለከቱ በኋላ ፣ "ምን ትቅልጹብኛላ ችሁ ! ባይኔ የማየውን ተራራ የባለ ሞጋግ ሲያለብሰው " ብለው ሲወ ረውሩት ያልታጡትን ያህል ፣ ለተወሰነ ሚላግ ተስተካክሎ ካዩበት ፣ ራሳቸውም ማስተካከሉን ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ ፣ የትም ቢሔዱ ከእጃቸው የማይለዩት ብርቅ ዕቃቸው እድርገውታል ።

ለራሱ በግልጽ እልነገሩትም እንጂ ፣ ከሌሎቹ የውጭ አገር እስረኞች የተለየ እስተያየት ለራሳም የሚያደርጉለት እንዱ ምክንያት ይህ መነ ጽር ነበር ። እልፍኝ ተወዝፎ እንደሚውል የዐረብ ሼህ በመቁጠር፣ አበባ ምንጣፍ ካመጣላቸው ከቆንስል ካሚርን የተሻለ አመለካከት ያለው ሆኖ አግኝተውታል ።

በየደረሱበት ፣ ዙሪያውን የሚጸኝ ከፍታ ቦታ ይመርጡና መነጽ ራቸውን ይደግናሉ። የመነጽሩ ዲካ እስከ ደረሰላቸው አካባቢውን ሁሉ ይቃኙታል ። መስኩን ፣ ጻገቱን ፣ ገብታውን ፣ ጀንተረሩን ፣ ጀለቆውን ሁሉ ያማትራሉ ። አትኩረው ያስተውላሉ ። ከመነጽሩም ይውን ተስሉ ከመቁ ረጣቸው የተንጣየሥጋት ስሜት አድርባቸው፣ የየዛፉ ቅርጽ፣ የሣሩ ቀለም፣ የኩረብታው አቀማመጥ ፣ የወንዙ ጠመዝማዣና ወልጊድጋዳ መንገድ ፣ ያጠጠው ጥቁር ቋጥኝ ሳይቀር፣ ሁሉም ነገር ወትሮ ያልነበረ አዲስና ብርቅ ሆኖ ይታያቸዋል ።

መነጽሩን ከዐይናቸው እንደ ተነሱ ይመረምሩና ከሚድት ናጋ ብለው ይቆያሉ ። " እንኮ ውብ እጁ ! ምናል ልጀኝ ብርቱና እንድ ብንሆን ! ሌላውን ንቆ ዐይኑን ከሚተክለብኝ ፣ ይላሉ ከራሳቸው ጋር ።

መንጽሩ ሴላም ሐሳብ ያመጣባቸዋል ። ‘‘የሠለጠነው ሕዝብማ ይኸውና የሩቁን የሚያቀርብ መሣሪያ ፈጠረ ። እኔ ግን ፣ ቅርብ የነበረው ዓላማዩም እየራቀ ሔደብኝ ! ምን ዐይነት እርግማን ነው ?’’ መንጽሩን ወርውረው የሚያሰኝ ምሬት ይሰማቸዋል ።

በዚህ ዐይነት አንድ ቀን ረፋዱ ላይ በሽሎ አፋፍ ደርሰው ከሸለቆው መዳፊያ ጠርዝ ላይ እንደ ቆሙ ፣ መንጽራቸውን ወደ ወንዙ መደብ ሲያ ነጣጥሩ በርከት ያሉ ሰዎች እንቅስቃሴ ተመለከቱ። ወንዙ ባሕር ቢጪ ሠርቶ የተንጣለለበት ስለሆነ ፣ ከመሠረቱ በዚህ መሻገሪያ ላይ ሰውም ከብትም ማየት አዲስ ነገር ባልሆነ ነበር ። ግን በሁለት ምክንያት ለቴ ዎድሮስ አዲስ ነገር መሰላቸው ። የነጋዴው ፣ የሽፍታው ፣ የአረኛ መተ ላለፊያ ቢሆንም ፣ በተለይ ለነጋዴና ለአረኛ የመናኸሪያ ጊዜው አይደ ለም ። በጠዋት ተነሥቶ ሲሔድ የዋለ ከቀትር በኋላ ዐረፍ ይልበታል። ወይም ደግሞ ራቅ ካለ ሥፍራ የመጣ ለማደሪያ ማምሻውን ያርፍበታል። የተመለከቱት ከሁለቱም አልሆነም ።

እርግጠኛ አይሁኑ እንጂ ፣ የተገነዘቡት ሌላ ነገር ብዙዎቹ ሰዎች ለመጠጣትም ይሁን ለመለቃለት ወደ ወንዝ የሚገቡት በመንጣጠል ለየብቻቸው ሳይሆን ፣ እንደ ታሰረ ጨፈቃ ሁለት ሦስቱ በአንድነት መሆናቸውን ነበር ። ብዙ ነገር ያዩትና የደረሰባቸው ቴዎድሮስ ወዲያው ጥርጣሬ አደረባቸው ።

‘‘ታች ተወንዙ ውረዱና ተዘያ ያሉትን ሰዎች ሁሉ ይዛችሁ እም ጡልኝ ። ቢሸሹም ፣ ቢርቁም ተከትላችሁ’’ ሲሉ ያስከተሉትን ሠራዊት አለቃ አዘዙ ።

‘‘ምንድናቸው አባ ታጠቅ ?’’ ሲል ጠየቀ ፣ ድንገት ሽፍታ ቢሆኑ ታች ወርዶ መዋጋቱ እየቀፈፈው ።

‘‘ምንስ ቢሆኑ ። ሒድ አልኩህ ! ተዚህ ታናንሚዬ ሥር ’’ አሉ ቴዎ ድሮስ የመንጽራቸውን ሜዳ እየጠቆሙ ። ‘‘ጠላቴ ተሆነ ቢያመልጥህ ሙት ፣ የኔ ባለሟል አይደለህም ።ወይስ ራሴው ልውረድ ?’’ ሲሉ ዛቱ ።

‘‘አፈ ግያለም አባ ታጠቅ ’’ አሉና ሠራዊቱን ለማሰባሰብ ሔዱ ።

ቴዎድሮስ ፣ ጆሮዋቸውን እንቅተው ቢያዳምጡም፣ አንዳች የጥይት ድምፅና የውጊያ ግርግር ሳይሰማ ፣ ጀንበር ወደ ምዕራብ ዘቅዘቅ ማለት ስትጀምር ማራኪም ተማራኪም ባንድነት መጡ ። የሔዱት ወታደሮች ኻያ ያህል ሲሆኑ ፣ ተይዘው የመጡት ሰዎች ግን ወደ መቶ ይጠጋሉ ። አብዛኞቹ ሴቶች ናቸው ። ከወንዶቹ መካከል ጕራዴና ነፍጥ የያዙት ከእምስት አይበልጡም ።

ተይዘው የመጡት ሰዎች ሁሉ ፣ ዘብ ዙሪያቸውን ቁም ተከማች ተው እንዲቀመጡ ከተደረገ በኋላ ፣ ቴዎድሮስ ዙሪያውን ዐለፍ መለስ በማ ለት አስተዋሉዋቸው ። ‘‘እሺ ምንድን ናቸው ?’’ ሲሉ አለቃ እድርገው የላኩትን ጠየቁት ።

‘‘ነጋዴ ነን ነው የሚለው’’ ሲል የዘመቻው መሪ መለሰ ፣ ከተቀ መጡት ሰዎች መካከል አንዱን በእጁ እያመለከተ ።

‘‘ነጋዴ ? እንዲህ አርጎም ንግድ የለ ። በጥቂት አሀያ ፣ በአንድ በቅሎ በሦስት አጋሰስ መጓት ሴትና የቀረውን ወንድ እየነዳ ምን ይሆን የሚነ ግደው ? ጨው ነው ? እህል ?’’ አሉና ቴዎድሮስ ዙሪያውን እየተመለከቱ ተወራጨ ። ከወንዶቹ ፍርጥም ፍርጥም ያሉት ፣ ከሴቶቹ ልጅ እግሮቹ በጥ ንድ መታሰራቸው ምን ዐይነት ንግድ መሆኑን ያስታውቅ ነበር ።

ከድንጋይ ላይ ቁጭ አሉና ፣ ‘‘ እስቲ ነጋዴውን አምጣው’’ ሲሉ አዘዙ ።

በአለባበሱ ፣ ጥምጥም ፣ ኩታ ፣ ከግያቱ የተነሣ ቀለሙ የማይለይ አብያላ ከኒ እጀ ጠባብ ፣ ሱሪ ፣ ደግ ሁሉንም ያቀላቀለ፣ጠና ያለ ሰው እየ ተገፈተረ ከቴዎድሮስ ፊት ተደፋ ።

‘‘እንዲህ መሆኑ ምንም አይረባህ ። መሬትና ሜማ መሰምህ ለኔ ፋይዳ የለውም ። ይልቅስ ለምንና የት እንደምትሔድ ንገረኝ’’ አሉት ቴዎድሮስ።

‘‘ለንግድ ፣ ለንግድ ነዋ አባ ታጠቅ’’ ሲል አውንም ድፍት ቀና እያለ መለሰ ።

‘‘ከጥቂት ሜንት ስንት በቀር ሸቀጥ አላይም ። ይሽን ሁላ ሴትና ወንድ ነው የምትነግደው ሸቀጥ ? ‘ስንተዋወቅ እንተናነት’ አሉ ። የባር ያን ንግድ ተከለከልኩ ስንት ዓመት ሆነው ? ባርያ የሸጠ ፣ የገዛ እይቀው ቅጣት እንደምቀጣው ታውቅ የለ ?’’

‘‘ባርያኮ አልታዘዝም አባ ታጠቅ ፣ እግዜር ምስክሬ ነው’’ በምሕ ረት ልመና አውንም ደፋ ቀና አለ ።

‘‘የግዜርን ስም በሐሰት አታንሣው’’ አሉ ቴዎድሮስ በቁጣ ። ‘‘ዛዲያ እነዚህ የታሰሩት ሁሉ ምን መሆናቸው ነው ? እንስሶች ?’’ መለስ ብለው የምሬትና የፈዝ ሣቅ ታጣቸው ።

‘‘የሩሳለም ስለምንሔድ መቱማ ድረስ እሻግረን ብለውኝ ነው’’

‘‘እሣር ተወርች ታስረው ?’’

‘‘ሽፍታው እያደባ እንዳንዱን ነጥቆ እየወሰደ ስላስቸገረን ነው፣ አባ ታጠቅ ።’’

“ስሜን አትጥራ ቀጣፊ ! መዋሸትስ ቢሉህ እንዲህ ነው ?”

“አረ እውነቴን ነው ! ” አሁንም መራት ሳመ ።

“እንግዲያው እሺ ይጠየቁ ።”

ሰዎቹ እየተመሩ ቀረቡ ።

“አሁን በእስላም ተይዛለች ። ተባብረን እናስለቅቃት ብላቸው ክር ስቲያን ነን የሚሉት ያውሮፓ መንግሥታት ችላ አሉ።ዛዲያ እናንተ ኢየሩ ሳሌም መሔድ ለምን ፈለጋችሁ ?” ሲሉ ቴዎድሮስ፣ ሰዎቹ ለነገሩ እንግ ዶች መሆናቸው ከአስተያየታቸው ያስታውቅ ነበር ።

“ንገሩኝ እንጂ ፣ ወይንስ አይደለም ?”

“ተየቤታችን ፣ ተየሠፈራችን በማናውቃቸው ሰዎች እየታፈንን መነዳታችንን እንጂ ፣ ኢየሩሳሌም የሚባለውን ነገር ዛሬ ገና መስማታ ችን ነው ። ‘ጽድቁ ቀርቶ በውል በኮነነኝ’ አሉ ። ኢየሩሳሌም ቀርቶ ለቤ ታችን በበቃን ” በማለት አንደኛዉ ሰለ ሌሎች ተናገረ ።

“ዛዲያስ ?” ሲሉ ቴዎድሮስ ፍርጥም ባለ አነጋገር፣ንጋዴ ነኝ ባዩን ጠየቁት። ድምፃቸው የተገታ ይሁን እንጂ እንደ መንቀጥቀጥ የሚሉት ከንፈሮቻቸው ፣ በሰውየው ላይ እንደ ጦር የተተከሉት ዐይኖቻቸው ፣ የታ ፈነ ይመስል ፣ ቁርጥ ቁርጥ እያለ የሚወጣው ትንፋሻቸው ፣ ከውስጥ ቁጣቸው እንደሳተ ገሞራ የሚፈላና የሚያቃጥላቸው መሆኑን ይገልጹ ነበር ። በመገረም ዐይነት ለጥቂት ጊዜ ዝም ብለው ተመለከቱት።“እኔን ጨካኝ ለማሰኘት ነው እንጂ ለንደዚህ ላለው ምንስ ቅጣት ይበቃዋል ?” አሉ ከራሳቸው ጋር ።“ ወደዚያ ውሰድና ዐርባ ግረፈው ።”

ሰውዬው እየተገፈተረ ሲወሰድ ሲል ፣ በሚያስደንቅ ቅልጥፍና ተፈ ናጥሮ ከእግራቸው ሥር ሲንደፋደፍ ነበር፣ ከጣቱ ላይ የሚያብለጨልጨ ውን የወርቅ ቀለበት ድንገት የተመለከቱት ። አሠራሩ ልዩና ለብዙ ዓመ ታት በጣታቸው ላይ አድርገውት የኖረ ስለነበር ለመለየት ጊዜ አልወ ሰደባቸውም ። “ቆይ ቆይ እስቲ ! ተየት አመጣኸው ይኸን ቀለበት?” ሲሉ በጃቸው እያመለከቱ ጠየቁት ። የሚሰጠውን መልስ ለመስማት ያህል እንጂ ፣ አሁን የሰውዬውም መልክ በመጠኑ ትዝ ይላቸው ጀምሮ ነበር ።

ሰውየው መልስ ለመስጠት አመነታ ።

“ተናገር እንጂ በሰው ተነገድክ ፣ መቸም ሌላው ሕሊናህን አይ ከብደውምና ፣ ዘርፈኸው ነው ? ሠርቀኸው ?”

“አረ እርሰዎ ነዎት የሰጡኝ ጃንሆይ ” ሲል በፈራ ተባ መለሰ ።
“የታ ?”

“ደብረ ታቦር ፣ ፊታውራሪ ገብርዬ የሚባሉትን የመር እዝማች ዎንና ሚሽታቸውን ተጭልጋ ይዣቸው የመጣሁ ጊዜ !”

“እዎ ! አሁን እውነትህን ነው !” አሉ ቴዎድሮስ በግስታወስ ወይነት ራሳቸውን እየነቀነቁ ።

ሰውየው ተደፋፍሮ ፣ ለቴዎድሮስ ታማኝ በመሆኑ ምክንያት ፣ የጋረድና የአገው ንጉሤ ሰዎች በየጊዜው ጉዳት ሊያደርሱበት መሞክ ራቸውን እያጋነነ መተረክ ጀመረ ።

“ሌላ ሌላ መወሻከቱን ተወው” ሲሉ ቴዎድሮስ አቋረጡት ። “ብቻ ያን ጊዜ ገብርዬን በደኅና ስታደርስልኝ መልካም ሥራ ሠርተህ ነበር። አሁን ዛዲያ ምን ሆንኩ ብለህ ነው፣አገሬንና ወገኔን የሚጐዳ የተፋት መንገድ የተከተልክው ? መነገዱን ፣ ማትረፉን የከለከልሀ የለ ? ” ሲሉ በትዝብት ጠየቁት ።

መልስ አልሰጠም ።

“ወንጀልና ጥፋት ለመሥራት እንዲያመቻቸው ፣‘ዐፈር ቁሱ ፣ ድን ጋይ ቀቅሱ’እያለ የሚያፋጥጥ መሪ መጣብን ተሚሉት ወስላቶች አንዱ መሆንህ አይደለም ? እኔማ እንግዲያው ለሠራኸው መልካም ሥራ ውለታ የጣቴን ቀለበት ሰጥቸህ ነበር ፣ ቀራጭ እንዳያስችግርህም ይረ ዳሃል በማለት ። አንተ ግን መልሰህ እጂን ነክሰኸው ። እንዲያውስ ማን ያውቃል ፣ ለበጎ ሥራ የሰጠሁህን ቀለበት ለባሪያ ንግድህ ከላ ግለፈያ አድርገኸው ይሆናል ። እሚገርም እኮ ነው !” ቴዎድሮስ ለጥቂት ጊዜ አሰብ አደርገው ፣ “ እንዲያውም ስለ ቅጣቱ ሐሳቤን ቀይሬአለሁ ። ሁለተኛ ወገኑን እያሰረ ባሪያ አድርጎ እንዳይነዳበት ሁለት እጁን ቁረ ጥና በአንገቱ ላይ አንጠልጥለህ ልቀቀው ። ለእንደዚህ ያለው ተዚህ ያነሰ ቅጣት አይገባውም” ሲሉ አዘዙ ።

አንዱ ወታደር፣ የሰውየውን እጅ የኋሊት ጠምዝዞ ቀለቡቱን ለማ ውለቅ ሲሞክር ተመለከቱና ፣“ተው ! ምንም በተግባሩ ቢያረክሰው እንጂ የሰጠሁትንማ መልሼ አልወስደው ። ታንገቱ ላይ አንጠልጥሉ ያኒዋ በት ” በማለት ከለከሉት ።

የታሰሩት ተፈትተው እህል ውሃ ሲሰጣቸው ፣ ሌሎቹ ለጥያቄ እን ዲቀርቡ ተደረገ ። ሦስቱ ነፍጣቸውን ፣ እንድ አራቱ ጐራዴያቸውን ተገፍፈው ስለ ነበር ሁሉም ጀለዎች ሆነዋል ።

“እነዚህ መሣሪያ ይዘው ነበር” ሲል የተላኩት፣ ወታደሮች የመ ራው አለቃ በእጅ እየጠቆመ አመለከተ። አባ ታጠቅ ግን ፣ የሚናገረው ንም ሆነ የሚያመለክተውን እምብዛም አይከታተሉም ነበር። ዐይናቸው ከአንድዋ ልጅ እግር ሴት ላይ ተተክሎ ፣ አስተያየታቸው ግን የጠፋባቸው

አንድ ነገር የሚፈልግ ይመስላል ። እቸፈር ዘመቻ መሔዱን ላፍታ ዘነ ግተው ፣ "ገብርዬ !" ሲሉ በመጥራት ዙሪያቸውን ቃኙ ። ትዝ ሲለ ቸው ተዉትና ፣ "አንቺ የታንጉት ልጅ አይደለሽም ?" ሲሉ በጥርጣሬ ጠየቋት ።

"አዎ ! አባ ታጠቅ ።"

"ዛዲያ ተነዚህ ጋራ ምን አብሮ አመጣሽ ? መቅደላ አምባ ገብተው ነበር ግለት ነው ?" ሲሉ በመገረም ጠየቋት ።

"እሜቴ አዘውኝ እሳቸው ናቸው ያመጡኝ" አለች አንገቷን ወደ ጐን ጠምዘዝ አድርጋ ፣ ባለጥምጥሙን ሰውዬ እያመለከተች ።

ማንነቱን ለማረጋገጥ ዐይናቸውን ላንዳፍታ በእርሱ ላይ ማሳረፍ ብቻ በቃቸው ። መቆጣት ቀርቶ መናገር ታከታቸው ። አገጫቸውን ከመ ዳፋቸው ላይ አስደግፈው፣ ከፊታቸው የተደቀነባቸውን ትርዕይት ማየት ያልፈለጉ ይመስል ዐይናቸውን ከደን አድርገው ፣ ባንድ እጃቸው ጭፍ ርር ያለ ቁንዳላቸውን እያፍተለተሉ ዝም ብለው ቆዩ ። በእካባቢያቸው የነበረውም ሁሉ የሠቀቀን ጣዕራቸው ተሰምቶት አብሮ በዝምታ ተኩ ማተረ ። ጸጥ ረጭ አለ ። "አሁንም አንተው ነህ ?" አሉ ቆይተው ቆይተው ከሩቅ ዓለም የመጣ በሚመስል ድምፅ ። ለሰውየው ሳይሆን ለራሳቸው ያቀረቡት የመገረም ዐይነት ጥያቄ ነበር ።

መልስ አልሰጠም ። ጨርሶ ተስፋ በመቁረጥ ላመል ያህል አንገቱን ቀልበስ አድርጎ፣ የሚሠነዘርበትን ሰይፍ የሚጠባበቅ ይምሰል እንጂ ብርኩ እንደ መንቀጥቀጥ ሲል ከሱሪው በላይ ያስታውቅ ነበር ።

"ለመሆኑ ይኸ ሰይጣን ማን እንደሆነ ታውቃላችሁ ?" ሲሉ ቴዎ ድሮስ በዙሪያቸው የቆሙትን ጠየቁ ።"ወይኒ ላይ ሕዝብ ያስጨረሰ ፣ ያስጨፈጨፈ ፣ ጋረድን በምኞት እንደ ፈረስ እያስጋለበ ደባርቅ ላይ ያንን ሁላ ሕዝብ ያስጨረሰ ፣ ለጥፋት ለተንኮል የተፈጠረ . . . እሱ ነው" ከሐሳብ ተመስጦ መለስ ሲሉ አንጋገራቸው ከረር ማለት ጀመረ። "ዛዲያ እንደዚህ ያለውን ተሰይጣን የከፋ ሰይጣን ፣ ተባብ የባሰ መርዘኛ ምና ርገው ትሉኛላችሁ ?"

የፍርድ ትችት ፣ ከዚህም ከዚያም ተሰነዘረ ።

"ተሰቅሎ ሲሞት ይታየኛል ።"

"እንደዚህ ያለው ግፈኛ አረመኔ በሰም ተነክሮ እንደ ጧፍ ይቃጠ ላል ፣ ይነድዳል ።"

"በፍትሐ ነገሥት እንደ ተጣፈው ፣ በድንጋይ ተወግሮ ይሞታል ።"

"ተመክዳት አንሥቶ እስተ ማሸፈትና እስተ መሸፈት ፣ ተዚያም አንሥቶ ሰው እስከ ማስገደል ፣ እስከ መግደል፣ እስተ ማስፈጀት ፣ የሰው ንብረት እስተ መዝረፍ፣ በአባ ታጠቅ ላይ እስተ መዋሸት፣ እረ ምኑ ቅጡ! ስለይህም ሁላ በብሉይም ፣ በሐዲስም ፣ በጓላም በፍትሐ ነገሥት የተደ ነገጉትን ጥፋቶች ሁሉ ሠርቷል ፣ ፈጥሟልና በሁላውም በየተራ ሲቀጣ ይታየኛል ።"

"ሐሳቡ ጥሩ ነው" አሉ ቴዎድሮስ በመገረም እኳኋን ፣ " ግና የዘረ ዘርካቸው ጥፋቶች በሞት የሚያስቀጡ ቢሆንስ ? አንድ ሰው ስንት ጊዜ ይሞታል ? አንዱ ከገደልከው በቃ አይደል ?"

"አሃ ! አሃ" ፍርድ ሰጭው ትንሽ ግራ ተጋባና ነቃ አለ ። "የሞ ቱን ቅጣት አቆይቶ በሌላ በሌላ መቅጣት ነዋ !" ሲል አስተካከለ ።

ቴዎድሮስ ፣ የብዙዎቹን ፍርድ ዝም ብለው አዳመጡና በተለይ የመጨረሻው ትንሽ ቢያስገርማቸውም ፣ የሁሉም ያላጠገባቸው መሆኑን በሚገልጽ አኳኋን ራሳቸውን ነቀነቁ ። "እያችሁ ? አሁን ይኸ ምኑ ይገደ ላል ?" አሉ ዐይናቸውን በአከሊሉ ቁመና ላይ ተክለው ። "ምናልባት አታውቁትም እንጂ የሞተ ሙት እኮ ነው ። እንደ መቃብር ጋኔን ለመ ልከፍ፣ ለማጥፋት ብቻ ነው እኩይ ትንፋሽ የሚተፋው ። የቀትር ምታት ምኑ ይገደላል ? ለእንደዚህ ያለው ለሥራው የሚተካከል ምንስ ቅጣት ይገኝለታል ? የሚገርመኝ ፣ እኔም እስታሁን ማስወገዱ ሳያቅተኝ ፣ ያች ምንትዋብ የሚሏት አሚናና ይኸ ጋኔን እንዲህ እኔን ነክሰው አለቅም ያሉበት ምህኖት ነው ። ያች እንኳን ተበደልኩ ብትልም ክፋትዋ ታፍ ልፍለፋዋ አያልፍም ። ይኸ ግን ፣ ይኸ ግን . . . " የታከቱትን ያህል፣ የተ ከዙትን ያህል ፣ የታገሡትን ያህል ፣ ሳይፈልጉ ጣታቸውን ቀሠሩበት ። 'ባንድ ልባቸው . . እባክህ አሉ ተዚህ ሁሉ ገላግለኝ' እያሉ ፣ በልባቸው እየተማጸኑ ። " ወዲያልኝ ! " ድንገት እጃቸውን በግወራጨት ።

"ምን ላርገው ዛዲያ አባ ታጠቅ ?" ሲል የወታደሮቹ አለቃ ጠየቀ።

ከመ ቅጽበት ይሠነዘራል ብሎ የጠበቀው ሰይፍ በመዘግየቱና ንግ ግር በመቀጠሉ ፣ አክሊሉ አንዳች ቅንጣት ተስፋ ዘርቶበታል። " ይፈቀድ ልኝና ልናገር" አለ በለዘብታ አነጋገር ።

"ምን ? ደሞ አሁንም መርዝህን ልትረጭ ?" አሉ ቴዎድሮስ የሚ ተናነቅ ስሜት ያመቀው በሚመስል ድምፅ ። "እረ ሰዎች ፣ እንድ በሱና ተፈቴ አስወግዱልኝ !" ማስወገድ የሚለው ቃል በመጨረሻ ቅጣትነቱ የገባቸው ወታደሮች ጐራዴ እየመዘዙ ፣ ነፍጥ እያጐረሱ አክሊሉን በግ ዳፋት ዘወር አድርገው ሲወስዱት ፣ ቴዎድሮስ አንድ የረሱት ነገር ትውስ እንዳላቸው ዐይነት ፣ መዳፋቸውን ከግንባራቸው ለጠፉና ፣ "እስቲ እስቲ ቆዩ" ብለው ወደ እርሳቸው እንዲቀርብ አደረጉ ። "ሰው

ተሆንክ ፣ ለነገሩ ሰይጣንም ቢሆን ምሥጢሩን ይገልጣ ልይላሉ ፣ አንድ ነገር ብቻ ንገረኝ ። ታንጉትን ምን አድርገሃት ፣ እንዴት ተመቅደላ እንደ ወጣህ ብቻ . . . ”

አክሊሉ ተጠፋ አይቀር ይዞ ለመጥፋት ፣ ምሕረት የሚያገኝም ተሆነ መናገሩ ሊያሥምረው እንደሚችል ተስፋ በማድረግ ፣ አክሊሉ ቴዎድሮስን ከሰዎቹ መካከል ወደዳር አየመራ ሔደና ተረከላቸው ።

ቴዎድሮስ ፣ ሲያዳምጡት ሕይወት ካለው ሰው እንደበት የሚወጣ ድምፅና ቃል አልመስላቸው አለ ። አክሊሉ የሠራውን ፣ የሆነውን ሁሉ ርቱዕ በሆነ አንደበት ይተርካል ። ግን በአንጋገሩ የጸጸት ቁርቶ የጥላቻ ወይም የበቀል ስሜት የለውም ። ሰው ይቆጣል ፣ ሰው ይናደዳል ፣ ሰው ያዝናል ፣ በዚህም ስሜቱ ድርጊቶች ይፈጽማል ። አክሊሉ የተረከላቸው ግን ፣ እንደ ተመልካች በመሰለ የያመነፍስ ወይም የበደን አነጋገር ነበር ። ቴዎድሮስ ፣ ሁናቴው ከማስገረም ዐልፎ አጠይፎዋቸው ወደ ሰዎቹ ይዘውት ተመለሱ ።

“እንዳትገድሉት ! ሙት ነው ። ምኑ ይገደላል ? በዚህ ላይ አውን ሳስ በው በሕይወት ለሱ የሚበቃ ቅጣት ዐይነትም ያለ አይመስለኝ ።”

ወታደሮቹ ምን እንደሚያደርጉ ግራ ተጋብተው ዝም ብለው ቆሙ። “እንዲያውም” አሉ ቴዎድሮስ አዲስ ሐሳብ እንደ መጣላቸው ለጠቅ አድ ርገው ። “እንዲያውም እሱው ራሱ ይወስን ። ገመድ ወይም መጫሻ ስጡት ። እልሞትኩም ፣ ሕይወት አለኝ ፣ ልብ አለኝ ፣ ሐሞት አለኝ ታለ ያሳየን ። የቢሠውርን ታሪክ መቸም ሳትሰማው አልቀረህም ” አሉ ወደ ኣክሊሉ አተኩረው። “ተሉ ብለህ ታታተህ ግን ፣ መቸስ ምን አደርጋ ለው ? በድንነትህን ራስህ መለከርክ ማለት ነው ። አዎ ፣ አልሆንለት ታለ በደኑን ነውና በቱሙ ቅበሩት ።”

ቴዎድሮስ፣ የፍርዳቸውን ውጤት ማየት ያልፈለጉ ወይም ሥፍራውን ደንገት የተጸየፉት ይመስል ፣ ወዲያው ዘወር ብለው መንገድ ጀመሩ ።

“ሌሎችንስ ምን እናርጋቸው አባ ታጠቅ?” የሚለ ጥያቄ ከኋላ ቸው ተከተላቸው ።

“ እንዳሻቸው ልቀቁዋቸው ” አሉ ቴዎድሮስ በታከተ አንደበት ። ወደ ታንጉት አገልጋይ በእጃቸው እያመለከቱ ፣ “ አንቺ ደሞ እስቲ ነይ ። ታሪኩን ልስማው ” አሏት ።

አክሊሉ ፣ ከተመረጠለት ዛፍ እግዳሚ ግንድ ላይ ገመዱን አስሮ መሸቀቆውን እንደ ምንም ከአንገቱ አስገባ ። ግን እግሩን ከተቆናጠጠ በት ቅርንጫፍ ላይ መንቀል አቅቶት ነፍስ ውጭ ፣ ነፍስ ግቢ በጣ ዕረ ሞት ዐይነት ብዙ ተንዘፈዘፈ ። በመጨረሻ በደመ ነፍስ ጅው

ብሎ ሲወረወር ፣ ከሱሪው ሥር ርዥበት መታየቱ ግምሻውን በሠፈር ሲወራ ቴዎድሮስ አልሰሙም ። ፍርድ እንደ ሰጡ የታንጉትንም ጉዳይ ለማጣራት ጥቂት ራሳቸውን ወደ መቅደላ ጉዞ ጀምረው ነበር ።

ገብርዬ ፣ ከአቸፈር ዘመቻ ተመልሶ የአክሊሉን ፍጻሜ እንደ ሰማ፣ በመገረም መልክ ለቴዎድሮስ አነጣባቸው ። “እንዲያው ለመጨረሻ ጊዜ መልኩን ባይ ደስ ይለኝ ነበር ” አለ ።

“ሰይጣን ማየት ምኑ ደስ ያሠኛል ብለህ ገብርዬ ?”

“እውነትም ሰይጣን ። ያንን ሁሉ ጠባቂ ዐልፎ እንዴት ከመቅደላ መውጣትስ ቻለ ? ሰይጣን ቢሆን ነው እንጂ ” ገብርዬ በመገረም ራሱን ነቀነቀ ።

ቴዎድሮስ ፣ በትካዜ ተውጠው ዝም ብለው ቆዩ ። ቀደም ሲል ሊን ግሩት ወስነው ነበር ። ራሳቸው የተሳቀቁትን ያህል ገብርዬንም አብር ሳሳቀቁ መልሶ ከበደባቸው ።

“መቸም ጠባቂዎችን በገንዘብ አታልሎ መሆን አለበት” ሲል ገብርዬ ቀጠለ ።

ቴዎድሮስ ፣ በቅሬታም በማስተባበልም ዐይነት ራሳቸውን ነቀነቁ ። “እውነቱን ማወቅ ትፈልጋለህ ገብርዬ ?” ሲሉ ጠየቁት ፣ ዕዳውን መወ ጣት እንደማይቀርለት መርዶ ነጋሪ ድንገት ቄርጠው ።

ገብርዬ ፣ የቴዎድሮስ አጠያየቅ ግራ አጋብቶት በመገረም ተመለከ ታቸው ።

“ጉዱ ተኛው ነው !” አሉት ።

አሁንም ሊገባው አልቻለም ።

“አዎ ! ታንጉት ናት እንዲወጣ የረዳችው !” አሉና ቴዎድሮስ በሰ ፊው ተነፈሱ ።

“ምን ?” ሲል ጮኸ ገብርዬ ። “ምን ነካት ? ምን ሆንኩ ብላ ? እሬ ምን ነካኝ ብላ ? እኮ ምን ነክቷት ?” እያለ ከመደጋገም በቀር የሚናገ ረው ጠፋው ።

“ማን ያውቃል ገብርዬ ? ጊዜ ምሥጢሩን ይፍታልን እንጂ !” አሉት በማጽናናት ፣ ትከሻውን ጨበጥ አድርገው ።

“እ - እሷስ ?” ገብርዬ አንዳች ስሜት እየተናነቀው ፣ መልሱን መስማት ያልፈለገ ይመስል ጥያቄውን አቋርጦ ተወው ።

"እባም ራፅ ጠፍታለች" አሉ ቴዎድሮስ በሐሳብ እንገታቱውን ደፉ አድርገው ። ከራሳቸው ጋር የሚጯጉቱ ይመስላሉ ። በመጨረሻ ጉዳዩን ከሐሳባቸው ያሰናበቱ በሚያስመስል መልክ እንድ እጃቸውን ወንጨፍ አደረጉ ።

ከዚህ በኋላ ፣ እንደማያነካ ቅዱስ ታቦት ወይም ርኩስ ነገር ቄጥረው የተዉት ይመስል ፣ የታንጉትን ጉዳይ ሁሉም ሌላ ጊዜ አላነሡትም ።

—7—

"ሳብ ! ሳብ ! ጉበዝ በርታ ! እረ ጉበዝ በርታ ! ሳብ ሳብ ! ባንድነት ሳብ ! ጉበዝ ግፋ ! ሳብ ጉበዝ ! . . . " እራፊ ጨርቅ ከራሱ ላይ አስሮ ነጠላውንና ድጉን ከወገቡ ላይ የጠፈረው ቀስቃሽ ፣ ዳር ዳሩን እየተራወጠ ሳንቃው እስኪዘጋ ድረስ ያበረታታል ። ይዘልፋል ። አንዳንዱም ለማ ሰፈራራት ያህል አሰንጋውን ወይም ዳላውን ያወዛውዛል ።

ቴዎድሮስ ፣ እንዴ አሰፈላጊነቱ ከወያፈትም ፣ ከወያ ኃላም ከመሻል ገደማም እየተገኙ የጉዞውን እንቅስቃሴ ይመራሉ ። ይቆጣጠራሉ ። መን ኩራኩሩን ፣ ገመድና መጫኛውን ይፈትሻሉ ። የዛሰ ሰውነት ሲያዩ "ምነዋ ! እንዲህ አርገህ አትሰበውም ?" ብለው ራሳቸው ይገበጡበታል። እንገብርዬ ፣ እንገልሞ ፣ እን ዓለሜና ሌሎችም የጦር አበጋቦች ፣ "እግ እያለን አባ ታጠቅ !" ሲሉ ተረባርበው ያስየሱዋቸዋል ። ዓለማየሁ ከአጠገባቸው ቁስ — ቁስ ይላል ። ከብት የተጫነለት ቢሆንም ፣ የአባቱን ድካም ለመጋራት የፈለገ ይመስል ፣ ብዙውን ጊዜ የሚጓዘው በእግሩ ነው ።

ጉዞው ከተጀመረ አንሥቶ ፣ ዘወትር ከፊት የሚተድመው ሲባሰቶኔል የተባለው ትልቁ መድፍ የተጫነበት ባለአራት መንኩራኩር ሠረገላ ነበር ። ለእጅ ጨበጣ እንዳይተርፍና ተመጥኖ በተያራረበ ገመድና መጫኛ ረድፍ ገብቶ የሲባሰቶኔልን ሠረገላ ፣ አቀበት ከፊት ሆኖ የሚስበውና ከኋላ ሆኖ የሚገፋው ፣ ቁልቁለት ላይ ከኋላ እየተሳበ የሚገታው ሰው ከአምስት መቶ ይበልጣል ። ሃምሳም መቶም ሰው የተሰለፈባቸው ሌሎቹ ሠረገላዎች በዚሁ ዐይነት ከኋላ ይከተላሉ ። ከሠረገላዎቹ ሁሉ ኋላ እህል የሚያዘጋጁ ሴቶች፣ ለሥራ የደከሙ ሽማግሌዎችና በሽተኞች ይጓዛሉ ።

ጉድጓዳው እየተሞላ ፣ ጉብታው እየተደለደለ ፣ በጠቅላላው ለመን ኩራኩር የሚሆን መንገድ ቢጠ እየተሠራ ፣ ቆላ ሲወረድ ፣ ደጋ ሲወጣ ለነጠላ እግረኛ ጥቂት ቀናት ብቻ የሚወስደው ፣ ከጋፋት እስከ መቅደላ ያለው መንገድ ብዙ ወራት ፈጀ ። እልህ የሚያጋባ ፣ እልህ የሚያስጨርስ ጉታታ ጉዞ ነበር ።

የእንግሊዝ ጦር ፣ ከምጽዋ ተነሥቶ ወደ መቅደላ በመገሥገሥ ላይ ነው ። የገነቡት የኢትዮጵያ እንድነትም በየሥፍራው ተናግቶ የፃረሳቸው ብቸኛ ሥልጣን ያወጁ ከናፍቾች ተነሥተዋል ። የእንገድ መንገሥት ገዛ ታቸው ከመጥበቡ የተነሣ ፣ ሽፍቶች ከሠፈራቸው አትረቢያ እያጋ እስከ መጣል ደርሰዋል ። በዚህ ሁሉ መሳቀል ለመጨረሻ ፈልግያቸው ወደ መቅደላ የሚያደርጉት ጉዞ ዕረፍት ቀርቶ ፍታዋለና አልተረፈም ።

ጠዛ መርገፍ ሳይጀምር ገና በማለ ሠፈር ያቆለቁላል ። ቀኝመው ተነሥተው "አሰነጣ እንጂ" ብለው ትዕዛዝ የሚሰጡት ቴዎድሮስ ራሳቸው ናቸው። ከዚያም ዕሐያዋ እስኪትበረታ እለቱ ተሰእት ጉዞው ቀጥሎ እህል ለመቅመስ ያህል ይታረፋል ። እንንገሽ ውጣ ውረዱ ፣ ሳብ ጉትቴ ፣ እንደዚሁ ያቆጥላል ።

በዚህ ዐይነት የዘወትር ጉዞ ፣ እንድ ቀን እንደቆበተ ጉሪምሳ ያረፍን የገሰበጠ በሚመስል ጸጥት ላይ ሲሰፍ ውሏው ፣ ጀንበርዋ ወደ ምዕራብ ዘቅዘቅ ሰትል ትልቁ ሠረገላ ከጉብታው አናት ላይ ወጣ ። ግራና ቀኝ ሚዳዋ ያለ ገደል ሆኖ ፣ ሠራዊቱ ከነሠረገላው እንደ ምንም እየተንጠለጠለ የወጣበት አቀበት፣ የኮረብታው አናት ከእንድ ትልቅ አውደማ አደለ ፋም ። ትልቁ ሠረገላ በዚህ ጠባብ ሥፍራ ላይ ያርሶ ሲቆም ሌሎቹ ሠረገላዎች ከኋላ ከአቀበቱ ላይ ተሰለፉ ። ከየመንኩራኩሩ ሥር ከተሻጠው ድንጋይና የግንድ ጉማጅ ጋር ያልጸለ መቆሚያ እስኪገኝ ቀኑን ሙሉ እየሳበ የመጣው ሠራዊት አሁንም ሠረገላዎቹን በመጫንና በገመዱ ገትር መያዝ ነበረበት ።

ትልቁን ሠረገላ ፣ ከኮረብታው አናት ላይ ያደረሱት እርያ ለማለት ያህል ሚን ሚን እየተንፈሱ ፣ ላባቸውን በጨርቃቸውና በእጃቸው ሲጠራርጉ ፣ ከኋላቸው የተከተሉት እያቃሰቱ ተወጥረዋል ። ቴዎድሮስ የኮረብታውን አናት ሁሪያ ገብ ሰትጽበት ታንና ጥቂት አሰቡ ። የኮረብታው ይልጸላ አናት ሁሉንም አጠቃልሎ ማሥፈር አያችልም ። አብዛኛውን ሠራዊትና ዓገ ከነሠረገላዎቹ ከዳገቱ ጥግ ማሳያር ይግሞ አሥጊ ነው ። ወን በያዎች ጥግ ጥጉን መዋተው አያጋ ሊጥሉ ይችላሉ ። ካሁን ቀደምም ሞክረውታል ። ሰው ባያገድሉ ፣ የየመንኩራኩሩን ማስያገፊያ እየፈነቱሉ ቢለቁተስ ? ስንት ዓመት የተደከመበት ሥራ መና ሆኖ ቀረ ማለት ነው ። መድፍ ከሌለ ጀሌ ሆኖ እጅን መስጠት እንጂ የእንግሊዝን ጦር በምን ያፋለሙታል ? የደከመው ሠራዊትም ቢሆን ከየመንኩራኩሩ ሥር እንደ ተኛ ሳይታወቀው በእንቅልፍ ልቡ ማስያገፊያውን ድንጋይና ግንድ ሊያንሸራትተው ፣ ራሱም ቢሆን እየተንከባለለ ገደል ሊገባ ይችላል ።

እጅግ ደፋታ የሆነ አጭር ቁልቁለት ወረድ ብሎ ግን ፣ ለኮረብታው አናት እንጂ ፣ ትከሻ የሆነ ሁሉንም ለማሥፈር የሚበቃ ደልዳላ ሥፍራ መኖሩን ቴዎድሮስ ተመለከቱ ። ሠራዊቱ በድካም መዛሉን አላጡትም ነበር ። የራሳቸውም አካል ቢሆን በመዶሻ እንደ ተቀጠቀጠ ያህል ይሰማቸዋል ። ግን ፣ እንደ ምንም ከደልዳላው ሠፍሮ ማደሩን መረጡ ። "እስቲ በሉ ጉበዝ ፣ ዳገቱን ከወጣን ዘንዳ ቁልቁል ተዚያች መድረስ እያቅ ተንም "አ ሉ በእጃቸው እያመለከቱ ።

ሴባስቶጶል የተጫነበት ሠረገላ ፣ ከደፋታው ጫፍ ላይ እንደ ተጠጋ ከፊት ሆኖ ሲሰብ የነበረው ሠራዊት ከወደ ኋላ ተዛወረና ገመድና መጫኛውን ስቦ ያዘ ። ጥቂት ሰዎች መንኩራኩሩን ወደፊት ገፉ አደረጉት ። መንኩራኩሩን የገፉት ሰዎች ይቸኩሉ ፣ ወይ ገመድና መጫኛውን የያዙት ሰዎች ጨርሰው ይዛሉ አይታወቅም ፣ ድንገት ድብልቅልቁ ወጣ ።ሠረገላው እንደ ደነበረ ከብት ባልታሰበ ፍጥነት ተፈትልኮ ሲሽከረከር ፣ ዳርና ዳሩን ይጠባበቁት የነበሩት ሰዎች ወደ ኋላ ተፈናጠሩ ። ገመድና መጫኛውን ስበው የያዙት ሰዎች እየተጨዋጨዋሁ ለመግታት ቢሞክሩም ብዙዎቹ እየተንሸራተቱ አብረው ወረዱ ። ጥቂቶቹም እየተደናቀፉ በመውደቅ መሬት ለመሬት ተጐተቱ ።

"ጉበዝ ለቀቃችሁት ? ገደል አስገባችሁት ፣ ጉበዝ !" ልጃቸው ውሃ እንደ ወሰደው ወይም ገደል እንደ ገባ ፣ ቴዎድሮስ እየተንደረደሩ ሔደው የሠረገላውን መንኩራኩር ተጋተሩት ። እያላጋ ይዟቸው እየወረደ ፣ ትግል ገጠሙት ። ዓለማየሁ በልጅ እግሩ እየበረረ ፣ እንደ ልጅ እያለቀሰ ከኋላቸው ደረሰ ። "አባዬ ! አባዬ ! ተወው አባዬ !" እያለ ጮኸ ። ቴዎድሮስ ግን ፣ ከተያያዙት ትግል በቀር ምንም ነገር አይ ለማቸውም ፣ እይታያቸውም ነበር ። ያንን መድፍ ፣ ባለ የሌለ ኃይላቸው ካላዳኑ አብረው ገደል ለመግባት የቆረጡ ይመስል ፣ ከመንኩራኩሩ ጋር ትንቅንቃቸውን ቀጠሉ ። ሲያላጋቸው ፣ ሲያሸንፋቸው ፣ "ወይኔ መይሳው !" እያሉ ።

ሠራዊቱ ከደንገተኛ ድንጋጤው ብንን እያለ ፣ የአባ ታጠቅንና የሴባስቶጶልን የመጨረሻ ትግል ሲመለከት ፣ እንደ ጦር እየተወረወረ ገባ። ከመ ቅጽበት አብዛኛው ሠራዊት ከሠረገላው ፊት ተጋፈጠ ።ግማሹ ደረቱን ገፍቶ ሲጋፋ፣ ግማሹ ከሥር እጐንብሶ ራሱን እንደ ጐማጅ እንቅፋት በማድረግ ሊማገድ ሲሞክር ፣ ከመሪውና ከመድፉ ጋር አብሮ ከፍ ጻሜ ለመድረስ የሚረባረብ መሰለ ።

በሰው ኃይል ብቻ ሳይሆን እንዳጋጣሚ በትርምሱ መካከል የሠረገላው አንድ እግር ከተጠረገው ጉዳና ወጥቶ ከዛፍ ግንድ ጋር ተናከሰና ተገታ።ተነፍቶ እንደ ተለቀቀ ፊኛ ሁሉም በኃይል ተነፈሰ።እፎይታው ግን ለአጭር ጊዜ ብቻ ነበር ። በጫጫታው ተውጦ የቆየ የሥቃይ ድምፅ ወዲያው ከያለበት አስተጋባ ። የሠረገላው መንኩራኩር፣መኻል አካላታቸውን

የጨፈለቀው እያጣጣሩ ጩርሱን ይላሉ ። እግራቸው ፣ ቋንጃቸው ፣ ክንዳቸው የደቀቀው ያታስታሉ ። ቴዎድሮስ ራሳቸው ከሚሽከረከረው መንኩራኩር ጋር ሲተናነቁ ፣ ሁለት እጃቸው ተገሽልጦ ልብሳቸው በደም ተነከሯል ። ግን የራሳቸውን ቁስል በሻሽ ጠቅልለው ፣ እየመሩና ትዕዛዝ እየሰጡ ፣ ሠረገሎቹ ሁሉ ቀስ በቀስ ከደልዳላው ሥፍራ እንዲወርዱ ተደረገ ።

ሠፈር ተተክሎ ቴዎድሮስ እየተዘዋወሩ ፈትሸውና ቁስለኞችን እበረታትተው ፣ ከትንሽ ድንኳናቸው በራፍ ከድንጋይ ላይ ዐረፍ ሲሉ ጀንበርዋ በምዕራብ አድማስ መጥለቅ ጀምራ ነበር ። አብሮ ወዲያ ወዲህ ሲል የቆየው ዓለማየሁ ከአጠገባቸው ተቀመጠ ። ለጥቂት ጊዜ አባትና ልጅ ዝም ብለው ተያዩ ። ዓለማየሁ በተለይ ትኩር ብሎ የሚያስተውለው እንደ ማሳ ትልም በፈታቸው ላይ የተሠመረውን የደረቀ ላብ ነበር ። ድንገት ብድግ አለና በእጅጌው ይጠራርግላቸው ገባ ።

"እይደክምህም እንተ የኔ አካል ? ለምን ገብተህ ጋደም አትልም ?" አሉት ጎዘን በተጫነው ቁልምጫ ።

"እንተስ አይደክምህም አባዬ ?"

"እኔማ ትልቅ ነኝ !"

"ትልቅ ብትሆን ዛዲያ ለምን በጣም ትለፋለህ ?"

"እየ የልጅ ነገር ! ምንላርግ ብለኸኝ አካሌ ?"

"ቅድምኮ ሠረገላውን ሩጠህ ስትይዘውና ሲሽከረከርብህ በጣም ደንግጨ ነበር ።"

"ደሞ የምን መደንገጥ አመጣህብኝ !" አሉ ቴዎድሮስ በፈዝ ቁጣ ።

"እስቲ እጅህን አባዬ ?" ሲል እንደገና ጠየቃቸው ፣ በሻሽ የተጠቀለለ መዳፋቸውን በጥንቃቄ እየነካ ።

"ደኅና ነው ።"

"ይኸ መድፍ ያንጊዜ አቃጠለህ ። አሁን ደሞ . . . " ሲል ዓለማየሁ ቅሬታውን አንጠልጥሎ ተወው ።

ሴባስቶጶል ፣ ከቅርጽ ማውጫው ተሠርቶ በወጣ ጊዜ የደረሰባቸውን ማስታወሱ ነበር ። ቅርጽ ማውጫው ሸክላ ተሰባብሮ፣ በሴባስቶጶል ሙሉ አካል ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ዐይናቸው ሲያርፍ ፣ ቴዎድሮስ በስሜት እጅግ ከመዋጣቸው የተነሣ ተንደርድረው ሳሙት ። ግለቱ ጨርሶ አልበረደም ነበርና ትሽሽ አድርጎ ከንፈራቸውን አነፈረው ። ሳምንት ሙሉ ደረቅ ምግብ መጉረስ አቅቷቸው ነበር ።

"ይሽንን መድፍ አትጥላው የኔ አካል" አሉ ቴዎድሮስ የዓለማ የሁ ሐሳብ ገብታቸው ። "የኢትዮጵያ ጠላቶችኮ ሊያጠቅዋት የሚመ ጡት እንደዚህ ያለ መሣሪያ ኃይል ስላገኙ ነው ። ለጀግንነቱ እንደሆነ ፣ እነገብርዬን ፣ እነገልሞን ፣ እነ ዓለሚን ማን ያህላቸው ነበር ? ሌሎቹ ቱርክ ሳይቀር ፣ ተራራ ተሻግሮ የሚጐዳ መሣሪያ ሲኖራቸው እኛ ከጥቂት ነፍጥ ፣ ከጐራዴና ዱላ ገና አልወጣነ ነገር ። ደካማ ያደረገን ይሽ ነው። ለደካማ ማን ይተኛለት ብለህ ? አሁንም እነሆ መጥተዋል ። እስቲ እን ተያያለን" ቴዎድሮስ የመጨረሻውን ቃል የተናገሩት በዛቻ ሳይሆን በእጸት መልክ ነበር ።

በሠፈሩ እሳት ተቀጣጥሎ ፣ ሁሉም በያለበት ወደራት ቢጤው መሰ ማራት ሲጀምር ፣ ምንትዋብ ባንድ እጅዋ ሞሶበ ወርቅ ከደረትዋ አስደግፋ ይዛ ፣ በሌላ እጅዋ ቅል አንጠልጥላ ፣ እየተጣደፈች መጣችና ፣ "እህል ቅመስ ይልቅስ !" አለቻቸው ቴዎድሮስን ፣ ትዕዛዝ ይሁን ግብዣ ባለየ ለት ኮስታራ አነጋገር ።

በድምፅዋ ወውቀዋት "አሁንም አንቺው ነሽ ?" ሲሉ ቀና ብለው በመገረም ተመለከቱዋት ።

የሁለቱ ነገር ጠብ ይሁን ዕርቅ ፣ በቀል ይሁን ይቅርታ የማይለይ እየሆነ ከሔዶ ሰንብቷል ። ዱሮ በአሽሙርና በግጥም ያለማቋረጥ ትወርድ ባቸው ያልነበረውን ያህል ፣ አሁን - አሁን አንድ ጊዜ ስትዘልፍ ፣ ሌላ ጊዜ ታሞግሳቸዋለች ። አንድ ጊዜ ስትወቅስ ፣ ሌላ ጊዜ ታደንቃቸዋለች ። ቴዎድሮስም ቢሆኑ ፣ የዘፈንና የልቅሶ ግጥምዋ እንደ ጦር ያልወጋቸ ውን ያህል ፣ ዓላማቸውን ለማሰናከል ሌሎች ከሚፈጽሙባቸው በደል ጋር ሲያስተያዩት ፣ የምንትዋብን ነገር እንደ ልጅ ልፍለፋ እየቈጠሩት ሔደ ዋል ። ነገርዋ አንድ ውል ያልያዘ በመሆኑ ፣ በቤተ ሰቦችዋ ማለቅ ምክን ያት አእምሮዋ እንደ ተነካ አድርገው የሚመለከቱዋትም ብዙዎች ናቸው ። በተለይ አብዛኛው ሕዝብ ፣ ከደብረ ታቦር ከተነሣ በኋላ ፣ ምንትዋብ ከቴዎ ድሮስና ከሠራዊቱ አካባቢ ባለመለየት በምታሳየው ሁናቴ ፣ "አሁንማ ሊለይላት ነው !" መባል ጀምራለች ። አንድ ጊዜ ሠራዊቱን በዘ ፈን ደኅና ታበረታታለች ። ሌላ ጊዜ ምግብ ከሚያስናዱት ሴቶች መኻል ገብታ ታተራምሳለች ። በዚህ መካከል ግን ፣ በጋፋትም ሆነ አሁን በጉዞ ላይ እንደ ሌሎቹ አጋዥ ሴቶች እካል ሆና መታየት ይዛለች ። ደብረ ታቦር ላይ አንድ ጊዜ እስከነአባቱ ወርፋና ረግማ ያላስለቀሰችውን ያህል ዓለማየሁም ቀስ በቀስ እየተላመዳትና እየቀረባት ሔድዋል ።

"ዝም ብሎ ማሰብ ወንዝ እያሻግርም' ተብሏ ል ። አሁን የእህል ውሃ ጊዜ ነው" አለች ምንትዋብ የጠየቋትን ሳትመልስ የያዘችውን ሞሰበ ወርቅ ከቴዎድሮስ ፊት እያስቀመጠች ።

"ባያሰኝኝስ ?" ሲሉ በቀልድ ፈዝ ጠየቋት ።

"እይዙህ አትፍራ ።"

"ምኑን ?"

"መርዝ እንዳላደርግብህ ብለህ እንደሆነ ።"

"ግን ያውቃል ?" አሏት አሁንም በቀልድ መልክ ።

"እኔ ምንትዋብ ! የሆነው ይሁን እንጂ በመርዝስ አልገልህም ! ጭራሽ !"

"እህሳ ?"

"በሌላውማ ወንድ ብሆን ነበራ !" ስትላቸው ቴዎድሮስ ፈገግ አሉና ሞሶበ ወርቁን ጠጋ አደረጉት ።

"ግና እንደዚህ አለቅህም ብለሽ የምትከተይኝ ለምንድን ነው ?" ሲሉ ጠየቋት ።

"የበደልከኝን ስታውቀው ትጠይቀኛለህ ? ጥላህ ሆኛ ገና እስከ መቃብር እከተልሃለሁ ።"

"በግል ፍላጎቴ አይደለ ! ያገር ጉዳይ ሆኖብኝ ነው እንጂ" አሉና ቴዎድሮስ በቅሬታ ላፍታ ሐሳብ ያዛቸው ። "ጥላ ? ጥላ አልሽኝ ? ጥላኮ የሚኖረው ብርሃን ሲኖር ነው ። እኔ ግን ጀንበሬ እየጠለቀችብኝ ምን ጥላ አለኝ ብለሽ እንግዲህ ! እስቲነ'ሳሌው 'ጥላ ቢስ' ይባል የል ?"

"እሳትም ፣ መብራትምኮ ጥላ አለው" ስትል ላለመረታት ተከራ ከረች ።

"ማን እንደ ጀንበር !" ቴዎድሮስ እንደ መተከዝ አሉና ለጠቅ አርገው ፣ "እና እስከ መቃብሬ ትከተይኛለሽ ? ልታለቅሽብኝ ነው ? ልታ ለቅሽልኝ ?" ሲሉ ጠየቋት ።

"እንደሆነው ። መጀመሪያ እስቲ ለዚያ ያብቃህ !" አለች በቀልድ መልክ ።

"ምን ብለሽ ?"

ጥያቄውን ያልሰማች በመምሰል "ብላ አንተ ልጅ ! እንዳባትህ ዝም ብለህ ቆዛሚ አትሁን" ስትል ቆሎ የያዘውን ሞሶበ ወርቅ ወደ ዓለ ማየሁ አስጠጋችለት ።

"ንግሪኝ እንጂ !" አሏት በድጋሚ፣ "እኔ ስሞት ምን ብለሽ እንደ ምታለቅሽ ?"

"ሰው ሲሞት ምን ተብሎ እንደሚለቀስለት አስቀድሞ መስማት አለበት ? አሆሆ ! እንዲህ ያለ ጉድ ሰምቸም አላውቅ " አለች በውሸት መኮሳተር ።

"ተሞትኩ በኋላማ ዛዲያ የታባቴን እሰማዋለሁ ። ይልቅስ አሁን ንግሪኝ ።"

"አሆ ! ተልጅ ፊት ስለ ሞት አይወራም ። ነውር ነው ።"

"እንዳይፈራ ነው ? የኔ እካል ሞት ትፈራለህ ?" ሲሉ ዓለማየሁን ጠየቁት ።

"ታንተ ጋራ ተሆንኩ አልፈራም !"

"እሰይ የኔ አምበላ ! ይሽውልሽ ! በይ ንግሪኝ ! " ለመሔድ ቃጣች።

"ቆይ ንግሪኝ እንጂ ! በሕይወቴ እያለሁ እንዲያ እየወረድሽብኝ ተሞትኩ በኋላ ለምትይኝ እንዳልቆጣ ነው ?"

"ብትቆጣ ማን ይፈራል ?"

ቴዎድሮስ ሣቅ አሉ ። "ደፋር ተሆንሽ ንግሪኝ !" የቴዎድሮስ ውት ወታ ከሞቱ በኋላ የሚባሉትን ለማወቅ ጓጉተው ሳይሆን ፣ ከጥቂት ጊዜ በፊት በደረሰው አሰቃቂ አደጋ እጅግ የተጫናቸውን ስሜት ተለል የሚ ያደርግ ሌላ ጭውውት ለማምጣት ያህል ነበር ።

"ምን ቸገረኝ !" ላንዳፍታ አሰበችና አመጣችው ።

"አባ ታጠቅ ብሎ ለምን ስም አወጣ ፣

ፈረንጆች ሲመጡ ተሥራው ተታጣ ?"

ቴዎድሮስ ሳያስቡት ክት ብለው ሣቁ ። "አሆሆ ! ይህማ ሽሽህ ማለትሽ ነው ! "

ምንተዳዬ እንደ ማለት ትከሻዋን ሰበቅ አድርጋ ሠፈርዋ ሔደች ።

የቴዎድሮስን ድንገተኛ የሣቅ ድምፅ የሰሙ ሁሉ ፣ በመገረም ጆሮዎ ቻቸውን ቀና አደረጉ ። ጦርነትና ድሉን አብረዋቸው ከተካፈሉት ባለሟ ሎቻቸው መካከል ብዙዎቹ በየራሳቸው ፈገግ አሉ ። የዛሬን አያድርገውና ሕይወታቸውን በተስፋና በደስታ የሚያቀጣጥል ድምፅ ነበር ። አሁንም ድጋሚ አልሰሙትም ። ብልጭ እንዳለ ወዲያው መልሶ ድርግም አለ ።

"ፈረንጆች ሲመጡ" የሚለው የምንትዋብ ቃል ሠቀቀናቸው ውስጥ መልሶ ዘፈቃቸው ። የሀገራቸውን ቅዱስ መሬት ረግጠ ካረከሰው ጠላት ጋር የሚያደርጉት ፍልሚያ ከፊታቸው ድቅን አለ ። ለዚያ ፍል ሚያ በሚያረገው ጉዞም በዕለቱ እንደ ደረሰው አደጋ ሁሉ ፣ ነገ ከነገ ወዲያ ከዚያ በስቲያ የሚጠብቃቸው ከባድ ትግል ታሰባቸው . . . "በዕለቱ አደጋ የሕይወቴ ፍጻሜ ቢሆን ኖሮስ ?" የሚለው ጥያቄ በአእምሮዋቸው የመጣው በዚህ ቅጽበት ነበር ። ዓላማቸውን ፣ ሕልማቸውን ፣ ሳያዩ ያልፉ ነበር ። ለነገሩማ ሕልሚና ዓላማዬ ጨልሞብኝ የለ ? ታትሚ በላይ ተሆነብኝ መቸስ ምን አደርጋለሁ ? አሉ ከሐሳባቸው ጋር ። "እንደ እኔ ማለም ፣ እንደኔ ግቀድ ብቻ ሳይሆን ፣ ያቀደውን ለመጀመር ፣ የጀ መረውን ለመጨረስ ፣ ጊዜውም ሁናቴውም የተሻለ ዕድል የሰ ጠው መሪ ያምጣልሽ እንጂ ሀገሬ !" ሲሉ ተመኙላት ።

በዓላማቸው የተቆራኙዋቸው ሰዎች ዕድልስ ? የእያንዳንዱን ለማየት ሞከሩ . . . እንግዳ ሽምገል ብለዋል ። በዚህ ላይ ብልጥም ወላዋይም ስለሆኑ ይዘልቁት ይሆናል ። ዓለሜ ጀግናም ብልህም ነው ። መንገዱን እያጣም ። ገልሞ ፣ በዘሩ ምክንያትም ሆነ በእልኸኝነቱ ትንሽ ገለልተኛ ስለሆነ፣ ከተ ከፋ ተመልሶ ጭልጋ በመውረድ የዱሮ ኑሮውን መቀጠል የሚችል ወይነት ነው ።

ከገብርዬ ላይ ሲደርሱ ከሁሉም የከበደ ሐሳብ ያዛቸው ። ገብርዬ ጀግና ነው ። ቅንጣት የማይጠረጠር ታማኛቸውም ነው ። ራሳቸው ለዚህም ነበር ምሥጢሩን ሁሉ ሳይገልጹለት ታንጉትን ያጋቡት ። ተዋበችን እንዳገኙ ፣ የሚያምኑዋትን ፣ የሚተማመኑባትን ሚሽት የሰጡት መስሏቸው ነበር ። በእርግጥም መልካም ሚሽት ሆና ለት ነበር ። በመካከላቸው ጥሩ ፍቅር እንደነበርም ተገንዝበዋል ። ዛዲያ በዘርዋና በመካንነቷ ምክንያት ከጥፋት ላይ ወደቀች ። የሆነውን ሁሉ በዝርዝር ገልጸውለት ቢሆን ኖሮ ይሻል ነበር ? ከራሳቸው ንዴት በተ ቀር ፣ ሠቀቀኑንና ጎዘኑን አይችለውም በማለት ነበር የተዉት ። በነገሩት ብቻ ስንኳ ከፍተኛ ትካዜ እንዳደረበት ሰሞኑን ከሁናቴው አስተውለዋል። ፈታቸውን ለማየት ያፈረ ይመስል ፣ ግድ ካልሆነበት በስተቀር ከእጠ ገባቸው መገኘቱን እየተወው ነው ። አሁን እንዳይነግሩት ጊዜው አለ መሆኑ ተሰማቸው ። በጦርነት ዋዜማ ላይ ለዘመቻው ይዘጋጅ ? ወይስ ጸጸት ያስታምም ?" አዎ ! የሁላችን የግል ሕይወት በሀገራችን ሕይ ወት ላይ የተመሠረተ አይደለ ?" ሲሉ ያመዷሙ ።

ሌሊቱ ገፋ ። ሰዉም በያለበት እየተጋደመ የድካም እንቅልፍ ወሰ
ደው ። ዓለማየሁ ፣ ከአባቱ ጭን ላይ ደገፍ እንዳለ ሽልብ አደረገው ። በየ
ሥፍራው ሲነድ የነበረው እሳት ፣ ማገዶው እያለቀና ቆስቋሽ እያጣጠፋ ።
አካባቢውን ጨለማና ጸጥታ ነገሠበት ። የጠፋ ሕልማቸውን ፣ ያመለጠ
ዓላማቸውን የሚፈልጉ ይመስል ፣ አባ ታጠቅ ብቻ ከትንሽዋ ድንኳናቸው
በራፍ ተቀምጠው ዐይናቸውን በጨለማው ላይ እንደ ተከሉ ቀሩ .....

ተፈጸመ

ድኅረ ታሪክ

ገብርዬ ፣ በወርቀ ዘቦ የነደደ ያንበሳ ቆዳ ለምድ ለብሶ ፣ እንፋሮ
ደፍቶ ፣ ጣምራ ጦር ይዞ ወታደሩን እየመራ በቴዎድሮስ ፊት ሲያልፍ ፣
“ናማ እስቲ አንደዬ ገብርዬ ” አሉት ቴዎድሮስ ። ነጠል ብሎ ወደ ቆሙ
በት ሔደ ።

በስንት መከራ ከጋፋት ከመጡት መድፎች ትልቁና ከፍተኛ ግምት
ጥለ ውበት የነበረው ሲባስቶጳል ፣ ሁለት ጊዜ ከተተኰሰ በኋላ በሦስተኛው
ፍርክስክሱ ወጥቶ ወድቋል ። የቀሩት አነስተኞቹ የሚተኩሱት አለሎ
ከሚላማው ሳይደርስ ከወደዚሁ እየቀረ ፣ በባዶ ሜዳ አቧራ ያስነሣል ። የአ
ንግሊዝ ጦር ታች እሮጌ ላይ ሆኖ የሚተኩሰው ግን የቴዎድሮስን ሠፈር
ያደባልቀዋል ። ሬሳ በየቦታው ወድቋል ። ቁስለኛ በያለበት ። በሩቁ ከፍ
ተኛ ጉዳት የሚያደርሰውን መሣሪያ ስላልቻሉት ፣ ከእንግሊዝ ጦር መኻል
ገብቶ ለመዋጋት ገብርዬ ሠራዊቱን እየመራ ወደ እሮጌ መውረዱ ነበር ።
ከንዱን ይዘው ወደ ጐን ወሰዱትና አንጀት በሚበላ አዘኔታ ተመለከ
ቱት ። “እንግዲህ መቸም የምንሆነው አይታወቅምና ልሰናበትህ ብዬ
ነው ። ለመሆኑ ታንጉት የደረሰችበትን ታውቃለህ ?” ሲሉ ድንገት ጠየ
ቁት ።

ባልሆነ ጊዜ ያልሆነ ጥያቄ ስለ ቀረበለት ትከሻውን ነቅነቅ አድርጎ፣
“ምናባቷን ደሞ ዐውቄላት ?” በማለት መለሰ ።

“ዘጌ መቃብር ቤት ነው ያለችልህ ። በደኅና ተተመለስክ እኔም
ባልኖር ሔደህ አምጣት ፤ ይበቃታል ።”

“ምን ዕንቆቅልሽ ነው የምትነግረኝ አባ ታጠቅ ?”

“ምንም ዕንቆቅልሽ የለበትም ። በቅጣት ነው ያጋዝኳት ። ለምን
አልነገርሽኝም ብለህ አትቀየመኝ ። ሌላም ያልነገርኩህ ነገር አለ ። ጥፋ
ትዋ ከባድ ቢሆንም ፣ እኔም የበደልኩዋት መስሎ ቢሰማት ደግሞ አል
ፈርድባትም ።”

“ደሞ ምን በደልካት ፣ አቀማጠልካት እንጂ !”

ቴዎድሮስ ለጥቂት ጊዜ በትካዜ ተመስጠው ቆዩና ፣ “እጎቴ እስ
ናት !” አሉ በመጨረሻ ።

“ምን ?” የገብርዬ አንጋገር ከጥያቄ ይልቅ የግራሜና የድንጋጤ
ዐይነት ነበር ።

“አም ! የእጎቴ ልጅ እጎቴ ፣ አባቴ ለአደን ሲዘዋወሩ ወይኒ ላይ
ከሌላ ሴት የወለዱዋት የእጎቴ ልጅ ናት።ለምን ደብቀኸኝ ኖርክ ብትለኝ፣
ለአባቴም ለእናቴም ስል ነው ። አባቴ ፣ እናቴ እንዳትቀየም ብለው ፣ ምና
ልባትም ከቅማንት በመውለዳቸው አፍረውበት ጭምር ሊሆን ይችላል ፣
በድብቅ ይዘውት ኖሩ ። እጎቴ በዚህ ተቀይማ ፣ የአባቴን አባትነት አስተ
ሕይወቷ ፍጻሜ እምቢ ብላ ቀረች ። ውርደትና ንቀት የማትወድ በጣም
ኩሩ ነበረች ። ላይሆንልኝ ቀረ እንጂ እጎትነቷ የሚያኮራ ... እኔንም አስ
ማለችኝ ። ታንጉት የልጅ ልጅ መሆንዋን እንዳላወጣ። ታንጉት ግን ላመ
ጣት ገና ልጅ ብትሆንም ላታውቅ የምትቀር አትመስለኝም።ዛሬያ የቴ
ዎድሮስ እጎት መባል ትፈልግ ኖሮ ይሆናል ። ያላደጋት ከመባል ፣ እጎ
ትነትዋን የደበቅሁት ምናልባት በቅማንትነትዋ ምህኖት መስሏት ይሆ
ናል ። የሰው አስተሳሰብ መቸም አስቸጋሪ ነው ።” ከዚያም አስተርጉ
የጻፈባቸውን ታሪክ በከፊል ታንጉት የነገረችው መሆንዋን ፣ ይህን
ንም ደብተራ አክሊሉ አወጣብሻለሁ ብሎ በማስፈራራት ለማምለጥ
እንድትረዳው ማድረጉን ተረኩለት ። የአምባ ጊዮርጊስን ጉዳይ ግን
አልነገሩትም ። የዚያ ዐይነት ምሥጢሮች ተቀብረው መቅረታቸው
የሚሻል መሆኑ ተሰማቸው ።

“እንተስ ቢሆን ፣ ቅማንት እጎቴ ናት ብዬ ብድርልህ ደስ ይልህ
ነበር ?” ሲሉ በሁለቱም ላይ የተጫነውን ትካዜ ለማቃለል ያህል በቀ
ልድ መልክ ጠየቁት ።

“ምነው ሌላው ሁላ ሴት እንደሷ ቅማንት በሆነ !” አለ ገብርዬ
ለታንጉት ያለው ፍቅርና ናፍቆት ድንገት ተቀስቅሶበት ።

“አዎ ! ለነገሩማ ቅማንት ሆነ ወይጦ ያው ሰው ነው ። ተሰው
ነቱ ላይ ልዩ ምልክት የለበት ። ብቻ ብዙው ሰው ፣ የዘመኑ ልማድ እስ
ረኛ መሆኑ አልቀር ይላል እንጂ ። እንሱ ልፋቱም ወገኔ ተንደዚህ ያለው
ልማድ እንዲላቀቅ አልነበር ።”

“ተዚህ ውጊያ በኋላም ገና ብዙ እንሠራለን ።”
ገብርዬ ትካዜያቸውን አይቶ ለማበረታታት ያለው ነበር ።

“ይመስልሃል ገብርዬ ?” ሲሉ ትኩር አድርገው አስተዋሉት ።
“ያም ሆነ ይህ ፣ ያለፈው ዐልፏል ። ወንድምዋ ምን ያህል ይወዳት እንደ
ነበረ ንገራት ።” ጉንጩን አገላብጠው ሳሙትና ትከሻውን በመዳፋ
ቸው ጠብ ጠብ አደረጉት ። “በል ሒድ ይቅናህ !”
ቁልቁለቱን ሲወርድ ዕንባ ቸፍ ያለበት ዐይናቸው ተከተለው .....

Meysor Bro
t.me/BooksandYou